# እውነተኛው ዓለም

# ሲገለጥ

በነብዩ ዳንኤል አቤ

መስከረም 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

Copyright © 2007 E.C

Prepared by

Prophet Daniel Abera

The Joy of God Presence

of Holy Spirit Universal Mission for Nation

Addis Ababa, Ethiopia

E-mail: pro.dany2007@yahoo.com

Phone: +251945239127 or +251945239128

# ማውጫ

ገፅ

## ምዕራፍ አንድ

## የጌታ መገለጥ

1. ኢየሱስ፤ የብርሃን አምላክ ........ 1

## ምዕራፍ ሁለት

## ጉዞ ወደ ምድር

2. የቫቲካን አደባባይ ........ 6
3. ኢየሩሳሌም ........ 12
4. ካባ፤ መካ መዲና ........ 21
5. በህንድ የተደረገ መንፈሳዊ ውጊያ ........ 27
6. በናይጀሪያ የተደረገ መንፈሳዊ ውጊያ ........ 29
7. የኢሉሚናቲ መንፈስ ........ 35
8. የምድር በረከቶች እና የሰይጣን ውጊያ ........ 64

## ምዕራፍ ሶስት

## ጉዞ ወደ ሲኦል

9. የሲኦል መልክ ........ 72
10. መሃመድ ........ 74
11. ውስጠኛው የሲኦል ክፍል ........ 78
12. ጓደኛዬ በሲኦል ውስጥ ........ 80
13. ታዋቂው የፖፕ ሙዚቃ አቀንቃኝ ........ 83
14. ኢትዮጵያዊው አፄ ........ 85

15. ሊቀ ጳጳሳቱ _____ 86
16. የእሳት ወንዝ _____ 87
17. ቡድሃ _____ 90
18. የዘሙት አዳሪዎችና የግብረ-ሰዶማውያን የእሳት ባህር _____ 94
19. ኢትዮጵያዊው ኢሉሚናት _____ 105
20. ታዋቂው ኢትዮጵያዊ ዳንኪረኛ _____ 114
21. የእስቶርቱ ደሁዳ _____ 117
22. ወላጅ አባቴ _____ 119
23. የሰይጣን ጉባኤ _____ 121
24. ሞቶ የተነሳው ብራዚላዊ _____ 136

## ምዕራፍ አራት

## አማራጭ መንገዶች

25. መንታው መንገድ _____ 170
26. ሰፊው ጎዳና _____ 172
27. ሶስቱ ማንነት _____ 175
28. የኢየሱስ መንገድ _____ 177
29. የሰይጣን ፈተና _____ 180
30. የሚዮን መንገደኛው _____ 181
31. ታሪከኛው ወጣት _____ 197

## ምዕራፍ አምስት

## ጉዞ ወደ ገነት እና መንግስተ ሰማያት

32. የጥፅሞን መንገድ _____ 207
33. ገነት _____ 209
34. ፃድቃን ሰማዕታት _____ 214
35. በእሳት የዳኑ _____ 215
36. የቀድሞው የኢትዮጵያ መሪ _____ 217

37. የገነት ከፍታ ______ 222
38. ኢትዮጵያዊው ሰማዕት ______ 227
39. ጥቂት ኦርቶዶክሶች እና ካቶሊኮች ______ 228

## ምዕራፍ ስድስት

## የእግዚአብሔር ዘላን እና አዲሲቱ ኢየሩሳሌም

40. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ______ 231
41. የእግዚአብሔር ዘላን ______ 239
42. ገሃነም እሳት ______ 254
43. የፍርድ ዘላን ______ 256

## ምዕራፍ ሰባት

## የመጨረሻው ዘመን የጊታ ትንቢት

44. የመጪው ዘመን የዓለም ገፅታ ______ 259
45. የመጨረሻው መጨረሻ ______ 275

በማይገባኝ ለእርሱ ግን ግልፅ በሆነ ቋንቋ እና ልሳን ካወራኝ በኋላ በሚገባኝ ቋንቋ "ይሄ ልሳን አለም ሳይፈጠር ጀምሮ እስከ ዘላለም የእኔን ስራ የሚገልፅ ሲሆን፤ ይህንን ልሳን በምድር ያለ ክርስቲያን ሁሉ እንዲያነበው ከራዕዩ መፅሃፍ መጀመሪያ ገፅ ላይ ፃፈው አለኝ እና ንግግሩን በመቀጠል ይህንን ልሳን በእምነት ሶስት ጊዜ የሚያነብብ ሰው በህይወቱ አዲስ ነገር ይሆንለታል፤ አዲስ ልሳን ይቀበላል፣ ጭንገፋ ከላዩ ላይ ይሰበራል፤ እስራቱ ይበጠሳል፤ ሸክሙም ይራገፋል፤ በሺታም አይሰለጥንበትም" አለኝ፡፡ ከዚያም "ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል"የሚል ድምፅ ሰማሁ፡፡

ኋላም ልሳኑን እንዳልረሳው በአእምሮዬ ውስጥ በመንፈስ ሲታተም ታወቀኝ፡፡ ራእዩን አይቼ ከተመለስኩ በኋላ መጀመሪያ የፃፍኩት ፅሁፍ ቢኖር ይህንኑ ልሳን ነው፡፡ ስለዚህ እንደተሰሩ ቃሉ ማንኛውም በጌታ የሆነ እና ይህንን መፅሃፍ የሚያነብብ ሰው ከእግዚአብሔር የተቀበልኩትን ይህንን ልሳን ለተከታታይ ሶስት ጊዜ በእምነት እና በመንፈስ በመሆን ካነበበ በኋላ እርግማን፣ጭንገፋ እና ድህነት በህይወቱ ላይ ለዘላለም አይሆንም፡፡ ይሄ ልሳን የመላእክትም አይደለም፤ የቅዱሳንም ልሳን አይደለም፤ ከራሱ ከእግዚአብሔር የወጣ ፍፁም ሰማያዊ ንግግር መሆኑን ለፍጥረት ሁሉ አበስራለሁ፡፡ እንባቢዎቼ ይህ በረከት በህይወታችሁ ዘመን ሁሉ በእናንተ እና በዘሮቻችሁ ላይ ይሆን ዘንድ የዘወትር ፀሎቴ ነው፡፡

## የከበረው የሰማይ ቋንቋ

*ማኑሰቴ ለውዳሪያ ተዎሚኪ*

*ያውማና ለሁዳሪ ቦላቴ*

*ሰከማኒ ለቡሩያ ሃዉንቴ*

*ሰመርኒዮ ለሰባዬ ሊማሰከ*

*ሜሻዳን ጁኛ ሺባቡላ*

ሀውብሊያ ዊራድ ቶባ
ሲረምን ጀነኮሪና ሁሎቶ
ሙርጼ ታጉ አቡባ
ያያውሉ ታሬጋ ሃቶካሙ
ዜሬዋ የእውካን ታምናን
ፈረሃውካ የኢጀማ ሃኑና
ሺላዷጉ ያሚያና ሃይዌ
ለገንዳ ሃድሪካ ማገዴሬ
ላዱቡራ ሸካዷሮ ሃበን
የአዷዱ ሺኢሬጋ ጊርዳበ
ማቶካ ሃይውዳን ኮንዶሮ
ጆንዷ ካማን ቡንዷያዱ
ወርናዷያ ጀመርዷ ካሞዶ
ጂካን ለቡንሹማ ዷርዳም
ፍሮፖቴ ሃሙኪያዶ ዷሬም
ሀውላኪያን ዘመርታን ጂጋር
አሬጋዴ ዘኮሬቶ ጀምር
ሃውቶኪቶ ሬዱያዳ ታሪም

ለሜን ሀሌሉያ ይሁንልን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ:: የዚህን መፅሃፍ ምስጢር በግልፅነት በማሳወቅ ጌታ በመንፈሱ ከእናንተ ጋር ይሆን ዘንድ እመኛለሁ:: ለህይወት ለውጥ የሆነ መልካም የንባብ ጊዜ ይሁንላችሁ::

ጌታ እግዚአብሔር ህዝቡን እና ርስቱን ለዘላለም አይጥልም

ኦቢይ ዳንኤል አበራ

# እማኝነት

ይህንን ራእይ የሰጠ ልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን። ከእግዚአብሔር ሰው ከነብይ ዳንኤል እበራ ጋር ከተገናኘሁበት ጊዜ ጀምሮ በእርሱ ላይ ስላለው የጌታ ፀጋ ባለማቋረጥ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። ይህ የእግዚአብሔር ባሪያ ህይወቱን ለጌታ ሙሉ ለሙሉ በመስጠት ፈፅሞ ራሱን የካደ አገልጋይ ሲሆን ይህንን ራዕይም ከእግዚአብሔር እንደተቀበለ ህያው ምስክር መሆኔን ለመግለፅ እወዳለሁ። ራዕዩን ከመቀበሉ አስቀድሞ ባሉት ጊዜያት በእርሱ ውስጥ ሲተላለፉ የማያቸው መልእክቶች ፍፁም እውነት በመሆናቸው እና ብዙ ቅዱሳን ከዚህ ፀጋ ሲካፈሉ በመመልከቴ ራሴን እንደ እድለኛ እድርጌ እቆጥራለሁ።

ቀደም ሲል ጌታ በተለያዩ እገልጋዮች ወደ መንግስተ ሰማያት እንደሚወስደው እና ታላቅ መፅሃፍ እንደሚፅፍ ሲናገረው ስሰማ በመቆየቴ "ጌታ ለአምስት ተከታታይ ቀናት እወስድሃለሁ ብሎኛል" ሲለኝ ምንም ጥርጥር አልተሰማኝም ነበር። ነገር ግን ሰው እንደመሆኔ መጠን ብዙ ጥያቄዎች በአዕምሮዬ ቢመላለሱም አብሬው መፀለዩን በመቀጠል የሚሆነውን ነገር በጥንቃቄ መከታተሌን ቀጠልሁ። በኋላም ሐምሌ 7/2006 ዓ.ም እሁድ እለት በቤቱ ውስጥ አብረን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተን እየፀለይን ሳለ ከዚህ ቀደም በላዩ ላይ ከማውቀው ልምምድ እጅግ ባለፈ በመነቃቃት ሲፀልይ ከቆየ በኋላ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ ላይ በድንገት ተዝለፍልፎ ሲወድቅ በድንጋጤ እንስቼው እያገላበጥኩ ስመለከተው ፍፁም እንደ ሞተ ሰው ሆኖ ነበር። ምንም እንኳን የሰውነቱ ሙቀት እንዳለ ቢሆንምትንፋሹ ግን ፈፅሞ ቆሞ ነበር። ከዚያ እንደምንም ሰብስቤ በፍራሹ ላይ አስተኝቼ ብጠብቀውም ሊነቃ ባለመቻሉ የማደርገው ነገር ጨንቆኝ በውስጤ "ሞቶ ቢቀርስ" እያልኩ በመጨነቅ መፀለዩን ቀጠልሁ።

ከተንበረከከሁበት ስፍራ በፍጥነት ተነስቼ ስልኩን አንስቼ ስመለከተው እና ነብዩ እንደሆነ ሳውቅ ስልኩን ማንሳቴን ትቼ መሬት ላይ በመውደቅ ጌታን ለረጅም ሰዓት ካመሰገንሁ በኋላ በተደጋጋሚ ስልኩ ይጮህ ኖሮ ካለሁበት የደስታ ስሜት ተነስቼ ስልኩን ላነሳው ስል ተቋረጠ። ወዲያውም መልሼ ወደ ስልኩ ስደውል ጥቂት ጊዜ ከጠራ በኋላ "ሰላም ላንተ ይሁን" የሚል የማወቀውን የነብዩን ድምፅ በመስማቴ እንደገና ሌላ የማላውቀው ስሜት ሲወርረኝ እንባ በዓይኖቼ ሞልቶ በጉንጮቼ ላይ በመውረድ ፊቴን አራሰው። በሲቃ በሚቆራረጥ ድምፅም ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ነብዩ ፍፁም በተረጋጋ መንፈስ አረጋግቶኝ ጠዋት እንድንገናኝ ተቀጣጥረን ስልኩን ዘጋን። እኔ ግን ከነብዩ በወጣው ድምፅ አንዳች የመንፈስ ቅዱስ ሃይል ነክቶኝ ኖሮ ዓይኔ ፈጥጦ ሌሊቱን በፀሎት አሳለፍኩት።

በማግስቱ ጠዋት ሐምሌ 13/2006 ዓ.ም ወደ ነብዩ ቤት ሄጄ ቤቱን ከፍቼ ወደ ውስጥ እንደገባሁ አንዳች ሃይለኛ መንፈስ ነክቶኝ ወለሉ ላይ ስወድቅ ነብዩ ተነስቶ እጄን ጭኖ ሲፀልይልኝ ባለ ሃይለኛ መንፈሳዊ መነቃቃት ውስጥ ገብተን ለሁለት ሰዓታት አንዳችም ሲጋዊ ንግግር ሳንነጋገር በመንፈስ ሰክረን ቆየን። በኋላም ተረጋግተን እየተጨዋወትን ነብዩ ፍፁም ድሮ እንደማውቀው አንዳች የድካም ስሜት ሳይታይበት ፍፁም ፊቱ አምሮ እና ደምቆ እመለከተው ነበር።

ከዚያም ተነስቶ ሻወር ከወሰደ በኋላ ምሳ ለመብላት ተያይዘን ስንወጣ አስቀድሞ ነብዩን ያውቁት የነበሩ ሰዎች ምንም እንኳን ምስጢሩን ባያውቁም "እንዴት ነው ያማረብህ? ፊትህ እኮ ያበራል" እያሉ ይናገሩት ነበር። እርሱ ግን ድሮ ከማውቀው ፍፁም ሌላ ሰው ሆኖ ተለዋውጦ በሁለንተናው የእግዚአብሔር ክብር ተሞልቶ እመለከት ነበር።

ከዚያ በኋላም በፆም እና በፀሎት ሆኖ ለሁለት ተከታታይ ወራት በየቀኑ በአምስቱ ቀናት የሰማይ ቆይታው ያየውን በፍፁም ትኩረት አገልግሎቱን ሁሉ

በማቆም ይፅፍ ነበር፡፡ ስለዚህ ይህንን የራዕይ መፅሃፍ የምታነብቡ ሁሉ ይህ መልእክት ከእግዚአብሔር ስለመሆኑ ባለማመን ጠንት ከጌታ መልእክት እንዳትጎድሉ እኔ ህያው ምስክር በመሆኔ ከተፃፈው የበለጠ በመንፈስ ቅዱስ ሃይል እግዚአብሔር ምስጢራቱን እንዲገልፅላችሁ እና እንድትጠቀሙ የዘወትር ልመናዬ እና ፀሎቴ ነው፡፡ የጌታ ሰላም እና ፀጋ ለሰው ልጆች ሁሉ ይሁን፡፡ አሜን፡፡

ሽመልስ ጌታቸው(በኢ.ኢ.ዩ. የፒ.ኤች.ዲ ተማሪ)

# ምዕራፍ አንድ

## የጌታ መገለጥ

### ኢየሱስ፣ የብርሃን አምላክ

ሰኔ 16/2006 ዓ.ም በአባታችን በቁስ በሊና ሳርካ መኖሪያ ቤት በተገኘሁበት ወቅት የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሳቸው በኩል መፅሃፍ እንደምፅፍ በተደጋጋሚ መልእክት ከመጣልኝ በኋላ በማስከተልም በሌሎች አገልጋዮች እና ነብያት እግዚአብሔር መንግስተ ሰማያት እና ሲኦልን እንዲሁም አለማትን ሁሉ ሊያሳየኝ እንደሚገለጥልኝ እና ለየት ያለ በአለም ላይ አነጋጋሪ የሆነ መፅሃፍ እንደምፅፍ ጌታ ይናገረኝ ጀመር።

በኋላም በመዲናችን በአዲስ አበባ በአንድ ፕሮግራም ላይ እግዚአብሔርን ካገለገልሁ በኋላ በአንዲት ነብይት በኩል እግዚአብሔር በቅርብ ቀን እንደሚወስደኝ እና መንግስቱን ሁሉ እንደሚያሳየኝ ከተናገረኝ በኋላ በመቀጠልም "ሰማያት ተከፍተው ታላቅ ዘይት ከሰማይ ያለማቋረጥ በላይህ ላይ ሲፈስስ አመለከታለሁ" ስትለኝሙሉ ለሙሉ በመንፈስ አይኖቼ ተከፍተው ዘይቱን እመለከት ጀመር። እርሷም ንግግሯን በመቀጠል "በአለም ካርታ ሉል ላይ ስትራመድ አያለሁ፤ ያለማቋረጥ ከሚፈስስብህ ዘይት የተነሳ ከኋላህ በእግር ዱካህ ዘይቱ ወርቅ ሆኖ እየተንጠባጠበ ሰዎች ሁሉ ከዱካህ ወርቅ ለመውሰድ ሲሻሙ ተመለከትሁ" አለችኝ።

ከዚያም በኋላ ወደ ቤቴ ገብቼ በመንፈስ ተነቃቅቼ እየፀለይኩ የመጣልኝን መልእክት ማሰላሰል ጀመርሁ። ኋላም የጌታ መንፈስ ለልቤ ይናገረኝ ጀመር። "ከነገ ጀምሮ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ወደ መንግስተ ሰማያት እወስድሃለሁ፤ እዚያም የማሳይህ እና ለህዝቤ የምልክህ መልዕክት ስላለኝ ተዘጋጅ" አለኝ።

ይህንኑ ድምፅ በተከታታይ ለሶስት ጊዜያት ከተናገረኝ በኋላ ፀሎቴን ጨርሼ ከተኛሁ በኋላ እንደገና በራዕይ "ልጄ ተዘጋጅ መንግስቴን ታያለህ" የሚል ድምፅ ከብርሃን ውስጥ በተጥታ ሲናገረኝ ሰማሁ፡፡ ስለዚህ ሲነጋ መዘጋጀት እንዳለብኝ ማሰብ ጀመርሁ፡፡ በኋላም ሐምሌ 7/2006 ዓ.ም ለአንድ ወዳጄ እግዚአብሔር እንዲዚህ ተናግሮኛል ለአምስት ተከታታይ ቀናት ከጌታ ጋር እሆናለሁ አልኩት፡፡ እርሱም "እግዚአብሔር ከተናገረህ ይሁንልህ ጥሩ ነው" የሚል መልስ ከሰጠኝ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተን አብረን መፀለያችንን ቀጠልን፡፡

ከዚያም ያለማቋረጥ በልሳን እየፀለይን እና የእግዚአብሔርን ፊት በመፈለግ ቢያምና በፀሎት ሆነን ሳለን አስቀድሞ ከነበረኝ ልምምድ በእጥፍ ውስጤ በመንፈስ ቅዱስ ይነቃቃ ጀመር፡፡ ሀሴት እያደረግሁ በመንፈስ ተሞልቼ በውስጥ መንፈሴ ወደ እግዚአብሔር በሃሴት ስገሰግስ ሳለሁ በድንገት ሰውነቴ መንቀጥቀጥ ጀመረ፤ ምድርም እንደ መናወጥ የምትል መሰለኝ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ፀሎቴን አላቆምኩም ነበር፡፡

ወዲያውም ከውጪ ወደ ውስጥ መኪና እንደሚያበራው እንደ ትልቅ ፓውዛ ከቤቴ በር አቅጣጫ ወደ ውስጥ ሀይለኛ የብርሃን ጨረር ይገባ ጀመር፡፡ ከዚያም ሁለት መላእክት በግራ እና በቀኜ መቆማቸውን ተገነዘብሁ፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ አይኖቼን ስከፍት በርግጥም በቀኝና በግራ በሁለት በኩል የተሳለ እና የእሳት ነበልባል የሚተፋ ሰይፍ ይዘው በአጠገቤ ቆመው አየኋቸው፡፡ ይህን ጊዜ ልቤ መደንገጥ ስትጀምር በቅፅበት አይን የመኖሪያ ቤቴ በር ወለል ብሎ ሲከፈት እና በጭላንጭል ይገባ የነበረው ታላቅ ብርሃን በሃይል ሲደምቅ ማየት ጀመርሁ፡፡

ወደ ቤቴ የገባው ይህ ብርሃን ዓይኔ ሊቋቋመው የማይችለው ከፀሃይ ሰባት እጅ የደመቀ ሆነብኝ፡፡ እንደ ፓውዛም ይበራብኝ ጀመር፡፡ ይህን ጊዜ ከዓይኔ ላይ ቅርፊት መውደቅ ጀመረ፡፡ ቅርፊቱ ከዓይኔ እየወደቀ ሳለ በድንገት ዓይኔ ለቅፅበት

መንግስቱን ከዛሬ ጀምሮ ለተከታታይ አምስት ቀናት ስለማስጎበኝህ በርታ አጅግም ፅና፤ ለአለም ህዝብ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሰዎች መልዕክቴን ታደርስልኛለህ እና በርታ" ብሎ አበረታኝ። ቀኝ እጄንም ይዞ በብርሃኑ ላይ ሲያራምደኝ ሲጋዊ አካሌ እንደተኛ ሰው በመኝታዬ ላይ ሆኖ አየሁት።

በብርሃኑ ላይ እየተራመድን የብርሃን ሉል የሚመስል መጓጓዣ ውስጥ ገባን እና በቀኙ እንድቀመጥ አደረገኝ። የተቀመጥሁበት ወንበር እጅግ ምቹ በመሆኑ እየተገረምኩ በመፍራት እና በመንቀጥቀጥ ጌታን ማስተዋል ጀመርሁ። እጅግ ነጭ የሆነ ልብስ እስከ እግሩ ድረስ ለብሶ ነበር። ወገቡንም እጅግ በሚያምር እና በእንቁ በተንቆጠቆጠ የወርቅ ቀበቶ አስሮ ነበር። ከአካሉም ኃይል ይወጣ ነበር። ፊቱ ከፀሃይ ሰባት እጅ የደመቀ ሲሆን እጅግ ሩህሩህ የሆኑ የፍቅር ዓይኖች ነበሩት። በቀኝ እጁ የፅድቅ በትር ይዞ ነበር። በትሩም የአለም ካርታ ሉል የሚመስል ጠፈር በእንቁ ላይ ያለማቋረጥ የሚሽከረከርበት አናት ነበረው።

ከዚህ ሉል መሳይ አናት በታችም እየቀጠነ የሚወርድ የወርቅ ዘንግ ነበር። እግሩ በእሳት እንደጋለ ነሃስ መስሎ 'የቅድስና መጫሚያ' የሚል ፅሁፍ በጉልህ የተፃፈበት በወርቅ እና በእንቁ እንዲሁም በከበሩ ድንጋዮች የተዋበ መጫሚያ ተጫምቶ ነበር። የጫማውም ዲዛይን ልክ የኢየሱስን የህይወት ታሪክ በሚዘግበው "ኢየሱስ" በተሰኘው ፊልም ውስጥ እርሱን ሆኖ የሚተውነው ሰው የተጫማው ጫማ አይነት ዲዛይን ነበር። በቀበቶው ላይ 'የነገስታት ንጉስ የይሁዳ አንበሳ' የሚል ልዩ ፅሁፍ እንደተፃፈበት አስተዋልሁ። ገዝም ብዬ ሳየው ውስጤ በሃሴት እና በደስታ በቋንቋ ልገልጸው በማልችለው ሁኔታ ተሞላ። ይህንን ሁሉ ነገር የተረዳሁት በማይከር ሰከንድ እድሜ ውስጥ ነበር።

በኋላም ጌታ በእጁ አቅፎኝ ጥዑም ወንድማዊ በሆነ መንፈስ ፀጉሬን እያሻሸኝ "ልጄ ከማህጸን ሳትወጣ ነበር ያወቅሁህ ለክብሬም የመረጥሁህ። ነገር ግን ሰይጣን ሊገድልህ ገና በህፃንነትህ ወጥመድ መዘርጋት ጀመረ። ገና የአራት ወር

ህፃን እያለህ ከእህትህ እጅ አምልጠህ ወድቀህ የሳተን ጠርዝ መሃል እናትህን መታህ፡፡ ከዚያም እህትህ ደንግጣ ስታነሳህ ፊፅመህ ሞተህ ነበር፡፡ ታዲያ ግራ ገብቷት እያለቀሰች ስታገላብጥህ መንቃት ተሰኖህ ሳለ እኔ መጥቼ ዳግመኛ በህይወት እንድትኖር አደረግሁህ፡፡ ይኸው ጠባሳው በጭንቅላትህ ላይ" ሲለኝ የራሴን አካል በማየት ከህፃንነቴ ጀምሮ የነበረብኝን ጠባሳ እስከ አንጎሌ ውስጥ ድረስ ዘልቆ አየሁት፡፡

ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አለኝ "ከተወለድህበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከተለያዩ አስር ሞቶች ያዳንሁህ እና ያተረፍሁህ፤ ከሰይጣን፣ ከሰዎች፣ እንዲሁም ከራስህ ጠብቄህና ሸሽጌህ በጉያዬ የያዝኩህ፤ ሰይጣን ካቀነባበራቸው ከተለያዩ ወንጀሎች እና ሀጥያቶች፤ ወገኖችህ ከሚያደርሱብህ ትችት እና ከስ የታደግኩህ እኔ ነኝ" አለኝ፡፡ "በመውጣት በመውረድ በሸለቆ እና በተራራ ደግፌህ የክብር እቃ ሳደርግህ ለዚህ መለአከት መልዕክተኛ እንድትሆን ሾምሁህ፡፡ መልኬ በአንተ ይታያል እና በምንም ነገር አትፍራ ልጄ" ሲለኝ እኔም "ጌታ ሆይ እባክህን እኔን አሁን ማን ያምነኛል ታሪኬ እኮ እጅግ መጥፎ ነው በሰው ፊትም የሚያቆመኝ አይደለም" ስለው "የላክሁህ እኔ ነኝ መልእክትህን የማይቀበል እኔን አይቀበልም፡፡ ስለዚህ አሁን የማሳይህን ነገር ሁሉ በመፅሃፍ ፃፈው፡፡ ይህንን መልዕክት ሊታደርስ በምትችልበት በማንኛውም በአለም ውስጥ ባለ ቋስ ተጠቀም፡፡ በነቹ ድምፄን ይሰማሉ የእኔ ያልሆኑት ግን አይሰሙኝም፡፡ ከለዚህ አትፍራ እስከ አለም ዳርቻ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ይህንን የመጨረሻው ዘመን መልዕክቴን አድርስ" ብሎኝ በብርሃን ሉል ውስጥ ሆነን መጓዝ ጀመርን፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ጉዞ ወደ ምድር

### የቫቲካን አደባባይ

ወዲያውም እንሄድባት የነበረችውን የብርሃን ሉል ከፍ በማድረግ ጠፈርን በሙሉ በአንድ ጊዜ እንድታሳየኝ አደረገ፡፡ በመቀጠልም ከጠፈር ውስጥ ምድርን ነጥሎ አውጥቶ የሰዎችን እንቅስቃሴ በሙሉ አሳየኝ፡፡ በእንቅስቃሴያቸውም ተመስጬ እየተመለከትሁ ሳለሁ ጌታ "አይዞህ አሁን ወደ ሰማይ ሳይሆን ወደ ምድር ነው የምወስድህ በውስጧ ያለውን የታላላቆችንና የታናናሾችን ገመና አሳይሃለው" ብሎኝ በብርሃን ሉሏ ውስጥ ሆነን ወደ ምድር ወሰደኝ፡፡

በሰከንዶች ጊዜ ውስጥ ወደ አንድ ታላቅ አደባባይ ደረስን፡፡ በአደባባዩ ዙሪያ ያሉ መስቀል ያለባቸውን ረጃጅም ህንፃዎች ስመለከት ቤተክርስቲያን እንደሆነ ተገነዘብሁ፡፡ "ይህ ቦታ የት ይሆን?" ብዬ ሳስብ ሳለሁ አውቆ ጌታ ሰፍራው የቫቲካን ካቴድራል አደባባይ መሆኑን ገለፀልኝ፡፡ እንጓዝባት የነበረችውም የብርሃን ሉል በአንድ ደረጃ አጠገብ ከማረፏ በእራቱም አቅጣጫ ልክ እንደ ብርቱካን ከላይ ወደታች በመከፋፈል ብርሃኗን በጨረር መልክ ዘረጋች፡፡

ከብርሃን ሉሏም ወጥተን በደረጃው ወደ ውስጠኛው ክፍል እያለፍን ሳለ ብዙ የክህነት ልብስ የለበሱ አርኪስ መናፍስቶችን ተመለከትሁ፡፡ እነርሱም ገታ መግባቱን አይተው ለመሸሽ በመሯሯጥ ላይ ነበሩ፡፡ ሁሉም "ምስጢራችን ተጋለጠ ወየው ጠፋን" እያሉ በፊቱ ብርሃን እየተወጉ እንደ አቧራ ሲበኑ ተመለከትሁ እና ምን እንደሆኑ ከመጠየቄ በፊት ጌታ እጅግ ብሩህ የሆነ ፈገግታ በተላበሰ ፊት እየተመለከተኝ "ልጄ አሁን የተመለከትካቸው አርኩሳን መናፍስቶች ቤተክርስቲያኗ ውስጥ ባሉ አገልጋዮች ላይ በመሆን የእኔን ወንጌል ለመሸቃቀጥ

እና ለመበረዝ በካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰሩ ናቸው። በአገሊጋዮቹ አዕምሮ ላይ ሀሰትን ይዘራሉ" ብሎኝ ወደ አንድ ትልቅ አዳራሽ አስገባኝ።

በአዳራሹ ውስጥ ስንገባ እጅግ ብዙ ካህናት ቢጫ በቀይ ዘርፍ የሆነ የክህነት ልብስ ለብሰው መሃል ላይ በዙፋን ላይ በተቀመጠ ካህን ዙሪያ ይነታረኩ እና ይጨቃጨቁ ነበርና ማንም ሰው ጌታ መምጣቱን ያስተዋለ አልነበረም። ነገር ግን አንዲት ካህናቱን ስታገለግል የነበረች መነኩሴ ብቻ የጌታን በዚያ ስፍራ መገኘት ተረድታ ነበር። በመንፈሷም ሀሴት እያደረገች እግዚአብሔርን ታመሰግን ነበር። ከካህናቱ መሃከል ግን ይህ ሁሉ ሲሆን ወደ እኛ የተመለከተም ሆነ ቁብ የሰጠን ሰው አልነበረም።

ከፊት ለፊታችን በእኛ ትይዩ ካለ ከአዳራሹ ጫፍ ከመድረኩ በላይ እግዚአብሔርን ፈልገው ለአምልኮ የሚመጡ ሰዎች በእውነት እና በመንፈስ እንዳያመልኩ ብዙ አጋንንት ያደሩባቸው ግብረ-ሰዶማዊ ሰአሊያን አንዳንድ አጋንንታዊ መላእክት አብረዋቸው ሆነው በምስጢራዊ የአሳሳል ዘዴ ጌታ ኢየሱስን እና ማርያምን የሚመስሉ ነገር ግን በምስጢር የሚሳደቡ እና የሚያንቋሽሹ ብዙ ስእሎችን በመሳል ስራ ላይ ተጠምደው ነበር። መሀከል ላይም አንዲት መልከ መልካም መነኩሴ የመሰለች ሴት በማርያም ተመስላ፤ እስራ ሁለት ከዋክብቶችን አክሊል አድርጋ፤ በጨረቃ ምስል ላይ ተቈምጣ፤ እጆቿን ወደ ፊት ዘርግታ፤ ከእግሯ ጀምሮ አንድ ትልቅ ዘንዶ በላይዋ ላይ ተጠምጥሞ ከአንገቷ ስር ሆኖ የሚያዋራት ትመስል ነበር።

ከዚያም ስዕሉን እየተመለከትን ሳለ ዘንዶው በአንደበቷ ካህናቱን ያወራቸው ጀመር። እንዲህም አለ የእናት በሚመስል ድምፅ "ኑ ወደ እኔ ልጆቼ" እያለ ዘንዶው ሲጣራ ሰማሁት። ያኔ ታዲያ ሁሉም ቤቱ ውስጥ የነበሩት ካህናት ከመቀመጫቸው በአክብሮት ተነስተው በሰልፍ በምስሉ ፊት እያማተቡ ዘንዶውን እየተሳለሙ ሲያልፉ ሳለ አንዳንዶቹን በጭራው እየተጠመጠመ በመርዙ

ተሰብሳቢዎቹም አንዳንዶቹ ለጉብኝት ሌሎቹም ለዝና እንጂ በእውነት ባርኮትን የፈለጉ አይመስሉም ነበር። ከዚያ ይልቅ የጳጳሱን እጅ ለመንካት በመጋፋት እየተዋከቡ ነበር። የጳጳሱ እና የሁላቸው አምላክ የሆነውና ሊባርካቸው የተገባው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመሃከላቸው ቢመላለስም ማንም ትኩረት የሚሰጠው አጥቶ ከዳር ቆሞ ነበር። ታዲያ ሊቀ ጳጳሱ አባርካለሁ ባሉበት በዚያ ቅፅበት ሰይጣን ንግግራቸውን በማስቀየር እና በመልካም ምኞት መግለጫ በመተካት ቀድሞውም ወደ ህዝቡ መድረስ ያቃተውን ባርኮት ውሃ እንደሌለው ደመና እንጠልጥሎ አስቀረው። ስለዚህም የጳጳሱ ንግግር መልካም ምኞትን ከመግለፅ የዘለለ ለሰዉ የሚደርስ አንዳች ፋይዳ ሳያመጣላቸው ቀረ።

እንዲህም ሆኖ ግን ህዝቡ ይህንን ልዩ ክብር የማይገባውን የጳጳሱን ንግግር በተመስጦ ሲያደምጥ እና ድጋፍ ሲሰጥ እመለከት ነበር። በህዝቡ ውስጥ ሆነው አንዳንድ ምእመናን ለጌታ በሚያቀርቡት አምልኮ እና ስግደት ከሰማይ የሚመጣውን ባርኮትም የሚቀበለው በማጣት በመሬት ላይ ወድቆ የሚያነሳው አጥቶ ሜዳው ላይ ሲጣል ተመለከትሁኝ። ሁሉም ግን ያለማስተዋል ይረጋገጡት ነበር። ጌታም አዝኖ ከዚያ "ና ልጄ" ካለኝ በኋላ ተመልሰን በመጣንበት የብርሃን ሉል ውስጥ ስንገባ ሉሏም ተሰብስባ እኛም መጀመሪያ በተቀመጥንበት መቀመጫ ተቀምጠን ጉዟችንን በሰማይ ላይ ወደ መካከለኛው ምስራቅ አቅንተን ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ መጓዛችንን ቀጠልን።

አውጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝኩበት ፍቅር የሰጠኋቸውን ኪዳን እነርሱ ባለመጽናት ስላፈረሱት በኪዳኔም ስላልጸኑ ችላ አልኳቸው በመቀጠልም ከእስራኤል ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን ገባሁኝ፡፡ አሁን በገባሁት ቃል ኪዳኔ ህጌን በልቦናቸው እኖራለሁ በመንፈሳቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ህዝብ ይሆኑኛል፡፡ ያኔ ታዲያ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ትልቁ ድረስ በውስጣቸው አምላካቸው እንደሆንኩ ያለ ምንም መከሪና አስተማሪ ያውቁኛል፤ በደላቸውን እምራለሁ፤ ሃጥያታቸውንም አላስብም አለሁ ነገር ግን ይህም ሆኖ ወደ እኔ ሊመለሱ ኢቃታቸው እንጂ ሰምቶኝ የሚመለስ ማንም ሰው አልነበረም የሚሰማኝ ቢኖር ግን በእርጋታ ይቀመጣል ከመከራ ስጋትም ያርፋል" አለኝ፡፡

ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ስንገባ ከተማዋ በቱሪስቶች ተጨናንቃ ነበር፤ እንዲያም ሆኖ ግን በየሰዉ ላይ ስጋት ነበር፡፡. ከጎብኚዎቹም አብዛኞዎቹ ክርስቲያን ነን እያሉ ከሚያስተምሩ ቤተ-እምነቶች የሚመጡ ነበሩ፤ ከተማዋ ለሁለት ተከፍላ ግማሿ በዌስት ባንክ ቁጥጥር ;ስር ነበረች፡፡ የከተማዋም ምዕራባዊ ክፍል ጥንታዊዋ ኢየሩሳሌም የምትገኝበት አብዛኛዎቹ ታሪካዊ ቅርሶች የሚገኙበት አካባቢ ነበር፡፡ ከተማዋ አሁንም ብዙዎቹ ገጽታዎቿ ጥንታዊ አስመስለዋታል፡፡ ከዚያም በጺዮን ተራራዎች ላይ በሚገኘው የጥንታዊው ቤተመቅደስ ቅሪት በሆነው ምዕራባዊው ግንብ (ዌስተርን ዎል) በተባለው ስፍራ ደረስንና የብርሃን ሉላችንም አረፈች፡፡ ከእርሷም ወጥተን አካባቢውን ስንመለከትም አይሁድ በሰለሞን የተሰራው ቤተመቅደስ አካል ነው ብለው በሚያምኑት በዚህ ስፍራ ከሰው ቁመት እጅግ ከፍ ብሎ በቆመው ትርር መሳይ ግንብ አጠገብ ብዙ ሰዎች ቆመው እያነበነቡ አካላቸውን ጥምር በማንቀሳቀስ ፀሎት ያደርጉ ነበር፡፡

በፀሎታቸው ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የሚናገሩት ፍጹም የሚማርክ ቃል ቢሆንም፤ ጸሎታቸው ምንም ቢያምርም ወደ ሰማይ አይወጣም ነበር፤ አብዛኛው የታይታ ፀሎት ነበር፤ ከአንደበታቸው ይልቅ ውስጣቸው በአመጽና በክህደት ተሞልቶ ነበር፡፡ ሁሌጊዜ ከሰማያዊው መንግስት ይልቅ አሁን ያለው የእስራኤል ህልውና ጉዳይ የበለጠ ያሳስባቸዋል፡፡ በሰው ልብ የሆነው የአዲሱ ኪዳን

ከቃላቸው ይልቅ ይናገር ነበር፤ ሁሉም በትምክህት ተሞልተው ነበር። ሁሉም በሚባል ደረጃ ልክ እንዳደረጉት ኮፍያ አይነት መነጽር የሚመስል ፈጽሞ ወደ ውጪ የማያሳይ ጥቁር መጋረጃ ጨርቅ ነገር አጥልቀው ነበር። ቶራህ የተባለው ህጋቸው ሲነበብ የበለጠ ይጨልምባቸው ነበር። ሃለካሆ የተባለው ደግሞ ፔንታቶክና የአባቶቻቸው ልማድን በጥምረት ያየዘውን ህግ እንብበው ሳለማየት ሲማማሉ ተመለከትን።

በየፀሎታቸውም ውስጥ መሲሁ እንዲመጣ ደጋግመው እግዚአብሔርን ይጠይቃሉ። ነገር ግን የሚጠይቁት ጠላቶቻቸውን እንዲበቀልላቸውና ከዚህ ምድር ችግር እና መከራ እንዲያወጣቸው ለዚህችው ለምድር ስኬት እና ብልጽግና እንደሆን በየጸሎታቸው የሚያነበንቡት ነገር ያሳብቅባቸው ነበር። ካህኑም ለተሰብሳቢዎቹ ጠዋት፣ ቀትር፣ ማታ ሁልጊዜ ይህን ጸሎት ሻሃሪት፣ ሚንሃስ፣ ማሪብ፣ በማለት በቀን ሶስቴ በመከፋፈል ምእመኑ እንዲፀልዩ ካስተማሩ በኋላ እግዚአብሔር ፀሎታቸውን እንደሰማ በመናገርና በማስተማመን ፕሮግራሙ አበቃ። ነገር ግን ፀሎታቸው እንኳን በእግዚአብሔር ሊሰማ ቀርቶ ከቤቱ ጣሪያ በታች ነበር የቀረው። የነበራቸውን ትጋት ስመለከት ፀሎታቸው ባለመሰማቱ እጅግ አሳዘኑኝ።

ያኔ ታዲያ ከጌታ አይኖች ያለማቋረጥ የእንባ ዘለላዎች እየወጡ ጉንጮቹን አቋርጠው ወደ ምድር ሲወድቁ ምድሪቱ በእሳት ትቀጣጠል ነበር። ምድርም አፏን አውጥታ "ወየው ጠፋሁ፤ እነዚህ አመጸኞች ለምን ይረግጡኛል" በማለት በጥላቻ አልጎመጎመች። ነገር ግን አይሁዶቹ ፈጽመው ምንም እንዳልሆኑ በትዕቢት ተነፍተው ይንጎማለሉ ነበር።

እስከ አሁን ያለንበት ግዛት ሁሉ በዌስት ባንክ ውስጥ ነበር፤ ይሄ ምኩራብ ያለበት አካባቢ የአይሁዶች ሰፈር ነው የሚባለው። ወደዚህ ምኩራብ እና ወደ ዌስተርን ዎል ፀሎት ለማድረስ ከሆሰበት የአለም ክፍል እያንዳንዱ አይሁዳዊ በአመት አንድ ጊዜ ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም ለፀሎት ማድረግ ግዴታው ነበር።

ጌታም እንዲህ አለኝ "በአሁን ሰዓት አብዛኞቹ አይሁዳውያን በአሜሪካ ቢኖሩም ነገር ግን ከምዕራብ አውሮፓ ሃገሮች ጀምሮ ካናዳ፣ አርጀንቲና፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ሩስያ፣ ዩክሬን፣ አውስትራሊያ፣...ወዘተ ከሚገኙበት የተለያዩ አገራት በተቆጣጠሯቸው ፖለቲካዊ ስልጣንና ኢኮኖሚያዊና ሳይንሳዊ ምርምሮች ስለ ኪዳኔ ስለ አብርሃም ስል ብጎበኛቸውም ነገር ግን ዛሬም ድረስ ከእውነት መንገድ ሀሊናቸው ጠፍቶ በዚህችው አለም ላይ አይናቸው ተሰክቷል" አለኝና በብርሃን ሉላችን ጉዟችንን ከአይሁዶቹ ምኩራብ ሰሜናዊ አቅጣጫ 'አል አቅሳ' የተባለ መስጊድን አልፈን በኢየሩሳሌም በእስራኤል ግዛት በሚገኘው የአገሪቱ አስታዳደርም በኩል አድርገን እየሄድን ወደታች ስንመለከት ሳለ ሁሉም ሰው በየራሱ ስራ ላይ ተጠምዶ ነበር፡፡

ሁሉም ስለ እስራኤል እና ሃማስ ጦርነት በአንክሮ በተለያዩ የመረጃ መረቦች አማካኝነት ዜናዎችን አብዛኛው ህዝብ በትኩረት ይከታተል ነበር፡፡ ከዚያም እኛ ጉዟችንን በመቀጠል በሮም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ስር የሚገኘው የሴፑልቸር ቤተክርስቲያን በሚገኝበት ስፍራ ቆም ብለን ስንመለከት ሳለ ጌታ መቃብሩን ፈንቅሎ ሲነሳ የሚያሳይ ምስል ተመለከትሁ፡፡ ያን ጊዜ ይህ ስፍራ ጌታ ለሶስት ቀናት በመቃብር ያሳለፈበት ቦታ መሆኑን ተገነዘብሁ፡፡ በኋላም የተለያዩ የአለማችን አገሮች ቤተክርስቲያናት በኢየሩሳሌም የየራሳቸው የእምነት ገዳማት እና አብያተ ክርስቲያናት እንዳላቸው ለመገንዘብም ቻልሁ፡፡ ለምሳሌ ሮማ ካቶሊክ፣ የአርመናውያን እና የግብፅ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የመሳሰሉት አብያተክርስቲያናት ከተማዋን ከአይሁዶችና ከሙስሊሞች ጋር በመሆን በመቀራመት ይዘዋት ለመመልከት ቻልሁ፡፡

ጌታም በምድራዊቱ ኢየሩሳሌም ቦታ ለማግኘት የሚሯሯጡትን ሁሉ ይነቅፋቸው ጀመር፡፡ እንዲህም አለኝ "የተለያዩ መንፈሳዊ ነጋዴዎች ጉዞዎችን በማዘጋጀት ሰዎች እጅግ ብዙ ገንዘብ አውጥተው ኢየሩሳሌምን እንዲጎበኙ ሲቀሰቅሱ ኖረዋል፤ አሁንም በመቀስቀስ ላይ ይገኛሉ፤ አንዳንዶቹ እንዲያውም መንግስተ ሰማይ ለመግባት እንደ ዋስትና አድርገውም በማስተማር ላይ ናቸው፡፡ ይህንን ስፍራ ከመጎብኘት ይልቅ ለዚህ ጉዞ የሚያወጡትን ገንዘብ አጠገባቸው

ላለው ወንድማቸው ወይንም ለችግረኛ ሰው በመስጠት ወንጌሉን በሙላት ቢሰብኩበት ዋጋቸው የበለጠ ታላቅ ይሆናል፡፡ ብድራታቸውን እከፍላቸዋለሁ፡፡ ክርስትና ታሪክ አይደለም፤ እኔም ትዝታ አይደለሁም፡፡ ህያው አምላክ ነኝ፤ በእውነት ለፈለጉኝ እገኝላቸዋለሁ፤ ማንም የተጠማ ቢኖር በነፃ ወደ እኔ በመምጣት ውሃን ይግዛ ይጠጣም፡፡ አሁን አሁን በተለያዩ ክርስቲያኖች ጉዞ ወደ ቅድስቲቱ አገር እየተባለ የቅዱሳንን ገንዘብ ለመበዝበዝ በሚሮጡ ተከታዮች ህዝቤ እንዳይታለል እኔ በሁሉ ስፍራ እገኛለሁ፤ ግኡዝ አምላክ አይደለሁም፤ ይልቁንም ኢየሩሳሌም ሰለላሟ የሚሆናትን በዚህ ቀን ብታውቅ ኖሮ ይበጃት ነበር፤ ግን ምን ዋጋ አለው እስካሁን አይኖቿ እንደተጨፈኑ ናቸው፡፡

እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በእውነትና በመንፈስ ሆነው ሊሰግዱለት ይገባል፡፡ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው" በማለት ከተናገረኝ በኋላ በብርሃን ሉላችን ሆነን በቤተ እስራኤል በኩል አድርገን ወደ ሰሜን እስራኤል በዛብሎን ሸለቆ ወደሚገኘው ወደ ገሊላ አካባቢ ስንጓዝ አካባቢው እጅግ ለምለም የሆነ የእርሻ ስራ የሚከናወንበት ምድር ነበርና ባየሁት ልምላሜ በመማረክ በጣም ደስ አለኝ፡፡ ያኔ ታዲያ ጌታም "በዚህ በገሊላ ክፍል ብዙ ተመላልሼ ያስተማርኩበት ስፍራ ነው" አለኝ፡፡

ከዚያም በቲቤሪያስ ሃይት (ገሊላ ሃይቅ) በኩል አድርገን ወደ ሰሜን ምዕራብ እስራኤል ቲቤሪያስ (ጥብሪያዶስ) ወደምትባል ከተማ ተጉዘን እጅግ ብዙ የአይሁድ መሪዎች መቃብሮችን ተመለከትን፡፡ እንዲያውም በጌታ ላይ ስቅላት እንዲፈረድ የተባበሩ ብዙ የአይሁድ መሪዎች እና ካህናት በ70ኛው ክፍለ ዘመን ኢየሩሳሌም ስትወድም ወደዚህችው ከተማ በመሸሽ በዚሁ ስፍራ መሞታቸውን እና መቀበራቸውን ጌታ ግን ጥንትም ያለ ዛሬም ለዘላለም ህያው ሆኖ የሚኖር መሆኑን ከካህናቱ ታሪክ ጋር እያይዞ ነገረኝ፡፡

በኋላም ጉዟችንን በመቀጠል ከሰሜን ምስራቅ ወደ ምስራቅ የሜዲትራኒያን ባህር ጠርዝ መጥተን ቴል አቪቭ ደረስን፡፡ ይህች ከተማ ደግሞ እጅግ ንፁህና ዘመናዊ መሆኗን ለማየት ቻልሁ፤ የብዙ አይሁዶች መኖሪያም ነበረች፤ ብዙዎቹ

ፒማቸውን አስረዝመው ጥቁር በጥቁር ለብሰው ከፍ ያለ ኮፍያ ያደርጉ ነ፤ር፤ በየምኩራባቸው ስርዓተ አምልኮን ያደርጋሉ፤ ነገር ግን ሁሉም አየሩን ዘሏቆ የሚገባ አልነበረም።

በቴል አቪቭ 'ቤን ጉሪየን' አየር መንገድ አካባቢ ነበር አንዳንዶች የአይሁድ ምኩራቦችን ማየት የቻልነው። ከቴል አቪቭ ወደታች በስተደቡብ የምትገኘው 'ሮሆቦት' የተባለችው አነስተኛ ከተማ ላይ ዋይዝማን ኢንስቲትዩት የሚባል እጅግ ንፁህና ዘመናዊ ህንፃ ነበረባት፤ ይህቺም ከተማ ይስሃቅ ጉድጓድን ሲቆፍር ሁለት ቦታ ከደፈኑበት በኋላ ሶስተኛ ለቆፈራት የውሃ ጉድጓድ 'ሮሆቦት' ብሎ ስም በሰጣት ስፍራ የተመሰረተች ከተማ ናት። በእርሷም በኩል አልፈን በደቡብ እስራኤል 'ኤሽት' ወደተባለችው የወደብ ከተማ ስንመጣም በወታደራዊ ካንፖችና በተለያዩ የጦር መሳሪያዎች የተከበበች ከተማ ነበረች። ከዚያም ወደ ደቡብ ምዕራብ አድርገን 'የሙት ባህር' የተባለውን የጨው ባህር ከተመለከትን በኋላ ጌታም ስለ ህዝቦቹ ልብ ደንዳናነት እያዘነ የእስራኤልን ምድር በዞርንበት በዚያን ጊዜ ሁሉ ከአይኖቹ እንባ ዝም ብሎ ያለማቋረጥ ይፈስስ ነበር።

ከፍ ብለን አገሪቱን ሁሉ ስንመለከት ጥቁር ጥላሸት የመሰለ ድቅድቅ ጨለማ የእስራኤልን ህዝብ ሁሉ ከድኗቸው ነበር። ሁሉም ልክ ጌታን ሰቀለው፤ ሰቀለው ብለው እንደጮሁባት ምሽት አይነት ከህደት እና ጨኸት ይታይባቸው ነበር። ከእውነት መንገድም ስተው ነፍሳቸውን ጠልተዋት ነበር። በሰማይ ያለው አምላካቸው ላይ ከመታመን እና ከመደገፍ ይልቅ በራሳቸው የጠነከሩ ለመሆን ብቻ ቀን ከለሊት ይደክሙ ነበር። ፀሎታቸውም እነርሱ የአለም የበላይ ገገር የሚሆኑበት ጊዜ እንዲፈጥን ብቻ ነው። ልመናቸውም ስራቸውም ይኸው ብቻ ነበር።

ጌታም እንዲህ አለኝ "ለተመረጡት በስሜ ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጅነት ስልጣን እንደተሰጣቸው እና ህዝቤ እንደሆኑ ሁሉ ነገር ግን ስለ እስራኤል ህዝብ እና ቅሬታዬ መማለድን እና መፀለይን እንዳይረሱ አሳስባቸው፤ ቅሬታዎች በፀጋ

ይድናሉና፤ ነገር ግን በስራ አይደለም። በመሆኑም የአይሁዶቹ እምነት ወደ መታሰቢያነት፤ አፀዶቹም ወደ ቅርስነት ተቀይረዋል።

አስቀድሜ በሙሴ እንዳዘዝሁት እንደ ቃሌ እንኳን አይደለም የሚኖሩት፤ ይሄ የእስራኤል ትውልድ በታሪክ ነው የሚኖረው። አይናቸው ከሰማያዊው ርስት ይልቅ ምድራዊው ላይ ተተክሷል፤ ሁልጊዜ የህግ መፅሃፍትን ሲያነብቡ የበለጠ ልቦናቸው ይጨልማል። የመረጥኳቸውን ረስተውኝ 'እኛ ከሰው ሁሉ የተመረጥን ህዝቦች ነን' ብለው ያምናሉ። መሲሃቸውን እኔን ግን ጀርባ ሰጥተውኛል፤ አይሰሙኝም፤ ዛሬም ልባቸው ደንድኗል፤ አይናቸው ታውሯል።

ጌዲዮን በዘመኑ ምድያማውያንን በእኔ ድጋፍ አጥፍቶ እኔ ከትቢያ ላይ ያነሳሁትን አምላክ በማረከው ምርኮ ለውጦኝ ከምርኮ ባገኘው ጌጣጌጥ ጣኦት ሰርቶ 'ይሄ ነው ያዳነን' በማለት እራሱም ስቶ እስራኤልን አንዳሳተና ፍጻሜውም ለእስራኤልና ለቤተሰቡ ለራሱም መሰናከያ እንደሆነ ሁሉ እባካችሁ በቁሳቁስ አትለውጡኝ በልልኝ ለአገልጋዮቼ፤ በመንፈስ ተመሩ እንጂ ስርዓትን አትከተሉ፤ ይሄ ጌታ በምድር ሳለ እዚህ ጋር ነው የሞተው፤ እዚህ ላይ ነው የተሰቀለው፤ በዚህ መንገድ ነው የሄደው፤ እያላችሁ አታምልኩ። እኔንም ፍለጋ ከአገር አገር አትባዝኑ፤ ይልቁንም ህዝቤ ከሆናችሁ እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ፤ ተቀባበሉ፤ በእናንተ መሃከል ችግረኛ አይኑር፤ ደሃዎቹን አገልጋዮቻችሁን ተመልከቱ፤ ማንም እኔን ሊከተል የሚወድ ቢኖር እራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።

ማንም እንዳያሲታችሁ ተርቤ ያላበላኝ፣ ታርዤ ያላለበሰኝ፣ እንግዳ ሆኜ ያልተቀበለኝ፣ ታምሜ ያልጠየቀኝ፣ ታስሬ ያልጎበኘኝ፣ የእኔ ሊሆን አይችልም። ለሰው ሁሉ እንደ ስራው የምከፍልበት ጊዜ ይመጣል" አለኝ። እኔም "ጌታ ሆይ መቼ አይተውህ ነው" ብዬ ስጠይቀው በምድር ላለው ሰው ለአንዱ በማንኛውም ሰዓት በስሜ ያደረጉትን በሙሉ ለእኔ እንዳደረጉ አድርጌ እቆጥረዋለሁ፤ ያላደረጉትን ሁሉ ግን ወደ ዘላለም ቅጣት አወርዳቸዋለሁ፤ ነገር ግን ጻድቃኖቼን ወደ ዘላለም ህይወት እና እረፍት አገባቸዋለሁ" አለኝ።

"ማንኛውም መብራትን አብርቶ በስውር የሚያስቀምጠው ማነው? ነገር ግን ወደ ቤቱ የሚገቡ ሰዎች አጥርተው ያዩ ዘንድ በመቅረዙ ላይ ከፍ ባለ ቦታ ያኖረዋል እንጂ:: ለሰው የሁለንተናው መብራት አይኑ ናት፤ አይኑ ጤናማ በሆነች ጊዜ ያኔ ሰውነቱ ሁሉ ጤናማ ይሆናልና፤ ያኔ ታዲያ ሁሉም ነገር ብሩህ ይሆንለታል፤ ነገር ግን የሰው አይኑ ታማሚ በሆነች ጊዜ ሰውነቱን በሙሉ ጭለማ ይወርሰዋል፤ ስለዚህ ሰው ሁሉ በአይኑ አስተውሎ ይመልከት:: እንዳች የጭለማ ቁራጭ በህይወቱ የሌለ እንደሆን ያንጊዜ ብሩህ ሆኖ መብራቱ ያበራለታል" ብሎ ካለኝ በኋላ በብርሃን ሉሷ በአለራሒል ደቡብ ምስራቅ በኩል አድርገን ወደ ሳውዲ አረቢያ ጂዳ ጉዟችንን ቀጠልን::

ውስጥ ሲጠናቀቅ በእውኑ አለም የእስራኤል ጆቶች አካባቢውን በሚባአልና በቦምብ በመምታት ደበላልቀውት ፈፅመው አመድ ሲያደርጉት ተመለከትሁ።

በመቀጠልም ይህ ካባ መፍረሱን እና መውደሙን የተመለከቱ አለም ላይ ያሉ ሙስሊሞች ተረዳድተው እንደገና መስጊዶቹን ቢያስገነቡም ነገር ግን ሀይሉ ፈፅሞ ተሟጦ ነበር እና በታውም የአምልኮ ስፍራ መሆኑ ቀርቶ እንደ ሙዚየም አድርገውት የሰው ልጆች ከተለያየ ቦታ እየመጡ ሲጎበኙት ብቻ ተመለከትሁ። ይህ የሰይጣን ተንኮል ለአንዴና ለዘላለም ዝከሩ ጠፋ፤ ጌታም እንዲህ አለኝ "እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ፤ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እኔን ብቻ ያመልኩ ዘንድ ንገራቸው።

ከዚህ በኋላ ይህ`ያየኸው አባብ ዝከሩ ጠፍቷል፤ ምንም እንኳን ብዙ ሙስሊሞች በተለያየ አገሮች ቢኖሩም ግን ከዚህ በኋላ የሃይል ምንጫቸው ደርቋል፤ ከዚህ በኋላ የእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ተገዳዳሪ ሆነው እንዳይቆሙ መርዙ ተወግዷል፤ ብዙ በዚህ ስም የሚነግዱ ምግባቸው ተወስዷል። እነርሱንም የሃብት ምንጫቸውን አደርቃለሁና ደስታቸው ወደ ለቅሶ ይለወጣል፤ ልታይ፤ ልታይ እንዳላሉ ሁሉ ልደበቅ፣ ልደበቅ ደግሞ ይላሉ፤ በዚህም ሳቢያ ብዙ ሙስሊሞችን ወደ ራሴ እመልሳለሁ፤ ልባቸውን አቀናለሁ፤ ለሞት እንኳን የቆረጡ ለእኔ ለመኖር የጨከኑትን ህዝቤን ከዚህ ከሙስሊም ማህበረሰብ መሃከል እለነሳለሁ" አለኝ።

## በህንድ የተደረገ መንፈሳዊ ውጊያ

ከዚያም ተነስተን ወደ ህንድ በብርሃን ሉላችን እየተጓዝን በሙምባይ አየር መንገድ አጠገብ ደርሰን ስንመለከት 'አናም' የሚባሉ መናፍስቶች የህንድን ምድር ሞልተው ነበር፡፡ እነዚህ መናፍስቶች ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ከሰው ልጆች ጋራ ተጋብተው የወለዱ፤ የተዋለዱ ግማሽ መንፈስ ግማሽ ሰዎች የሆኑ ነበሩ፡፡ በተለምዶ ሬድ ኢንዲያንስ በመባል ቢታወቁም እነርሱ ግን ቀን ቀን ሰው ማታ ማታ የተለያየ አውሬ በመሆን ራሳቸውን የሚቀያይሩ እንዲሁም የራሳቸውን ልጆች ሳይቀር ለምግብነት የሚያውሉ እጅግ ጨካኝ መናፍስቶች ነበሩ፡፡

እነዚህ መናፍስት ውሃ ባለበት ቦታ እና እንዲሁም በደን ውስጥ የሚኖሩ ናቸው፡፡ በህንድ አገር ወደ ሙምባይ ከተማ ስንደርስ እነዚህ መናፍስት ከሰዎች ጋራ አብረው እየተዳሩ የተለያዩ አጋንንታዊ ትርኢት የሚያሳዩበትን ስፍራ ተመለከትን፤ ይህንን ሁሉ የሚያደርጉት በከተማዋ መሃከል ባለው ቤተመንግስት ውስጥ በሚገኘው 'ግሪን ጋርደን' ውስጥ ነበር፡፡ ከአውስትራሊያ፣ ከብራዚል እንዲሁም ከአሜሪካ ወዘተ በመንፈስ ሆነው ነበር በዚህ ስፍራ የተሰበሰቡት፡፡

ከአለም የተለያየ ስፍራ የመጡ ጠንቋዮችና አስማተኞች፣ ሰላቢዎችና ቡድሃዎች እንዲሁም የሂንዱይዝም የእምነት መሪዎችም በፌስቲቫሉ ላይ ነበሩ፡፡ አካባቢው በአጠቃላይ በሰይጣን እና በአርኩሳን መናፍስቶች ተሞልቶ ነበር፡፡ ገና ታዲያ ወደ ፌስቲቫሉ ስንቀርብ ሳለ ጌታ በብርሃን ሉሏ ተቀምጦ ከአግሩ በሚወጣ የእሳት ጨረር እነዚህን እርኩሳን መናፍስቶች ይወጋቸው እና ያቃጥላቸው ጀመር፡፡ ከእጁ ደግሞ የጸሃይ ጨረር አይነት ጠንካራ ጦር እየወጣ መናፍስቱን ሲወጋቸው ሲቃጠሉ እና እንደ ውሃ ሲተንኑ እንመለከት ነበር፡፡

በኋላም የእግዚአብሔር መላእክትም አካባቢውን በመውረር በመናፍስቱ እና በተሰብሳቢዎቹ ላይ በቁጣ ተነስተውባቸው ሲያጠፏቸው ተመለከትሁ፡፡ "እነዚህ

ደግሞ የእግዚአብሔርን ህዝብ በደከመ ሰአት እየመጡ የሚያጠቁ የምድያም መናፍስት ናቸው" አለኝና ጌታ ፈጽሞ በነጎድጓድ እና በሙብረቅ ከመላእክቱ ጋር ሰይጣን እና ሰራዊቱን በህንድ አየር ላይ ድል ነሳቸው፤ ከሃዲዎችንም በማስደንገጥ ምክራቸውን ለዘላለም አፈረሰባቸው።

በምድር ሁሉ ያሉ ጣኦት አምላኪዎችና ጠንቋዮች በሙሉ ሃይላቸው በዚህ በህንድ አየር ላይ ለዘላለም ሲቃጠሉ ተመለከትሁ። ሁሉም በአለም ያሉ ጠንቋዮች እና መተተኞች ከዚያች ደቂቃ በኋላ ሃይላቸው ተመትቶ ግማሹ በሞት ሲነሱ ሌሎቹም በንስሃ ሲመለሱ ተመለከትን። በህንድ አገር የሚሰራው ይህ ትብታብ ለዘላለም ተጠረገ። ሁሉም ሰፍራዎች ወደ ሙዚየምነት ሲቀየሩ ተመለከትሁኝ፤ ቀድሞ ለድግምት ይጠቀሙባቸው የነበሩት ቃላት ሳይቀሩ ፈጽሞ ሃይል አልባ ባዶዎች ሆኑ።

በአለም ዙሪያ እንዲህ ያለው የሰይጣን አሰራር ዘመን ያለፈበት ኋላቀር ተደርጎ በምድር ነዋሪዎች ሁሉ ሲቆጠር ተመለከትሁ። ሰዎች ላይ ወድቆ የነበረው የጣኦት አምልኮ ፍርሃት ከላያቸው ሲገፈፍ አይ ነበር። ከዚህም የሰይጣን ተንኮል ያመለጡ እጅግ ብዙ ሰዎች ወደየቤተክርስቲያኑ ሲሄዱና እጃቸውን እንስተው ለጌታ ሲሰጡ እመለከት ነበር። ወገኖቼ ጌታ በዚህ ስፍራ የተደረገውን ይህን ድል ያሳየኝ እርግጠኛ ነኝ ይህን ጦርነት እንድዘግብ ብቻ እንዳልሆነ። የእግዚአብሔር ህዝብ ይህን የተገለጠውን ድል አውቆ ምርኮን እንዲበዘብዝ እሰቦ እንደሆነ ይገባኛል። ስለዚህ ድሉን ተከትለን በክርስቶስ አለምን እንድንጠቀልል ሃሳቡ መሆኑን ገብቶኛል። እናም ክርስቲያን ሆይ በበቀል ተነሳ ምርኮን በዝብዝ ነው መልእከቱ። በማስከተልም አሁንም ተሳፍረንባት በነበረችው የብርሃን ሉል ከህንድ የተለያዩ አገሮችን አየር በማቋረጥ ከጌታ ጋር ወደ ናይጄሪያ ጉዞ ቀጠልን።

## በናይጄሪያ የተደረገ መንፈሳዊ ውጊያ

ከህንድ በቀጥታ ተሳፍረንባት በነበረችው የብረሃን ሉል ተጉዘን በቻድ ሃይቅ በኩል አድርገን ወደ ናይጄሪያ ስንገባ በአጠቃላይ በአፍሪካ አህጉር በሙሉ የሚሰሩ ነፍሰ ገዳይ መናፍስት በቻድ ሃይቅ አካባቢ በናይጄሪያና በካሜሩን ድንበር አጠገብ በምትገኝ 'ካምቦሩ' በምትባል አነስተኛ ከተማ ከኒጀር፣ ከካሜሩንና፣ ከቻድ እንዲሁም ከናይጀርያ የተሰበሰቡ ጠንቋዮችና እጅግ ብዙ ሺህ የሚሆኑ መናፍስት ጠሪዎች እና የእስልምና አክራሪ ጅሃዲስቶች ሰብሰባ ተቀምጠው ተመለከትን፡፡ ያኔም ወደ አጠገባቸው ስንጠጋ ወዲያው የብርሃን ሉላችን መምጣቷን እንዳወቁ የጌታ መላእክቶች መናፍስቶቹን እየለቃቀሙ ያቃጥሏቸው ያዙ፡፡ በጠንቋዮቹና በጅሃዲስቶቹ ላይም የእግዚአብሔር መቅሰፍት ይወርድባቸው ጀመር፡፡

ከጠንቋዮቹ እና ከጅሃዲስቶቹ መሃከል ከሱዳን፣ ከህንድ፣ ከቻይና፣ ከቬትናም፣ ከኩዋላላምፑር፣ የመጡም ነበሩበት፡፡ እንዲሁም ከተለያዩ የአፍሪካ አገራትም የመጡ ነበሩ፡፡ ብዙዎቹ በህንድ ከደረሰባቸው ሽንፈት ለማገገም እየተጣጣሩ ነበር፤ ነገር ግን አልቻሉም፤ ሁሉም ግራ ገባቸው፡፡ አካባቢው በእሳት ነሞራ እንደሚፈነዳ ተራራ ጭስ በጭስ አቧራ በአቧራ ሆኖ ሁሉም በሚባል ደረጃ ተደመሰሱ፡፡

በመቀጠልም ጌታ "ወደ ሌጎስ እንሄዳለን በዚያ ነው ዋና ካንፓቸው" ብሎኝ ጉዟችንን ወደ ሌጎስ አደረግን፡፡ በቅፅበት አይንም በሌጎስ ከተማ መሃከል በቲንባ ሰፈር በሚገኘው በሮዊ ፓርክ ስንደርስ እጅግ ብዙ መናፍስቶች ልክ እንደ ጉንዳን ከመሬት በመውጣት የተለያየ ትርኢት ሲያሳዩ ተመለከትን፡፡ በዚህ ሰፍራም ከአለም አገሮች በሙሉ ሃይላቸውን ለማደስ ጠንቋዮች፣ መተተኞች፣ ሟርተኞች፣ ሰላቢዎች፣ ነጋዴዎች፣ ምሁራኖች፣ ታዋቂ የአለማችን ዘፋኞች፣ እንዲሁም ሀሰተኛ ፓስተሮች ጭምር ተሰብስበው ሰይጣንን ያመልኩት ነበር፡፡

እነዚህ የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ መፅሃፍ ቅዱስን ገንጥለው በጥርሳቸው ይዘውት ነበር፡፡ እጅግ ለቁጥር የሚታክቱ መናፍስቶችም እስከ ጭፍሮቻቸው

ተራቸውን በመጠባበቅ ላይ በመድረኩ በስተግራ ተቀምጠው አየሁ፡፡ ከተቀመጡበትም በየተራ እየተነሱ የተለያዩ ዘፋኞች ዘፈናቸውን ያቀረቡ ነበር፡፡ ከእነዚህም መሀከል ኢትዮጵያ ውስጥ ታዋቂ የሆነ ዘፋኝ የቀስተ ዳመና ባንዲራ ይዞ ሰውን ሁሉ ሲያስጨፍር ተመለከትን፡፡ ከዚያም በብዙ እርኩሰት የተሞሉ ዜማዎችና ግጥሞች በየቋንቋቸው ተዕፈው በጠረቷ ንግስት ጠባቂዎች እማካኝነት ለእያንዳንዳቸው ይሰጣቸው ጀመር፡፡ ዘፈኑ ላይ ላዩን እንደ ሽፋን ስለ ተቃራኒ ጾታ የሚያወራ ሆኖ ነገር ግን ከከበሮው ጀምሮ ዜማው፣ ግጥሙ፣ ቅንብሩ በሙሉ እግዚአብሔርን የሚሰድብና እመፅ የተሞላ ነው፡፡

ሁሉም እዚያ የተገኙት በመንፈሳቸው ነበር፤ አንዳንዶች በዚያ ወቅት እልበማቸውን ያስመርቁ ነበር፡፡ ሮሊጅግ ብዙ የአገራችን ዘፋኞችንና ከውጪ ደግሞ የአለማችን እጅግ ኮከብ የሆኑ ዘፋኞች እንዲሁም ከሱዳን፣ ከህንድ፣ ከናይጀሪያ፣ ከማሊ፣ ከደቡብ አፍሪካ እና ከኤርትራ አገር ወዘተ ብቻ ከየቋንቋውና ከየብሔሩ ታዋቂ የሆኑ ዘፋኞች ነበሩበት፡፡ ከዘፋኞቹ በተጨማሪም ከአገራችን ጀምሮ በአለም ሁሉ ያሉ ሙዚቃ አቀናባሪዎች እና ፕሮዲውሰሮች እንዲሁም ዳንሰኞች እና የዘፈን ግጥም እና ዜማ ደራሲዎች ነበሩባቸው፡፡

እነዚህ ዘፋኞች በዚህ ወቅት በአካል በየአገሩ በተለያዩ ቦታዎች ወደ ሰይጣን ወኪሎች በመሄድ በገሃዱ አለም እንድም የሚሰሩት ሙዚቃ እየተጻፈ ነው፤ ወይ እያቀናበሩ ነው፤ ወይ ዜማ እየደረሱ ነው፤ ወይ ደግሞ ዘፈናቸው በህዝብ ተቀባይነት እንዲያገኝ እያስደገሙ ነበር፡፡ እያንዳንዳቸው ዘፋኞች በህሊናቸው ይህንን እጋንንታዊ መልእክት እንዴት እንደሚቀበሉ እመለከት ነበር፡፡ ግማሾቹ በጫት ደንዝዘው እንዲሁም በአሽሽ ጦዘው በመመሰጥ በህሊናቸው ከመናፍስቱ ነበር የሚቀበሉት፡፡ ነገር ግን ሁሉም በሚባል ደረጃ የጠረቷ ንግስት በምትሰጣቸው ሃይል ነበር ፈጠራውን እንኳን የሚያገኙት፤ አንዳንዶቹ በአካልም ጭምር ሳይቀር በምድር ባሉ በእጋንንት ወኪሎች አማካኝነት ግብር በመገበር በግልፅ የጥልቁ አባላት ሆነው ነበር፤ ሌሎቹ ግን አባላት ቢሆኑም በምስጢር ነበር የሚሳተፉት፡፡

አብዛኞቹም መንፈሳዊ አይኖቻቸው የተከፈቱ እና ከማንባራቸው ብርሃን የሚወጣ ነበሩ፡፡

በዚህች ቤተክርስቲያን ወንጌል በሙሉ ሃይሉ ይሰራ ነበር፡፡ በአለም ባሉ የመናፍስት ወኪሎች ከቤተክርስቲያኒቱ መሪ እሳት እየተወነጩፈ በየፕሮግራሞቹ ስራቸውን ያፈርስ ነበር፡፡ ጌታም ከቤተክርስቲያኑ መሪ ጎን ቆሞ ተመለከትሁኝ፤ ከእኔም አጠገብ እንዲሁ ተቀምጦ ነበር፡፡ ይህን ባህሪውን አስተድሜ ለምጀው ስለ ነበር ጌታዬን አከበርሁ፡፡ ከዚያም በብርሃን ሉላችን ውስጥ በመሆን ከናይጄሪያ ወደ ዩ. ኤስ. አሜሪካ መጓዛችንን ቀጠልን፡፡

# የኢሉሚናቲ መንፈስ

ኃይልህ ብዙ ሲሆን ጠላቶችህ በከንቱ ዋሹብህ እንደሚል ቃሉ በዚህ ዘመን ጠላት ሰዎችን ከሚዋሽበት መንገድ አንደኛውና የመጨረሻው ዘመን የክርስትና ተግዳሮት ሆኖ ሰይጣን አለምን ለመቆጣጠር እየተጠቀመበት ያለበት አዲስ አስትራቴጂ ሲሆን ጌታም እነዚህ የኢሉሚናቲ አባላትን ምስጢር ያሳየኝ ዘንድ ወደ አሜሪካ ኒው ዮርክ ከተማ ውስጥ ወደሚገኝ አንድ ትልቅ የሆቴል ህንፃ ወሰደኝ፡፡ በብርሃን ሉላችን በዚህ ሆቴል ግቢ ውስጥ በሚገኝ የዋና ስፍራ አጠገብ ካረፍን በኋላ እጄን በመያዝ ከብርሃኗ ሉል በመውጣት በህንፃው ውስጥ ወደሚገኝ አንድ ትልቅ አዳራሽ ወሰደኝ፡፡

በአዳራሹ ውስጥ ብዙ በምድራችን ላይ ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን ያካተተ እጅግ ምስጢራዊ የሆኑ የኢሉሚናቲ ከፍተኛ አባላት ከሰይጣን ጋር የህፃናት ልጆችን ደም በመጠጣት እና "ነፍሳችንን ለሰይጣን ሸጠናታል" እያሉ ቃል ኪዳን እየገቡ ባለ ሰድሰት የቃል ኪዳን አንቀጽ የተፃፈበትን መጽሃፍ በቀኝ እጃቸው በመያዝ ኪዳን ሲገቡና ሲቀመጡ እንመለከት ነበር፡፡ እነዚህ ከፍተኛ የምስጢር ማህበር አባላት ፊታቸው ላይ ምንም አይነት የደስታ ስሜት አይታይባቸውም ነበር፡፡ ሁሉም በደባል ስብእና ማንነታቸው አደገኛ በሆኑ መናፍስት ተፐለትልተው ነበር፡፡

በዚሁ ስብሰባቸው ከመቀመጫቻቸው ሁሉም በመነሳት እያመለኩተ ሰይጣን የሆነ ወረቀት ላይ የተፃፈን ልክ እንደ መዝሙር አይነት ነገር ይዘምሩ ነበር፤ ሆኖም ግን መልእክቱ የእግዚአብሔርን ታላቅነት የሚያንኳስስ እና በሰዎች ግለኝነት ላይ የሚያተኩር ይዘት ያለው ግጥም ነበረው፡፡ መዝሙሩም እንዲህ የሚል ነበር፡፡

*ሲይጣን ለምላሳችን አንተ ነህ*

*አንተ ብርሃን ነህ*

*ለእናም ለይዕምሮአችንን አበራህልን*

*አንተ ነህ ፍትሃዊ አምላክ*

*እግዚአብሔር አምላክ አይደለም*

*ጨካኞች ነን ለም ምህረትን አናውቅም*

*ምህረት የሚባል ነገር ስለማታውቅ ብዙ እውቀት ሰጠን*

እያሉ በአለማችን ቁጥር አንድ በሆኑ ዘፋኞች እየተመሩ ይዘምሩ ነበር፡፡ ከመዝሙሩ በኋላም ሁሉም በየስፍራቸው ተቀመጡ፡፡ ይሄ እምልኮተ ሰይጣን በስነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ 'እኛ የኢጋንንቶች የዘር ሃረግ አለን' የሚሉ ሁሉ ተነስተው የተለያዩ ያልተገቡ ተግባራትን በሰው ሁሉ ፊት ሴቶች ከሴቶች ጋር እንዲሁም ወንድ ከወንድ ጋር ወሲብ ማድረግን ተያያዙ፡፡

ቀጥሉም ለሁሉም እራሳቸው በሆስፒታላቸው በሚያስደርጉት ውርጃ እንዲሁም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የተፀነሱ ህፃናትን እስከነ ህይወታቸው ሰፋ ባለ ትሪ በእያንዳንዱ ሰው ፊት ከቀረበላቸው በኋላ ለእያንዳንዳቸው በተዘጋጀ የሰይጣን መስዋዕት ማቅረቢያ ምድጃ ገና አይኖቻቸውን ያልገለጡ እና በደም የተጨማለቁ ህፃናትን አንገታቸው ስር ያለውን የደም ስር በጥርሳቸው ቆርጠው ደማቸውን ሲጠጡ ከቆዩ በኋላ አዳራሹ በህፃናት ዋይታ ተሞላ፤ ነገር ግን ህፃናቱ በመጨረሻ ድምፃቸው እየደከመ በመሄድ በእነዚህ የጥልቁ አባላት ሳቅና ጫጫታ ተሞላ፡፡ ከየሁሉም የተለያየ እንስሳ አይነት ድምጽ ይወጣ ነበር፡፡

ኋላም ከገፈራቸው በሰው ደም ርሶ ወደ መስዋዕት ስፍራ በመሄድ በሲሊንደር አሮስቶ መጥበሻ ላይ የህፃናቱን ስጋ በማገላበጥ እንደ ካምፕ ፋየር ምድጃ በዳንብ

ካበሰሉ በኋላ ሁሉም ሲጋውን በእጃቸው በመያዝ ለሰይጣን አምልኮ አድርገው ሁሉም ወደ መቀመጫው ሲመለስ አስተናጋጆቹ የህፃናቱን ስጋ በመቆራረጥ ቢታዋቂ ሼፎች ለምግብነት እንዲዘጋጅ ተደርጎ ለእያንዳንዱ ሰው እንዲቀርብለት ተደረገ። እነዚህ የጥልቁ ማህበር አባላት ሁሉም ቅርጥፍ አድርገው የህፃናቱን ስጋ ከበሉ በኋላ ተጣጥበው በየወንበራቸው ተቀምጠው ይታዩ ነበር።

ወገኖቼ እነዚህ የጥልቁ ማህበርተኛ ኢሉሚናቲ አባላት በምድራችን ላይ እጅግ ታዋቂ የሆኑ ቢሊየነሮች ናቸው። በአገራችን እሉ የተባሉ ባለሃብቶችን ጨምሮ በዓለም ዙሪያ ያሉ ታዋቂ ሰዎች፣ ዘፋኞች፣ እንዲሁም ታዋቂ የእግር ኳስ ኮከቦች፣ የአገራችን እንዲሁም የአለማችን ቁጥር አንድ ኮኮብ አትሌቶች፣ እንዲሁም የምድራችን ቁጥር አንድ የሆሊውድ ኮከቦች፣ ዳይሬክተሮች፣ ከታላላቅ የአገር መሪዎች መካከል እጅግ ብዙ ነበሩበት። እንዲሁም የሞሳድ እና የሲአይኤ ከፍተኛ ባለስልጣኖች፣ ታዋቂ የናሳ እና የተለያዩ አገሮች የጠፈር ተማራማሪዎች፣ የዩኒቨርሲቲ ታዋቂ ፕሮፌሰሮች፣ አንዳንድ ታላላቅ የሃይማኖት መሪዎችን ጭምር ያካተተ ነበር።

ቀጥሎም ሰይጣን በአካል በመገለጥ እጅግ የሚያምር እና በሱፍ ሽክ ያለ ጎልማሳ መስሎ ሲገባ ሁሉም በመሬት በመውደቅ እጅ ነሱት፤ ከዚያም በተዘጋጀለት ዙፋን ላይ እንዲቀመጥ ሆነ። ከሰው ጋር የተዳቀሉ ነጫጭ ሰዎች የሚመስሉ ልክ እንደ በረራ አስተናጋጅ አለባበስ አይነት የለበሱ ሞዴል ሴቶች በዙሪያው ቆመው ነበር። ሰይጣንም በዝርዝር ሲወያዩበት የሚገባውን ማኒፌስቶ ለእያንዳንዱ ሰው በኮፒ በአስተናጋጆቹ አማካኝነት እንዲሰጣቸው አደረገ። በኋላም እራሱን የሰው ልጆች አሳቢ አድርጎ የተለያዩ ከአዳም ጀምሮ የሰራቸውን መልካም ነገሮች ናቸው ያላቸውን በሙሉ መጽሃፍ ቅዱስን በመተቸትና የእግዚአብሔርን ጨካኝነት እያጣቀሰ ከታሪክ፣ ከመጽሀፍ ቅዱስ ወዘተ ያብራራ ጀመር።

ራሱንም የዚህች አለም መፍትሄ በማድረግ ያቀርብ ነበር። እንዲህም አለ "አሁን እዚህ የተሰባሰባችሁት እስኪ እስረዱኝ ማነው ብርሃን፣ እኛ ከሰው ልጆች ጋር ከቃየን ጀምሮ በመዳቀል በእነ ናብሮድም ዘመን በመዋሲድ እንዲሁም በኖህ

ናቸው የትኛውንም የስልጣን ተዋረድ መያዝ ያለባቸው፡፡ ማንኛውም የዚህ ምስጢራዊ ቡድን አባል የስጋ ዘመዱም ቢሆን የአባላቱን ምስጢር አደጋ ላይ ሊጥል ከቻለ ማስወገድ አለበት፤ አለበለዚያ ግን እራሱ ይወገዳል፤ ሃይማኖት የኋላ ቀርነት እግር ብረት ነው ብሎ ህዝቡን ማስተማር፤ የተለያዩ በሽታዎችን በላብራቶሪ በመፍጠር የሰው ልጆችን ቁጥር በተላላፊ በሽታዎችና መድሃኒት በሌላቸው አደገኛ ቫይረሶች በብዛት ያልተማረና ድሃ የሆነውን ህብረተሰብ መጨረስ፤ ከምድር ማስወገድ፡፡

የምድር ነዋሪዎችን ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ፤ ጦርነቶችን በማስነሳት እንዲሁም በመርዘኛ ጋዞች መጨረስ እና ማጨራረስ፤ ርህራሔ አለማድረግ፤ በተለይም ደሃ የሆኑ እና የማያስፈልጉ የሰው ዘሮችን ከምድር ላይ በበሽታ፤ በጅምላ ጨራሽ መሳሪያ፤ በመርዝ እና በተለያዩ መንገዶች ማስወገድ፤ እጅግ ጠንካራ የሆነ የጋራ የመከላከያ ሃይል ማቋቋም፤ የፖለቲካ ስልጣን በቁጥጥር ስር በማዋል አለምን አንድ አድርጎ መምራት፤ ትውልዱን እግዚአብሔርንና መሲሁን ማስካድ፤ መሲሁ እንደሚወለድ ሁሉም የዚህ ምስጢራዊ አባላት በሙሉ ይሄንን እዲጠብቁ ማድረግ፡፡

በአባላቱ ላይ ማንኛውንም እፍራሽ ተልእኮ አለመታገስ፤ በጭካኔ ማጥፋት፤ የተለያዩ የጅምላ ጭፍጨፋዎችን የሚያደርጉትን እውቅና መስጠት፤ እልፎም ማቀናበር፤ ሰዎች እራሳቸውን የሚወዱ ስለ ሌላው የማይጨነቁ እንዲሆኑ ማድረግ፤ ግለኞች ማድረግ፤ ገንዘብን የሚያመልኩ ማድረግ፤ ማንኛውም አባል ገንዘቡን ለእርዳታ ማዋል የለበትም፤ ድሆችን ከመርዳት ይልቅ ማጥፋት፤ የእግዚአብሄር ጥገኞች ስለሆኑ መጥረግ፡፡ ከጠላት ጋር ፍፁም ተነጋግሮ ችግርን መፍታት አይገባም ማስወገድ ብቻ፤ ከዚያም ሌላ አማራጭ ፕላኔትን ለመኖሪያነት ማዘጋጀት፤ ለሰው ልጆች ዲሞክራሲ፤ እኩልነት የሚባሉ ሃሳቦችን ማጥፋት ማስወገድ፤ በዚሁ አለምን ወደ አንድ መንደር፤ አንድ ገዢ፤ አንድ አምላክ፤ በእኔ፤ ለእኔ ክብር መስጠት" ሲል ሁሉም "ሰይጣን ገዢአችን ነህ፤ አምላካችን አንተ ነህ"፡ በማለት ጉባኤው በጭብጨባ ተደበላለቀ፡፡

ዲስኩሩን ሲያበቃ ሁሉም "ነፃ አስተሳሰብ ለተሻለ ህይወት" በማለት ተነሰተው ደስ ያላቸውን ያደርጉ፣ ይፈነጥዙ ጀመር:: ሰይጣንም ንግግሩን በመቀጠል "የሰሻል ሚዲያዎችንና የሆሊውድ ፊልሞችን በተለይም ሳይንሳዊ ፊልሞችን ተመልከቱ፤ በመንፈሴ እገለጥላችኋለሁ:: እንዲሁም ዘፈኖችንና ዘፋኞችን ተከታተሉ፤ መልእክቶቻችን ይተላለፋሉ" በማለት በመጣበት አኳኋን ሳይሆን ልክ መብራት ሲጠፋ እንደሚሆነው ከፊታቸው በድንገት ጠፋ::

በኋላም መናፍስቱ ግማሹ ሴት ሞዴሎች ሲሆኑ ደግሞ ወንድ ሞዴሎች ሆነው እጅግ ተብለጭልጨው ይታዩ ነበር፤ ሁሉም ግን ጭራ ነበራቸው፤ ሲስቁም የውሻ ከራንቻቸው ብቻውን ሾል ሆኖ ልክ ቫምፓየሮችን ይመስሉ ነበር:: ከዚያም ሰዉ ሁሉ እንደ ምርጫቸው በአርከሰት፣ በዝሙት፣ በግብረ-ሰዶም፣ በጭኸትና በአጋንንታዊ ትርኢት ተሞልተው በአለም ታዋቂ በሆኑ አርቲስቶች ሙዚቃ ይጨፍሩ ጀመር:: ውድ የሆኑ ውስኪዎች በሰው ደም ተበርዘው ለየታዳሚዎቹ በአስተናጋጆቹ ይቀርብላቸው ነበር:: ብቻ ድል ያለ ፓርቲ ሆነ፤ እጅግ ጫጫታም ሆነ:: ከውጪም ከትምህርት ቤት ከተለያዩ የህፃናት ማሳደጊያ የተወሰዱ የ13 ዓመት እና ከዚያ በታች እስከ ሰባት አመት የሆኑ ሴቶችና ወንዶች ልጆች ታጅበው ወደ አዳራሹ ከገቡ በኋላ በመድረኩ ላይ አቁመዋቸው በግልጽ ከመድረኩ ላይ "ከታዳሚው በፍቃደኝነት እዚህ መጥቶ እነዚህ ህፃናትን የሚደፍር ማነው?" በማለት ሲጠይቁ የእጅ ምልክት ያሳዩ ሰዎች እየወጡ አንዱን ልጅ ለአምስት ለስድስት ሲደፍሩት አመለከት ነበር፤ እንዲሁም አንዷን ህፃን ሴት ለአስር እየከበቡ ልክ እንደ አሻንጉሊት ሁለንተናዋን ሲደፍሯት አመለከት ነበር::

የህፃናቱ ጩኸት አዳራሹን ቢሞላውም እየቀረበ በነበረው የሙዚቃ ትርኢት ድምፃቸው ተዋጠ:: ከዚያም መናፍስቱ የህፃናቱን ደም እየመጠጡ ረጃጅም በሆነው ጥፍራቸው ሰውነታቸውን እንደ ቲማቲም በመቀዳደድ ልባቸውን አውጥተው እንደ አይስክሬም ይመጥጡት ጀመር:: ይህን የሚያደርጉት እነዚያ ቀድመው ከህዝቡ ጋር የተደባለቁ ሞዴል መሳይ ቫንፓየሮች ነበሩ፤ ልቡንም

እንቅስቃሴዎችን መቆጣጠር ይገባቸዋል፤ እያንዳንዱን ቤጋ የመጠበቅ ሃላፊነት አለባቸው፡፡ ሳይቀድሟቸው የሰው ልጆችን ከጥፋት መታደግ ያለባቸው ሰዓት አሁን ነው" አለኝ፡፡

ጌታም ንግግሩን ቀጥሎ "የእነዚህ ኢሉሚናቲዎች ሁለተኛ ደረጃ አባላቶቻቸው ወደ ሰላሳ ሚሊዮን እየተጠጉ ነው፤ ከመጀመሪያዎቹ አባላቶቹ ውጪ ሰይጣን ለብዙዎቹ ይሁን ምስጢር እንዲያውቁት አያደርግም፤ ነገር ግን 'ሃይማኖት ማለት ፖለቲከኞች ሰዎችን ለመቆጣጠር የተጠቀሙበት መሳሪያ ነው' ብሎ ይምግትና በተለይም ክርስቲያኖችን ከምድር ለማጥፋት ካለው ከፉ ሃሳብ በመነሣ ፈርጀ ብዙና እጅግ ውስብስብ ቅድመ ሁኔታዎችን እያስቀመጠ የሰው ልጆችን ወደማያባራ ጥፋት ይነዳቸዋል፡፡

ሰይጣን በዚህ በመጨረሻው ዘመን ትንሽ ቀን እንደቀረው አውቆ የውጊያ እስትራቴጂውን እዚህ ደረጃ አድርሶታል። የሰይጣን ማህበር አባላት መለያቸው ይሄ ነው፤ ርህራሔ አልባ ናቸው፤ የእንስሳትን ስጋ አይበሉም፤ የቱንም ያህል ንብረት ቢኖራቸው ድሆችን አይረዱም፤ የሰው ሃይማኖት ስራ ነው በማለት በተለይም ክርስትናን ይቃወማሉ፤ ይትርታ አድራጊዎች አይደሉም፤ እራሳቸውን እጅግ ይወድዳሉ፤ ሃይማኖት በተለይም ክርስትና የከፋት ምንጭ ነው ብለው ይሰብካሉ፤ ስለ እግዚአብሔር ከፉ በማድረግ ያስተምራሉ፤ ሃሳባቸውን ለማስፈፀም ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰድ አይመለሱም፤ በግልጽ እንደሚያስተምሩት እውነትን ቢያውቁም አይከተሏትም፤ አውቀው ለዚህ ምድርና ለሰይጣን ሃሳብ እራሳቸውን ሸጠዋል በዚህ ታውቋቸዋላችሁ፡፡

እንግዲህ በመጨረሻው ዘመን የሚያስጨንቁ ቀናት እንደሚመጡ ሁሉም የእኔ ተከታይ ይወቅ፡፡ ሰዎች እራሳቸውን የሚወድዱ ይሆናሉ፤ ገንዘብን የሚወድዱ፤ ትምክህተኞችና ትዕቢተኞች፤ ተሳዳቢዎች፤ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፤ የማያመሰግኑ፤ ቅድስና የሌላቸው፤ ፍቅር የሌላቸው፤ እርቅን የማይወዱ፤ ሃሜተኞች፤ ራሳቸውን የማይገዙ፤ ጨካኞች ናቸው፡፡ መልካም የሆነውን ሁሉ የማይወዱ፤ ከዳተኞች፤ ችኩሎች፤ በትዕቢት የተነፉ፤ ከእግዚአብሔር ይልቅ

ተድላን የሚወድዱ፣ ሃይሌን የካዱ፣ ሁልጊዜ እየተማሩ ወደ እውነት የማይመጡ ሰዎችን በሚያባብል ቃላት እያታለሉ ብዙዎችን ወደ ሞት ይነዳሉና ስለዚህ ከሩታቸው መገለጡ አይቀርም፡፡ ከፊት ይልቅ አሁን እይተናላቸውም፤ ሁሉም እንደ ገለባ ተጠርገው ይጠፋሉ፤ እናንተ ግን ከከንቱ እና ህይወት ከማይገኝበት ልፍለፋ እና ትምህርት ራቁ፡፡

አባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳተ ሁሉ ዛሬም ሰይጣን ብዙዎችን ለማሳት በተቀናጀ መንገድ እየሰራ በመሆኑ ሁሉም ሰው ነቅቶ ምሽጉን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ የሚቀጠቅጥ በፊቱ እንደወጣ አውቆ በህያዋንና በሙታን ላይ በሚፈርደው ፊት ቃሌን ብቻ ህዝቤ በእምነት እንዲሰብከና በጊዜውም ያለጊዜውም በመጽናት በትእግስት ከቃሌ በመማር እንደቃሌም በመገለጽ እንዲኖሩ አስተምር፡፡ የእውነት ቃልን ሰዎች የማይታገሱበት ዘመን መጥቷልና እንደራሳቸው ምኞት የሆነውን፣ ስሚታቸውን ደስ የሚያሰኘውን፣ እንደ አሮጊቶች ተረት የማያስቀውን፣ እንደ መዝናኛ የሚሰብኩትን ከመቀበል ህዝቤ ልበን እንዲጠብቅ ንገራቸው" አለኝ፡፡

በኋላም እንደዚያ በደመቀው የአጋንንቶችና የኢሉሚናቲዎች ማህበር ፓርቲ ውስጥ ሰይጣን የሚሰራቸውን የተለያዩ አጋንንታዊ ጥበቦችን በመግለጽ የተለያዩ ሳይንቲስቶችን ያስተዋውቅ ጀመር፡፡ በመድረኩ ላይ ያሉ ሰዎች ይቀያየራሉ እንጂ ያው ሰይጣን ነበር በውስጣቸው የሚያወራው፡፡ ከዚያም ጌታ በብርሃን ሉላችን ወደ አሜሪካ ኦሃዮ አስቴት ወሰደኝ፣ በዚያም ሰፍራ በጄኔቲክስ እናት አባታቸውን የማያውቁ በህፃንነታቸው በጭንቅላታቸው ውስጥ ከኮምፒውተር ጋር የመረጃ ልውውጥ የሚያደርጉበት መስመር ያላቸው 500 ህፃናት ልዩ በሆነ ምስጢር የሚጠበቁ በሶስት አጥር ተከብበው በተለያዩ አለማዊ ጥበብና እውቀት እየሰለጠኑ ያሉትን ወንዶችና ሴቶች ህፃናት ተመለከትሁ፣ እነዚህ ልጆች ከህፃንነታቸው ጀምሮ ፈጽሞ ስለ ሐይማኖት እንዳያውቁ ተደርገው ነበር ያደጉት፡፡

እነዚህ ህፃናት ስለ ቤተሰብ እና ስለ ሀብረተሰብ ምንም ርህራሄ የማያውቁ ሲሆን አካላቸው የህፃናት ሆኖ ነገር ግን ግንባራቸው እጅግ ተቆጣጥሮ ልክ የትልቅ ሰው ፊት ይመስል ነበር፡፡ ከህፃንነታቸው ጀምሮም እርስ በእርስ ልክ እንደ መብላት እና መጠጣት በየቀኑ ወሲብ እየፈፀሙ ነበር የሚያድጉት፡፡ እነዚህ ህፃናት ማገንኛውም የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በተለያዩ ካሜራዎች ይቀረፅ ነበር፡፡ እንዲሁም ጭንቅላታቸው ውስጥ በተቀበረው የኮምፒውተር ቺፕስ አማካኝነት ጠቅላላ ሁኔታቸው በተሰጣቸው የሰው ቁጥር ዶክመንት ይሆን ነበር፡፡ በዚህ እድሜያቸው እንኳን ወደ ጥልቁ እየተወሰዱ አዕምሯቸውን በሃይል የመሙላት ስራ ይከናወንላቸው ነበር፡፡

በተመሳሳይ በኖርዌይም በምስጢራዊ የኢሉሚናቲ ማህበር አባላት ይሄ ተግባር እየተካሄደ ተመለከትን፤ ይህ ተግባር አውስትራሊያን ጨምሮ በሌሎች ያደጉ አገራትም ይከናወን ነበር፡፡ ታዲያ እነዚህ ልጆች አድገው የተገለጡ እለት የተለያዩ የመንግስት ስልጣንን እንዲይዙ ከመደረጋቸውም ባሻገር ታላላቅ ነጋዴዎች እና ባለሃብቶች እንዲሆኑ ተደርገው ነበር፡፡ ሰይጣንም በብዙ ጥንቃቄ ከሰው ልጆች ጋር አብሮ የሰውን ልብ እሳያሞኝ ነበር፡፡ ስለዚህ ወገኖቼ እነዚህ አደገኛ ሰዎች ምድራችንን በኢሉሚናቲ አስተሳሰብ የሚሞሉ፤ በፍፁም ከሀደት የተሞሉ፣ ታሪከን የማያውቁ፤ ማንንም የማይወዱ፤ ርህራሄ አልባ፤ ጅምላ ጨራሽ፤ የሆኑ ነበሩ፡፡ ያቺ እንሄድባት የነበረችው የብርሃን ሉል ሃይለኛ ጩረር በማመንጨት እንዲህ አለች "አዘዘኝ ጌታ ሆይ ላጥፋቸው" በማለት ተነሳች፤ ጌታ ግን ፈጽሞ አልፈቀደላትም ነበር፡፡ የጌታ ርህራሔ ከሁሉን ቻይነቱ የመነጨ እንደሆነ ወዲያው ሳይናገረን ተረዳን፡፡

ከዚያም በአሜሪካ ኦሃዮ እስቴት ውስጥ ባለ እስር ሰይጣናዊ የኪዳን ህግ ያስቀረፁበትን አንድ ሃውልት በአንድ ስፍራ ላይ ቆሞ ተመለከትሁ፤ እሳዩ ላይም ህዝብን የሚያስት መንፈስ ሲቀመጥበት አየሁ፡፡ በመቀጠልም በዚያው አሜሪካ ወደምትገኘው ኖርዝ ካሎራይና ተጓዝን፡፡ ከዚያም ወደ አንድ ሌላ ምስጢራዊ እና በልዩ ጥበቃ ወደሚጠበቅ ደን ውስጥ ወደሚገኝ አንድ ላብራቶሪ ውስጥ ገባን

በዚህ ላብራቶሪ ውስጥ ስምንት ሳይንቲስቶች የተለያዩ የመከላከያ ልብሶችን ለብሰው እጅግ አደገኛ የሆኑ ቫይረሶችን እርስ በእርስ እያዳቀሱ በመቀመር ስራ ላይ ተጠምደዋል፡፡ እነዚህ ተመራማሪዎች ከእነርሱ በእስር እጥፍ በሚበዙ እርከሳን መናፍስቶች ተሞልተው ነበር ይህንን ተግባር የሚፈጽሙት፡፡

እየተመለከትንም ሳለን አንድ አደገኛ ቫይረስ በድንገት አምልጦ በአንደኛው ሳይንቲስት ልብስ ውስጥ ገብቶ ኖሮ ሳይንቲስቱ ወዲያውኑ ተንዘለፍልፎ ወደቀ፡፡ ይህ ሰው ፕሮፌሰር እንደሆነ ጌታ ነገረኝ፡፡ ሁለት ሴት ልጆች ነበሩት፡፡ የተማረው በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ነው፤ በውስጥ ደዌ ነው ዶክትሬቱን የሰራው፡፡ እጅግ ምጡቅ አዕምሮ የነበረው ሰው ነበር፡፡ በአባቱ የእስፓኝ ዝርያ ያለው ሲሆን እናቱ ግን ከወደ እንግሊዝ የመጣች ነበረች፡፡ ይህ ፕሮፌሰር በቤተክርስቲያን ውስጥ ከሰንደይ ስኩል ጀምሮ ጌታን በማገልገል ነበር ያደገው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እየተማረ በነበረበት ወቅት በተማሪዎች ፌሎውሺፕ ውስጥ ያገለግል ነበር፡፡

ተምሮ ታላቅ ሰው ሆኖ ቤተሰቡን ለመርዳት ከነበረው ታላቅ ህልም የተነሳ ወደ ዩኒቨርሲቲ በከፍተኛ ውጤት ከገባ በኋላ ከትምህርቱ ጎን ለጎን የፍልስፍና መጽሐፍትን ማንበብና መፈላሰፍ ጀመረ፡፡ የህክምና ትምህርት ውጤቱ ላይ ተጽዕኖ እስከሚያሳድር ድረስም እነዚህን የፍልስፍና መጽሐፍት ማንበቡን አጠናክሮ ቀጠለ፡፡ በመጨረሻም እንደ ምንም ተጣጥሮ ዶክትሬቱን ቢይዝም በውስጡ የተፈጠረውን የፍልስፍና ትምህርት ፍቅር ለመወጣት እንደገና ወደ ቨርጂኒያ በመሄድ በፍልስፍና ድግሪውን ያዘ፤ በዚሁ ዘርፍ ማስተርስ ድግሪውን መማር ቀጥሎ በዚያው ዩኒቨርሲቲ ሌክቸረር ሆኖ ተቀጠረ፡፡ ማስተርስ ድግሪውን በሚሰራበት ወቅት ነበር ከልጆቹ እናት ጋር የተገናኘው፡፡

ይህች ወጣት እጅግ ቆንጆ ስትሆን ከእስራኤል ይሁዲ ከሚመዘዙ ቤተሰቦች የተገኘች ነበረች፡፡ ነገር ግን እርሷም የተወለደችው በዚያው በአሜሪካ ነው፤ እንዲያውም አንድ ጊዜ ብቻ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆና ወደ ዋሽንግተን እንቷ

ጋር ከመሄዱ ባሻገር ምንም አይነት ሌላ አገርን አታውቅም ነበር፡፡ በተማረችበት ኬሚስትሪ ያን ያህል ጠንካራ ባትሆንም እንኳን ፖለቲካ እጅግ ይስባት ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ የተለያዩ የክልል መንግስት (እስቴት ጋቨርመንት) ስብሰባዎች ሲኖሩ ሳትጠራ እየሄደች በተመስጦ ታዳምጥ ነበር፡፡ ይህንን ዝንባሌዋን በትምህርት ለመደገፍ ሁለተኛ ድግሪዋን ለመማር ወደ ቨርጂንያ ዩኒቨርሲቲ በገባችበት ሰዓት ነበር ከፕሮፌሰሩ ጋር ተገናኝተው በመጋባት ሁለት ልጆች ለማፍራት የቻሉት፡፡ ነገር ግን ሶስት አመት አብረው ከኖሩ በኋላ የመጀመሪያ ልጃቸው የሁለት ዓመት ልጅ እንደሆን እና ሁለተኛዋ ልጃቸው እንደተወለደች ባለመስማማት ለመለያየት በቁ፡፡ በዚህም ሰዓት ፕሮፌሰሩ ተስፋ በመቁረጥ ስራውን ለቅቆ ወደ ዋሽንግተን በመሄድ የኬሚስትሪ ትምህርት መከታተል ይጀምራል፡፡

ይህ የሚማረው የኬሚስትሪ ትምህርት በውስጡ ከተሞላው ፍልስፍና እና ከሀኪምና ዶክትሬቱ ጋር ተረዳድተው እጅግ ከፍተኛ የሆነ ውጤት በማስመዝገብ በዚያው በዋሽንግተን በኬሚስትሪ ዶክትሬቱን አጠናቀቀ፡፡ ለመመረቂያው በሰራው የጄኔቲክስ ቴክኖሎጂ ምርምር ልዩ ክብርን አግኝቶ በአጭር ጊዜ በአሜሪካ ታዋቂ የሆነ ፕሮፌሰር ለመሆን ቢታ፤ ነገር ግን በልጅነቱ ያመልከው የነበረውን አምላክ ፈጽሞ ከመካዱም በላይ እንዲያውም ሃይማኖት ፈጠራ ነው ወደሚል ፍልስፍና ውስጥ ጠልቆ በገባበት ጊዜ ነበር ከኢሉሚናቲ አባላት የግብዣ ካርድ የተሰጠው፡፡ በኮንፈረንሳቸውም ነገሮችን ሲመለከት እጅግ ደስ አለው፡፡ ወዲያውም አባል በመሆን እንዲያውም ይሄ የኢሉሚናቲ የበሽታዎች አምጪ ተዋህሲያን ቫይረሶችን መፍጠሪያና ማራቢያ የሳይንስ ማዕከል እንዲቋቋም ሃሳብን ከማቅረብ ጀምሮ ዋንኛ ተዋናይና ዳይሬክተር በመሆን እስከዚህች ቀን ድረስ እራሱን ሰጥቶ ሰዎችን በአንድ ጀንበር ሊጠርጉ የሚችሉ ገዳይ ቫይረሶችን ለመስራት ሲተጋ ቆይቷል፡፡

ይህ ሰው በስሩ ብዙ ፕሮፌሰሮችን ይዞ በከፍተኛ ደረጃ ይህን ተንኮል ሲያቀነባበር እና ሲያስተባብር ነው የኖረው፡፡ በኑሮው እጅግ የብዙ ሚሊዮኖች ባለቤት ቢሆንም ነገር ግን እናትና አባቱ እርሱን ለማየት እንደናፈቁ ሳያያቸው

ጥይት ከኋላው ሞንቅላቱን ሲመታው ኮሪደሩ ላይ ደሙ ቡልቅ ብሎ በመረጨት በማንባሩ ወደ በሩ ተደፋ።

ወዲያውም ከኋላ የነበሩ ወታደሮች መሳሪያቸውን ዘቅዝቀው ወደ ውጪ እየነተቱ ሁለት እግሩን ይዘው ካወጡት በኋላ እርሱንም በሌላኛው ጉድጓድ ጣሉት፤ በላዩ ላይም አፈር ሞሉበት። የሳይንቲስቶቹን መውጫ በር በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ከውስጥ ካሉት ጋር እየተገናኙ እየጠበቋቸው ነበር። በወቅቱ ሰውየው እንደወደቀ ተደናግጠው እርሱን ይዘው ሲወጡ የየራሳቸውን ስራ ዘንግተውት ስለነበር ተመልሰው ሲገቡ ሁሉ ነገር በቫይረሶች ተጥለቅልቆ ነበር። ይህን ግልጽ በሆነ መስታወት ከውጪ ይመለከቱ የነበሩ ወታደሮች በሮቹን እና መስኮቶቹን በሙሉ ምንም አየር እንዳያስገቡና እንዳያስወጡ አድርገው ቆለፏቸው።

ይሄኔ ሳይንቲስቶቹ በሙሉ አየር አጥሯቸው ወደ መስታወቱ መጥተው ቢለማመጡም ግን ሰሚ አላገኙም ነበር። እያዩአቸው ተዝለፍልፈው መውደቅ ሲጀምሩ በጄኔራሎች ትዕዛዝ ወታደሮቹ በዙሪያው ቤቱን በፈንጂ እያጠሩት ነበር። አጥምደው ሲጨርሱም እነርሱ ወደ ሄሊኮፕተራቸው በመመለስ በቀጥታ ሄሊኮፕተሯ እንደተነሳች ጄኔራሉ በእጁ ላይ ፈንጂውን የሚያነዘበትን ቁዩን ሴንሰር ሲጫኑው በታላቅ ፍንዳታ አካባቢው ተናወጠ።

በመቀጠልም ጥቁር የሆነ ጭስ በቦታው እየተግተለተለ ወደ ደመናው ወጣ። ከዚያም በውጪ የነበሩትን ጠባቂዎች እንዲሁም ዕዳቶች በሙሉ በሄሊኮፕተሩ እየተመላለሱ በመትረይስ ጥይት ደብድበው ከገደሏቸው በኋላ በተጨማሪም ተወንጫፊ ሮኬት በህንፃው እና በግቢው ላይ በመጣል ፈፅመው ድምጥማጡን አጥፍተው ተመለሱ። ከዚያም በመገናኛ መረባቸው ሁሉን እንዳስወገዱ ሪፖርት ካቀረቡ በኋላ ሄሊኮፕተሯ እየበረረች በተራራው መሃከል ስታልፍ ለካስ የኢሉሚናቲ አባላቱ በሌላ ሄሊኮፕተር ውስጥ ሆነው እየጠበቋቸው ነበር፤ ወዲያውም ብቅ ከማለታቸው በላያቸው ተወንጫፊ ሚሳኤል በመተኮስ በአየር

ላይ ጄኔራሎቹን እንዲሁም ወታደሮቹን ደመሰሷቸው:: ወዲያውም ወደ ኒው ዮርክ በፍጥነት በመብረር ተመልሰው ሲሄዱ ይታይ ነበር::

እነዚህ ርህራሄ የሌላቸው የኢሉሚናቲ የምስጢር አባላትን ስራ አስቀድሞ ፔንታጎን ደርሶበት ኖሮ እየተከታተላቸው ሳለ በአጋጣሚ በተከሰተው አደጋ ምክንያት ስልካቸውን ጠልፈው ሰለ ነበር ወታደሮቹ ላብራቶሪዎቹን ቢያጠፏቸውም ነገር ግን እነዚህ የምስጢር አባላት አስቀድመው ተሰርተው ያለቁ አደገኛ ገዳይ የሆኑ ቫይረሶችን አሽሽተው በሄሊኮፕተር ጄኔራሎቹን እስከሚያልፉ ጠብቀው አጋይተዋቸው ቫይረሱን በካዝናቸው ይዘው ነበር የተመለሱት::

እነዚህ የኢሉሚናቲ የምስጢራዊ አባላት ሁሌጊዜ እርስ በእርሳቸው ይሰላለሉ ነበር፤ ልክ እንደ አሊቃይዳ ሴሎች አሏቸው:: ዋንኛዎቹ መሪዎችን ማግኘት የሚቻልበት መንገድ እጅግ ጠባብ ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ በዘረጉት መረብ የተለያዩ የምስጢር ደረጃዎች ስላሉ ነው:: ሰይጣናዊ ሃሳባቸውን ቀስ በቀስ ለሰው ነፃነት በሚመስል መንገድ እንዲሁም በጭፍን እግዚአብሔርን በመተቸት ይጀምሩና በመጨረሻ ግን ሰይጣንን እስከማስመለክ ይደርሳሉ:: እስኪ ተመልከቱ የሰው ልጅ ሁሉ እንከን አልባ አይደለም፤ ሁሉ ሰው ተሳስቶ ነው ከስህተቱ ተምሮ የሚኖረው:: እነዚህ የምስጢር አባላት ግን ሰው መሳሳት የለበትም ከተሳሳተ መወገድ አለበት ነው አስተምህሮታቸው፤ እንዲያማ ከሆነ ሁላችንም በእነርሱ ሂሳብ በጠፋን ነበር::

እኔ እንኳን እግዚአብሔር የምህረት አምላክ ባይሆንና ብዙ ወገኖቼ ምህረት ባያደርጉልኝ ኖሮ እርግጠኛ ነኝ ዛሬን አላይም ነበር፤ ለምን ቢባል ህይወቴ ከህፃንነት ጀምሮ በብዙ ስህተቶች የታጀበ ስለነበር፤ እንደ እነርሱ ቢሆን ኖሮ ድሮ ገና ሞቼ ታሪኬም ተዘንግቶ ነበር:: ነገር ግን አምላኬ ባለ ብዙ ምህረት ስለሆነ ምህረቱ በህይወቴ ዘመን እየተከታተለኝ ለዚህ አደረሰኝ:: ይሄ ነው በግልፅ ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር እና ከሰው ተፈጥሯዊ ሰብእና ጋር የሚጋጨው

ሀሳባቸው፡፡ በዚህ ስሌት እንግዲህ የአለም ህዝቦች በሙሉ በዚሁ እምነት ተይዘው ቢሆን ኖሮ እስከ ዛሬ ድረስ እርስ በእርሳቸው ተጠፋፍተው ነበር፡፡

ሌላው ደግሞ ድሆችን እናጠፋለን እለም ለተሳካላቸው ሰዎች ብቻ ናት የሚል ከፋ ሃሳባቸው ነው፡፡ ሆኖም አሁን ካለው አጠቃላይ የአለም ህዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ድሃ እንደሆነ እሙን ነው፤ ታዲያ በአንድ ጀንበር ይህንን ሁሉ ድሃ መጥረግ ነው አላማቸው፡፡ ሰው ማንንም ተስፋ ማድረግ የለበትም፤ እራሱ የራሱ መፍትሄ ፈጣሪ ነው ይላሉ፤ ሆኖም ግን ሰው ያለ ምግብ ብዙ ቀናት ሊኖር ይችላል እንጂ ያለ ተስፋ ግን ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ሊኖር አይችልም፡፡ ይህንን አስተሳሰብ ነው ሰው እንዲጥል የሚያስተምሩት፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አላማ የሌላት ህይወትን እንቀህ ግደላት ነው ሌላው አስተምህሮታቸው፡፡ እስኪ ያለ አላማ በመንከራተት የእለት ጉርሱን አጥቶ ማደሪያ፣ መጠለያ አጥቶ የሚኖረውን ሰው አስቡት፤ ይህ ህዝብ በሙሉ በእነርሱ ሂሳብ መኖር የለበትም፤ እራሱን ማጥፋት አለበት ማለት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በግልፅ ጅምላ ጭፍጨፋን እንደግፋለን ብለው ነው የሚያምኑት፤ እራሳቸውም በግልፅ እንደሚናገሩት የዚህችን አለም ነዋሪ አሁን ካለበት ቁጥር በተለያየ ሳይንሳዊ በሽታ እንዲሁም ጅምላ ጨራሽ ቫይረሶችን በአየሩ ላይ በመልቀቅ ብዙሀንን በመጨፍጨፍ መቀነስ እና ከእነርሱ ተከታዮች ውጭ ሌላውን ማፅዳት ነው አላማቸው፡፡ እንዲያውም አሁን ኒውክለርን ሌሎች ህይወት ያላቸውን ፍጥረቶችን ሳይጎዳ የሰው ልጆችን ብቻ ማጥፋት እንዲችል አድርገው አሻሽለው ሰርተው ይዘው መሳሪያ እጃቸው ገብቷል፤ መከላከያውንም አምርተዋል፡፡ ይሄንንም ቴክኖሎጂ ለሚፈልጓቸው ተከታዮቻቸው አስቀድመው በመስጠትና በማስጠንቀቅ የአለምን ህዝብ ወደ አምስት መቶ ሚሊዮን የመቀነስ አጀንዳ ነው ያላቸው፡፡

በዚህም አጀንዳ አማካኝነት ሰው ሁሉ የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል፤ ያ ብቻ አይደለም የእነርሱ አባልም ቢሆን እርስ በእርሱ እንዲጠፋፋ ምህረት፣ ይቅርታ፣

• የሰይጣንን ሀሳብ እንስተውም እንደሚል ቃሉ ወገኖቼ ይህ የጠላት ሀሳብ ለእኛ እንጂ ለሌሎች እንዴት ሊገለጥላቸው ይችላል? ታዲያ እኛስ በተገለጠልን ልክ ስራውን ካላፈረስንበት ማን ያፈርስበታል? ነው ጥያቄዬ፡፡ በዚህ አስተምህሮት ሰዎችን ደረጃ በደረጃ ወደ ሰይጣኒዝም ለማስገባት ነው በሰይጣን የታቀደው፡፡ ይህንን አስተምህሮት በሰይጣን አየተመሩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ስማቸውንና ምልክታቸውን እየለዋወጡ በአለማችን ቁጥር አንድ የሰልጣን እና የሀብት ማማ ላይ ተቀምጠው በሰይጣናዊ መዘውር አውሎት የሚመስል! ቴክኖሎጂ የሚመስል ነገር ግን የሰው ልጅችን በሙሉ ለመቆጣጠር የሚያስችል አስትራቴጂ ነድፈው እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡

ወገኖቼ አመኑኝ ይሄ የጠላት ሀሳብ ለእናንተ አልተገለጠም ማለት፣ የለም ማለት አይደለም፣ አለ፡፡ መንፈሳዊው አለም እውነት ነው፤ ሰይጣን ለሊትና ቀን በመሯሯጥ ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ በላብራቶሪ ውስጥ ገብታችሁ በማይክሮስኮፕ ካላያችሁ በስተቀር እነዚያን ደቃቅ ተዋህሲያን አታዩአቸውም፡፡ እናንተ አላያችኋቸውም ማለት ግን ተዋህሲያኑ የሉም ማለት አይደለም፤ አሉ፡፡ ችግሩ እናንተ የምታዩበት መነፅር ወይም አንግል ነው ማለት ነው፡፡ ለማየት ከፈለጋችሁ ሊታዩ የሚችሉበትን ማይክሮስኮፕ መጠቀም ሲኖርባችሁ ነው፡፡ እንደምታውቁት መንፈሳዊውን አለም ለመንብኘት የእምነት መነፅርን ማጥለቅ ይጠይቃል፣ ከዚያ ሁሉንም ነገር መመልከት ይቻላል፤ ስለዚህ ጌታ ያሳየኝ ነገሮች በሙሉ እውነተኞች ናቸው፡፡

ምናልበት ያየሁትን ነገር የምገልፅበት ቋንቋ የማጣት ጉዳይ ካልሆነ እንጂ እንደገናም የእኔ አዕምሮ ውሱንነት ካልሆነ በስተቀር ያየሁት በሙሉ እውነት ነው፡፡ ስለዚህ የማበረታታችሁ ሁሉም ሰው ተዋጊ እንዲሆንና በሰማይ ዋጋ ያለው መሆኑን ተረድቶ ለክርስትናው ትልቅ ቦታ እንዲሰጥ ነው፡፡ ጌታን የተከተለ ሰው ሁሉን ትቶ መከተሉን ሁልጊዜ ማረጋገጥ አለበት ማለት ነው፡፡

ያውቃል፤ ደፋሮችና ኩሩዎች ሆነው ስልጣን ያላቸውን ሲሳደቡ ምንም አይመስላቸውም፤ አይንቀጠቀጡም። መላእክቱ እንኳን በእግዚአብሔር ላይ ቃል አያወጡም፤ እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ ሰይጣንም ያውቃል ይንቀጠቀጣማል።

ምንም እንኳን ይህንን ክፋት ሰይጣን የፈለሰፈው ቢሆንም እነዚህ የኢሉሚናቲ አባላት ለእግዚአብሔርና ለኢየሱስ ያላቸውን አይነት ንቀት መቼም አያሳይም ነበር፤ ዳሩ ግን እነዚህ ሰዎች ለመጥፋትና ለመጠመድ ገና ሲፈጠሩ እንደ እንስሳ አይነት አስተሳሰብ ተሰጥቷቸዋል። ገና ለእነርሱ ባልገባቸውም ነገር ጭምር እየተሳደቡ በጥፋታቸው ይጠፋሉ፤ የአመፃቸውን ደመወዝ ይቀበላሉ፤ ዘፈንን እንደ ተድላ ይቆጥሩታል፤ ታላላቅ ፓርቲዎችን በማዘጋጀት የሰውን ልብ ይሰልባሉ፤ እነርሱ ነውረኞች እና እርኩሶች ሆነው ሳሉ ልብሳቸውንና የሚጠቀሙባቸውን ነገሮች ንፁህ በማድረግ የገማውን ማንነታቸውን በእነዚህ በሚብለጨለጩ ነገሮች ይሸፍናሉ።

ልክ በኖራና በእንቁ እንደተንቆጠቆጠ መቃብር ናቸው፤ ምንዝርና የሞላቸውና ሃጥያትን የማይተዉ የሚታዩ አይኖቻቸውን ተጠቅመው የዋህ የሆኑትን ቃሉን እየተማሩ እውነትን ወደማወቅ የማይደርሱትን ያስታሉ፤ ያልፀኑትንም ነፍሳት ያጠምዳሉ፤ ምኞትን ይወዳሉ፤ አይጠግቡምም፤ የተረገሙ እርጉማኖች ቆሻሾች ናቸው፤ የአመፅ ደመወዝ ተዘጋጅቶላቸዋል፤ ቅንን መንገድ የክርስቶስን መንገድ ትተው በሀሊናቸው ከንቱነት ከእውነት መንገድ ጠፍተዋል። ለእነዚህም ድቅድቅ ጨለማ፣ የማይሞቱ ትሎች፣ እባብ የሚርመሰመስበት ጉድጓድ፣ በድኝ የተሰበጠ የእሳት ጉድጓድና፣ ለሰጣይንና ለመላእክቱ የተዘጋጀላቸው ገሃነም እሳት ይጠብቃቸዋል።

እነዚህ ውሃ የሌለባቸው ምንጮች ናቸው፤ በአውሎ ንፋስ እንደሚጠፉ ደመናዎች ናቸው፤ ከንቱና ከመጠን ይልቅ መጥፎ የሆነውን ቃል ይናገራሉ። እውነትን በአመፅ ይከለከላሉና ስለዚህ የእግዚአብሔር ቁጣ በላያቸው ላይ

ኢየሱስ ያድናል!! ጌታም እንዲህ አለኝ "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱ እንደ ስራው እከፍላለሁ፤ ጆሮ ያለው ካለ ይስማ፤ ያስተውል፤ ድል ለነሳው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፤ እኔ የህይወት እንጀራ ነኝ፤ ቃልም ስጋ ሆነ እውነትና መንፈስን ተሞልቶ በእናንተ ያድራል፤ እንግዲህ ከወደዱት እንደወደድኋችሁ እስተውሉ፤ ንስሃ ግቡ፤ እኔ እውነትና መንገድ ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ ዘላለማዊ ህይወት የሚገባ የለም፤ እኔ የሰው ልጆች ብርሃን ነኝ፤ ጭለማም አያሸንፈኝም፡፡ ድል ለነሳው በገነት ካለው የህይወት ዛፍ እሰጠዋለሁ እርሱም ይበላል ለዘላለምም አይራብም፤ የሚሰማ ሁሉ እነሆ በቶሎ እመጣለሁና 'ማራናታ' ይበል" አለኝ፡፡ እኔም "አሜን ማራናታ ጌታ ሆይ ቶሎ ና" አልኩኝ፡፡

መልአኩ ገብርኤል "ሰይጣንና ሰራዊቱ ፈታኙሁ ስለመሸኑ አንተም ሚካኤል አሁን ሰራዊትህን ወደ ሰይጣን እና ወደ ሰራዊቱ አድርግ" የሚል መልእክት 'ከጌታ-ኢየሱስ' በሚል ፖስታ መሳይ ነገር አስተላለፈላቸው።

ወዲያው ውጊያው በሚካኤል እና በመላእክቱ ከሰይጣን እና ከሰራዊቱ ጋር ተጀመረ። ሰማዩም ቀላ። በዚህ ውጊያ ላይ ሀይለኛ የሆኑ እና በምድር ላይ ፈፅሞ አይቻቸው የማላውቃቸው የጦር መሳሪያዎች ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር። እርኩሳን መናፍስቱም መላእክቱን ተቋቋሟቸው። ያንጊዜም እነዚያ ታላላቅ የምድር በረከቶችን የሚጉ መላእክቶች ባሉበት ቦታ ተከልክለው ቆሙ። ወዲያውም መንፈስ ቅዱስ በምድር ላሉ ቅዱሳን ሰልባቸው በአየሩ ላይ ስላለው ውጊያ ለብዙዎች ገለፀላቸው። ብዙዎችም ከእንቅልፋቸው በመንቃት ሰይጣንን እና ሰራዊቱን ከምድር መቃወም ጀመሩ። ሌሎቹ ደግሞ አምላካቸውን እግዚአብሔርን ማመስገን ቻሉ።

ያኔ ታዲያ እንደ ረጅም ባውዛ አይነት ብርሃን የተሞላ ሚጌፉ እንደ ጦር መሰሉ ነገር ግን ተቀያያሪ ባህሪ ያለው የጦር መሳሪያ ከምድር የተለያዩ አገሮች ካሉ ቅዱሳን ከእያንዳንዳቸው ያለማቋረጥ እየተግተለተለ እየወጣ በእርኩሳን መናፍስቱ ላይ ይዘንብ ጀመር። ይህ ጦር በየእርኩሳን መናፍስቱ ልብ ላይ በመሰካት እንደ እቧራ ያቦናቸው ነበር።

በሰማዩም ላይ የአቧራ ጭስ ሞላ። ሰይጣን እና ሰራዊቱም ሲበታተኑ አየሁ። ወዲያውም በምድር ያሉ የሰይጣን ወኪሎች አንዳንድ የእግዚአብሔር ታላላቅ ሰዎችን ፓስተሮችን፣ ነብያትን እና አገልጋዮችን ውጊያቸውን አቁመው እርኩሰት እንዲሰሩ በመገፋፋት ሲያረክሷቸው ተመለከትሁ። ሌሎች ቅዱሳን ደግሞ በመታከት እና በድንዛዜ ሲሞቱ አብዛኞዎቹ ወደየግል ጉዳያቸው እንዲያተኩሩ ሲያደርጓቸው አየሁ።

እያየ ጥርሱን ነክሶ ከሁለት ዓይኖቹ እንባ መንታ፣ መንታ ሆኖ ይወርድ እና ያለቅስ ነበር፡፡

በለቅሶ ሲቃ ድምፅም "ልጄ ና ተመለስ ዛሬም አልረፈደብህም ሊታስተካክለው ጊዜህ በእጅህ ነው፡፡ በምንም ለመከለል አትሞክር፤ ሲቃዩን ኢታብዛው ብለህ ንገራቸው" ሲለኝ የተወሰኑ የአህጉሪቱ ፓስተሮች እና ነብያት ከእኔ ጋር መሬት ላይ ወድቀን በንስሃ በማንባት ላይ ሳለን ስማያት ተከፈቱ እና የአፍሪካን በረከት የሚነው ግዙፍ መልአክ በጌታ ትዕዛዝ አዲስ አበባ ላይ ሲያርፍ ከዚያም ሌሎቹንም በረከቶች የሚኑት የየአህጉሩ ግዙፍ መላእክት በጌታ ትእዛዝ በኢስያ፣ ላቲን አሜሪካ፣ አውስትራሊያ፣ አውሮፓ እና አሜሪካ በተመረጡ ታላላቅ ከተሞች ላይ በክብር አረፉ፡፡

ለአፍሪካ የመጣው እና አዲስ አበባ ላይ ያረፈው በረከት እንደ ደረሰ ጌታ ኢየሱስ ራሱ በክብር ለአንድ ታላቅ ኢትዮጵያዊ መንፈሳዊ አባት የበረከቱን ቁልፍ ሲያስረክባቸው ታላቅ እልልታ እና ደስታ በኢትዮጵያ ሰዎች እና በመላው አፍሪካ ሰዎች ላይ ሆነ፡፡ ከዚያም ጌታ እኚህን ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው የአፍሪካ አባት እንዲሆኑ እና በረከቱን እንዲያከፋፍሉ ራሳቸውን በዘይት ቀባቸው፡፡

በአህጉሪቱ ከሚገኙ አገሮች በጌታ የተመረጡ ፓስተሮች እና ነቢያት እንዲሁም አገልጋዮች በአንድ ታዋቂ ናይጀሪያዊ ፓስተር እየተመሩ ወደዚህ በረከት ሲታደሙ ተመለከትሁ፡፡ እነርሱ ብቻም አልነበሩም የአፍሪካ መሪዎችም በኢትዮጵያዊው መሪ እየተመሩ መጥተው በረከታቸውን ከእኚህ አባት እጅ በመረከብ ላይ ሳሉ ዙሪያቸውን የእግዚአብሔር መላእክት ቆመው ስርዓቱን ሲያስተባብሩ ሳሉ ብዙ አጭበርባሪ እና ሃሰተኛ ፓስተሮች፣ ነብያትና አገልጋዮች በጌታ ትእዛዝ በመላእክቱ በእሳት ታጥረው ወደ በረከቱ እንዳይገቡ ሲከለከሉ ተመለከትሁ፡፡

ከዚያም ከተለያዩ የአፍሪካ አገራት ለመጡ እና እጅግ ብዙ ለሆኑ ወደፊት የአገር መሪዎች፣ ነብያት እና ፓስተሮች እንዲሁም አገልጋዮች የሚሆኑ ህፃናት ራሳቸው በዘይት ከተቀባ በኋላ መንፈሳዊ ዓይኖቻቸውን የመከፈት ስነስርዓት ተከናወነ:: ከዚያም የድል ችቦ ከጌታ ተቀበሉ:: ህፃናቱም ላይ ትንቢት ተነገረባቸው:: ይህንን ትንቢት ይናገሩ የነበሩትም አንድ ኢትዮጵያዊ ፓስተር ነበሩ:: እርሳቸውም ህፃናቱን እንዲህ በማለት ባረኳቸው "ሂዱ የአፍሪካን መአድናት የሚበረብር ዓይን ይሁንላችሁ፤ እውቀታችሁ ለህዝባችሁ አድርጉት" ብለው እንደተናገሩ ወዲያው የምድሪቱ ተራሮች እና ምድረ በዳዎች ተገልጠው በረከትን ሲያንጠባጥቡ ተመለከትሁ:: መአድናቱን እየበረበሩም ለአገራቸው ጥቅም አውጥተው ሲጠቀሙ፤ አገልጋዮቹም የእግዚአብሔርን ቤት የአምልኮ ስርዓት ፈፅመው ሲያስተካክሉ ተመለከትሁ::

በኋላም ከአፍሪካ የተለያዩ አገራት የተሰባሰቡ ዘማሪያን እነዚያን ህፃናት ትንቢታዊ በሆነ ዝማሬ እንዲህ አሏቸው፤ "ለህዝባችሁ ስሩ እትታክቱ፤ ድከሙ፤ የሰይጣንን ስራም አፍርሱ፤ ህዝባችሁን ውደዱ ፍትህን አስፍኑ፤ ደምን አታፍስሱ ሁሉን በቅንነት አስተዳድሩ፤ በእውቀት እና በጥበብ ምድሪቱን ግዟት" እያሉ በዝማሬ ከባረኳቸው በኋላ እጅግ የሚያምር ውብ መዓዛ ያለው ዝማሬም ለጌታ ከህዝቡ ጋር ያቀርቡለት ጀመር::

በዚህ ፕሮግራም ላይ ከተለያዩ አብያተክርስቲያናት የመጡ ፓስተሮች እና አገልጋዮች እንዲሁም ጥቂት የኦርቶዶክስ እና የካቶሊክ የእምነት አባቶች እና ካህናቶች ከኢትዮጵያ ሲገኙ በተጨማሪም ከተለያዩ የአፍሪካ አገራት የመጡ ብዙ የማላውቃቸው እና ታዋቂ የሆኑ ፓስተሮች፣ ነብያቶች እና አገልጋዮች በክብር ተደርድረው የማዕረግ ልብሳቸውን ለብሰው በበእሉ ላይ ታድመው ይታዩ ነበር::

ከዚያም ከእነዚህ ፓስተሮች እና አገልጋዮች የተወሰኑት ተራ በተራ ስለመጣው የአፍሪካ በረከት እግዚአብሔርን ካመሰገኑ በኋላ ጌታም "አሁን የክብር ሽልማት የሚገባው ሰው ይመጣል" ብሎ ሲናገር ህዝቡ ሁሉ እና የየአገራቱ መሪዎች ሁሉ

ከመቀመጫቸው ተነሱ፡፡ ያኔ ታዲያ ይህ የከብር እንግዳ ቀደም ሲል የአፍሪካን በረከት በማስለቀቁ ውጊያ ላይ ከፍተኛ ተጋድሎ የፈፀመው ኢትዮጵያዊ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው በመላእከት ታጅቦ እጅግ የሚያምር የከብር አክሊል ደፍቶ ሁለቱን ልጆቹን ከግራና ከቀኝ አስከትሎ ሲመጣ ተመለከትሁ፡፡ የተቀመጡትንም ህዝብ በእጁ ሰላምታ እየሰጠ ወደ ጌታ ለሽልማት ቀረበ፡፡ ጌታም በወርቅ እና በእንቁ የተንቆጠቆጠ የአበባ ጉንጉን የመሰለ ነገር በአንገቱ ላይ ካጠለቀለት በኋላ ሁሉም እያዩት እዚያው ፕሮግራም ላይ ከሌላ ውብ ቆንጆ ወጣት ሴት ጋር የጋብቻ ስነስርዓት ተደረገለት፡፡

በተመሳሳይም በየአህጉራቱ እንደርሱ በፀሎት ይጋደሉ የነበሩትም ተመሳሳይ ሽልማት ከጌታ ከተበረከተላቸው በኋላ ወደ አንድ ዘመናዊ ቤት በመላእከት ታጅበው ሲወሰዱ ተመለከትሁ፡፡ እንደዚሁ አይነቱ ፕሮግራም በተመሳሳይ ጊዜ በየአህጉራቱ በተመረጡ ከተሞች እየተከናወነ ነበር፡፡ ጌታም በሁሉም ስፍራዎች በተመሳሳይ ሰዓት ተገኝቶ ከአህጉራቱ የተመረጡትን አገልጋዮች ይሸልም ነበር፡፡

ስነስርዓቱም ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ታዳሚው ሁሉ ቆሞ ነበር የተከናወነው፡፡ ፕሮግራሙም ከጌታችን ባርኮት በኋላ ሲደመደም ሁሉም ወደየመጣበት አገር በብዙ በረከት ሲመለስ እያንዳንዱ ታዳሚ የሚመለስበት አገር ሁሉ ከፊቱ አሮጌው ነገር እየተደረመሰ እና እየጠፋ ወደ አዲስ እና የሚያምር እጅግ ዘመናዊ ሁኔታ ይቀየር ነበር፡፡ ኋላም እኛም ተሳፍረን በመጣንባት የብርሃን ሉል በመጣንበት ሁኔታ መጓዛችንን ቀጠልን፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## ጉዞ ወደ ሲኦል

### የሲኦል መልክ

የብርሃን ሱሪ ከመሬት ከፍ እንዳለችም ሰይጣን በአየሩ ላይ በዘንዶ መልክ እየተወራጨ የራሱን ሰራዊት ሢምር በመጨፍጨፍ እና በምድር ላይ የተለያዩ መቅሰፍቶችን በሰው ልጆች ላይ በማድረስ ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ጩኸት እያሰማ ከአፉ እሳትን በመትፋት እየዞከረ እንዲሁም እግዚአብሔርን ይሳደብ ነበር። በኋላ ግን ሳያስበው ድንገት ከሰማይ እሳት ሲወድቅበት የታሰረበት ሰንሰለት ታየን። ከዚያም መላእክቱ በቀጥ መልሰው ትተውው ወደ ጥልቁ ወረወሩት፤ ጌታም "አሁን ወደ ሲኦል ስለምንሄድ ተዘጋጅ" አለኝ፤ እኔም "ጌታ ሆይ ያንን ቦታ አኮ እፈራዋለሁ" አልኩት። ጌታም "እኔ አኮ ከአንተ ጋር ነኝ አትፍራ" ሲለኝ ያን ጊዜ በረታሁኝ እና ጉዟችንን ወደ ምድር ልብ ውስጥ ወደ ሲኦል ቀጠልን።

ከርቀት ወደ ጥልቁ እየወረድን ሳለን በጀርባዋ የተንጋለለች ሴት የመሰለ ቅርፅ ያለው ግዙፍ ጨለማ ለማየት ቻልሁ፤ ያን ጊዜ "ጌታ ሆይ ይሄ ምንድነው?" ብዬ ጠየቅሁት እርሱም "የሲኦል መልክ ይሄ ነው" አለኝ። "ታዲያ ይህ የሴት ምስል ምንድነው?" አልኩት እርሱም አለኝ "የምታየው ምስል አሁን በዚህ ዘመን ሰይጣን የሚሰራባት የኤልዛቤል ተምሳሌት 'የጠረፏ ንግስት' ብላ ለራሷ ስያሜ የሰጠችው የዝሙት መንፈስ ተምሳሌት ነች" አለኝ።

ከዚያም ወደ ጨለማው ቅርፅ ስንጠጋው በጀርባዋ የተንጋለለች እና እግሮቿን እንፈራጣ ለግብረ ስጋ ግንኙነት የተዘጋጀች ሴት ትመስል ነበር፤ ነገር ግን ከብልቷ ውስጥ እሳት ወደ ውጪ እንደ አባብ ምላስ ያገኘውን ለመንደፍ መንታ ሆኖ

ወዲያ እና ወዲህ ይወናጨፍ ነበር፡፡ ከዚያም የበለጠ እየተጠጋን ስንመጣ የእሳቱ መጠን እጅግ ትልቅ ነበር፡፡

ከወደ ግራ በኩል የሆነ የሚጫጫታ ድምፅ መሰማት ጀመርን ወዲያውም ስንቀርብ አንድ ሙስሊም ሽማግሌ በሰይጣን እርኩሳን መልአክት እየተሰቃየ ነበር፡፡ ሽማግሌውን "ግባ" ይሉታል እርሱ ደግሞ "አልገባም እኔ በቀን አምስት ጊዜ እሰግዳለሁ፤ በወጣትነቴ አፍጋኒስታን ውስጥ ቅዱስ ጦርነት ተዋግቻለሁ፤ ሁለት ካፊርም ገድያለሁ፤ እድሜዬን ሙሉ ከዜና እርቄ ቁርአን ስቀራ ነው የኖርኩት፤ ሁልጊዜ የሀብቴን ግማሽ ጁምአ በመጣ ቁጥር ዘካ እሰጣለሁ፤ ለዚህም ነብያችን ሰለላ አውሰለም እና አላህ ምስክሮቼ ናቸው" ሲል አንድ ክፉ እርኩስ መንፈስም "ካካካ" እያለ አሽካካ እና መለሰ "የእኛ ቅዱስ ካካካ አንተ አይደለህም እንዴ ታላቅ ወንድምህን ሀብቱን ፈልገህ በመድሃኒት አስገድለህ፤ ልጆቹን ሜዳ ላይ በትነህ፤ ሃብቱን እና ሚስቱን ከወረስክ በኋላ ሚስቱን ቀጥቅጠህ የገደልካት? ከአልጋ ላይ ወርውረህ ጥለሃት ወድቃ ሞተችብኝ ብለህ ሶስት ቀን ሀዘን ተቀምጠህ በወረስከው ንብረት እስላምን እንድታሸብር ተጠቀምክብህ፡፡

ኸረ ለመሆኑ ግን ሰለላ አውሰላም ነብይ የምትለው መሃመድን ማነው ነብይ ያደረገው? እርሱ እኮ የእኔ መጠቀሚያ ነው፡፡ ስለዚህ ነው እንደ አንተ አይነቶቹን ወርበላ የሚደብቅ ጭንብል 'የአላህ ህግ ነው' ብሎ እንዲያስተምር ያደረግሁት፡፡ ከፈለግህ ደግሞ እንዴት እንደተጠቀምሁበት ላሳይህ እችላለሁ፤ ተመልከት" ብሎ ሲናገር የመሃመድን ታሪክ መመልከት ጀመርን፡፡

እምላኩን መሳደባቸውን አይተዉም ነበር፤ ሆኖም እነዚህ እርኩሳን መናፍስት እኛ እንያቸው እንጂ እነርሱ ግን እኛን አይመለከቱም ነበር፤ ሰዎች የሆኑት ግን እየተቃጠሉም ቢሆን እኛን ያዩን ነበር፡፡

ቀደም ሲል ከሰይጣን ጋር ቃለ-ምልልስ ሲያደርግ የነበረው እላማ ሼኪ እየሮጠ መሃመድ ወዳለበት የእሳት ጉድጓድ ሲጣል ከመሃመድ ጀምሮ ጉድጓዱ ውስጥ የነበሩት ብዙዎቹ ሙስሊሞች ፈገግ ሲሉ ተመለከትሁ፡፡ የራሳቸው መቃጠል ሳያንስ ሌሎች ወደዚህ እስከፊ የእሳት ጉድጓድ ሲጣሉ የጨለመ ፈገግታ ያሳዩ ነበር፡፡ እኔም ለምን በሰው ውድቀት ይደሰታሉ ብዬ እያሰብኩ ሳለሁ ጌታ "ልጄ እዚህ ያሉት ሰዎች እኮ በምድር ላይ በነበሩበት ወቅት የነበራቸው ሰሜት ሁሉ በእስር እጥፍ አድጎ ነው የሚሰማቸው፡፡ ብዙዎቹ በምድር ሳሉ ከራሳቸው ማግኘት ይልቅ የሌላው ማጣት እና ሀዘን የበለጠ ያስደሰታቸው የነበሩ ናቸው" አለኝ፡፡ እኔም አንዳንዶቹ እንደውም እግዚአብሔር ጨካኝ ስለሆነ ነው እንጂ "ለምን ሲኦልን ሰራ" ብለው ንስሃ ከመግባት ይልቅ ጣቶቻቸውን ወደ እግዚአብሔር ቀስረው ሲሳደቡ ተመለከትሁ፡፡

ፍርሃት፤ ወይንስ ሰይፍ፤ በዚህ ሁሉ ግን በወደድኩህ በእኔ ከአሸናፊዎች ትበልጣለህ፡፡ ሞት ቢሆን፤ ህይወትም ቢሆን፤ መላእክትም ቢሆኑ፤ ከፍታም ቢሆን፤ ገዢታም ቢሆን፤ ልዩ ፍጥረትም ቢሆኑ፤ ከእኔ ማንም ሊለይህ አይችልም፡ አለኝ፡፡

## ኢትዮጵያዊው እኔ

ጉዟችንን በሲኦል ውስጥ ቀጥለናል፡፡ ከዚያም አንድ ፅሁፍ ተመለከትሁኝ 'የይሁዳ ንጉስ' ይላል፡፡ በጣም ተገርሜ "ማን ይሆን?" ብዬ ተጠግቼ ብመለከት የእኛው አገር የቀድሞ መሪ መሆናቸውን ተረዳሁ፡፡ እርሳቸውም ልክ እንደ ዘፋኙ ሁሉ አኟቸው ግራ እና ቀኝ ታስሮ የከበረ ዘበኛ ዓይነት ቆብ ደፍተው ነበር፡፡ ጌታን እንዳዩትም "አባክህን እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ማረኝ" እያሉ ሲያለቅሱ ያንጊዜ አንድ አጅግ የሚዘገንን ዘንዶ በመቀመጫቸው ገብቶ በአፋቸው ወጣና "ማረኝ፣ ማረኝ ማነው የሚምርህ? እኔ በአንተ ስም እየተመለከሁኝ ነው፡፡ ምን ነካህ ስዩመ እግዚአብሔር" እያለ በማሽሟጠጥ ተናገረ፡፡ "በአንተ ስም የሚያመልኩኝ ብዙ ሚሊዮን ተከታዮች አሉኝ፤ ሰማህ!" ሲልም አንባረቀባቸው፡፡

ሸማግሌውም "አንተ ከይሲ አሳትከኝ" አሉ፡፡ እኔንም እንዲህ አሉኝ "ልጄ አባክህ ለአገሬ ልጆች እኔ ሞቻለሁ፤ እኔ ተሳስቻለሁ ሰይጣን ነው በውስጤ አድሮ እኔ እንደማልሞት የነገራችሁ አባካችሁን ስቃዩን አታብዙት" እያሉ መጮህ ሲጀምሩ በጉድጓዱ ውስጥ ባሉት ትሎች ሰውነታቸው በሙሉ ተከደነ፡፡ እኚህ ኢትዮጵያዊ እኔ ባሉበት አካባቢ የሌሎች የቀድሞ የአገር መሪዎች እና አፄዎች የእሳት ጉድጓዶችም ነበሩ፡፡

የእግዚአብሔር መንፈስ ጥያቄ ይኑር አይኑር አላውቅም፤ በአይኔ አላየሁ፤ ዝም ብለው ነው ነቢዮቹ ሐይማኖትን የፈጠሩት፤ ለቅኝ ግዛት ነው። እግዚአብሔር የሚባል ነገር የለም ያሉት ልክ ነው" እያለ በህሊናው እያሰላሰለ ሳለ ሰይጣን ሃሳቡ እንደተሳካለት ተመልክቶ እርኩስ የሆነ ሳቁን ይስቃል።

ከዚያም ሰውየውን ልክ እንደ ፈረስ እየጋለበው የእርሱን ሃሳብ የሚደግፉለትን ማስታወቂያዎች እንዲያነብ እንዲሁም ሀሳቡን የሚደግፉለት ፊልሞች ወደሚታዩበት ፊልም ቤቶች ይወስደዋል፡፡ ስለ ክህደት የሚያወሩ መፅሃፍት የሚያገኝበትን እድል ይፈጥርለታል፡፡ የሚያገኛቸውን ሰዎች እንኳን እላማውን የሚያሳኩ እንዲሆኑለት ሰይጣን ይመርጥለታል፤ ከዚያም ክርስቶስን ካስካደው በኋላ የመጠጥ፣ የጫት፣ የሃሽሽ፣ ሱሰኛ ያደርገዋል። የገቢ ምንጭ እንዲያጣ እያደርገውም፤ ሁሉን በአስፈላጊው ጊዜ የሚያገኝበትን ሰይጣናዊ መንገዶች ይሰጠዋል። ለምሳሌ ምን ቢሰራ የተሳካለት የንግድ ሰው መሆን እንደሚችል ይገልጥለታል።

በሲኦል ውስጥ እያንዳንዱ የእምነት አይነት በየራሱ ስም የእሳት ጉድጓድ ነበረው፤ በዚያም እየተመለከትሁ ሳለ አንድ እድሜው እስከ 80 አመት የሚገመት የህንድ ሽማግሌ በሲኦል ውስጥ በመቃጠል ላይ ነበረ:: በምድር ላይ ያከናወናቸውን ነገሮች እየተመለከትሁ ነበር::

ይህ ሰው በህንድ አገር ካርላሽቶ (ኔፓል) በምትባል ግዛት ውስጥ ይኖር ነበር:: ወጣት ሳለ እድሜው ለጋብቻ ሲደርስ ሚስት ቢያገባም ነገር ግን ልጅ የወለደው በ29 ዓመቱ ነበር:: በአካባቢው የተለያዩ በጥንቆልና የሚተዳደሩ ሰዎች ሞልተው ነበር:: እያንዳንዱ በዚያን ዘመን የነበረ ሰው ሁሉ ወደ አንደኛው ጠንቋይ ቤት በመሄድ የአማልክት ተገዢ መሆን ነበረበት:: ነገር ግን ይህ ወጣት አባቱ የአካባቢው ገዢ ስለነበሩ በዚሁ ምክንያት ከልጅነቱ ሰው ሁሉ እየወደቀ እጅ ሲነሳው ያደገ የንጉስ ልጅ ነበር:: ነገር ግን እነዚህ በአካባቢው ያሉ ጠንቋዮችና አማልክቶች አኩል የአካባቢው አስተዳደር ጋር በህብረተሰቡ ይከበሩና ይመለኩ ስለነበር እና እንዲያውም አንዳንዴ ህዝቡ ከአባቱ አስተዳደር አስበልጦ ለአካባቢው አማልክቶች ይገዛ ስለነበር አባቱ ይህ ጉዳይ ያበሳጫቸው ነበር::

ይህን የተመለከተው ይህ ወጣት አንድ መላ መዘየድ እንዳለበት ያሰብ ያሰላስል ጀመር:: ይሁንና ያሰባቸው መላዎች በሙሉ ህብረተሰቡ ለአማልክቶቹ በሚሰጠው ከፍተኛ ቦታ ምክንያት ሲበላሹበት ከቆዩ በኋላ "ለምን እኔስ የአምልኮ ቤተ-መቅደስ አላሰራም ከእነዚህ በአካባቢያችን ሁሉ ካሉ አማልክቶች በላይ የሆነና የሚያሳያምን የእምነት ዶክትሪን ለምን አላዘጋጅም ብሎ የእያንዳንዱን አማልክት እና ጠንቋይ ቤት ስርዓትና የአምልኮ ደንብ መከታተልና ማጥናት ጀመረ:: ከዚያም በኋላ በ35 ዓመቱ በአንድ ምሽት ይሄንኑ ሃሳቡን

ነገር ግን በዮቶን እጅግ ብዙ ህዝብ ዘር፤ ቀለም ሳይለይ ከተለያዩ የአለም አገራት ይጎርፍበት ነበር፤ ሰይጣንም እነዚህ እምነት የሌላቸውን ሲያገኝ "አሁንስ እኔንስ አታምንም?" እያለ በማሳገጥ ይጫወትባቸው ነበር፤ ወገኖቼ ታዲያ ለእያንዳንዳቸው መሳት ምክንያቱ እራሱ ሰይጣን መሆኑን ለመገንዘብ ቻልኩ፤ የሰው ልጅ ለዘያች አኗኗር ዘመኑ ለመኖር ከሰው በላይ የመሆን ህልሙ ለብዙዎች የሲኦል የመቃጠያ ምክንያት መሆኑ እጅግ ይገርመኝ ነበር፡፡

ሁልጊዜ በአለም ሳለን በምንኖርበት አካባቢ የበላይ ለመሆን እንዲሁም ሃብታም ለመሆን የሚመጡልንን ሃሳቦች ቆም ብለን ልናስብባቸው ግድ ነው፤ አለዚያ ከራስ አልፎ እስከ ዘር እንዲሁም ትውልድን በየዘመናቱ የሚቀጥፍ መርዝ ተክሎ ማለፍ ይሆናል ፍፃሜው፡፡ ሁልጊዜ ደግ መስሎን በምናውጠነጥነው ሃሳብና መፍትሄ ሰይጣን ሊጠቀምበት እንደሚችል ከዚህ ታሪክ መረዳት ይቻላል፤ ከአስተሳሰቦቹ ጀርባ ሆኖ በብዙዎች ልብ እየተመሰከ የቡድሃን ምስል አስቅሎ ያ በውስጥ ያለውን የሰው ልጆች ሁሉ ጠላትነት እርሱ ለዘላለም ተፈርዶበት ሰዎች ግን በህይወት መመላለሳቸው በቅናት አይን እርር ብሎ በምቀኝነት ወደዚህ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ሰዎች እንዳይገቡ አጥምዶ እየተበቀለ ነው የሚገኘው፡፡ ወንድሜ ልንገርህ ቡድሃ ነኝ በማለት ከእሳት ባህር ማምለጥ እንደማትችል ለገልፅልህ እወዳለሁ፡፡

እነርሱ በየአካባቢያቸው በሚገኙ ጥንቱልና ቤቶች በመቶት በመተብተብ ብዙ ጊዜ ሰዎች በአጠገባቸው ሲያልፉ እንኳን በሰይጣን ሰራዊቶች ወደ እነዚህ ቤቶች እንዲገቡ በመወስወስ ብዙዎችን ንብረት እና ትዳር አልባ አድርገዋቸዋል። በእነዚህ መናፍስት አማካኝነት የስንቱ ትዳር ፈርሷል። ብዙዎች በበሽታ ተመትተዋል ብሎኝ እየተመለከትን በዚህች ሴትዮ ቤት እና በተለያዩ በካባንችስ ባሉ ጭፈራ ቤቶች በድብቅ ዘንዶ ተነጠምጥሞ ወደ ውስጥ የሚገቡትን እየጠበቀ ሲወጋ ይታይ ነበር።

ይኸው ትዕይንት በአለም ዙሪያ ባሉ ምሽት ቤቶችና በቀን የገዘሙት ቤቶች አማካኝነት ወደ ሲኦል ደጅ (በር) ልክ የቤት ብልት በመሰለ መግቢያ በዘንዶው መርዝ እየተወጉ ሰዎች ወደ ውስጥ ሲገቡ ተመለከትን። ከዚያም ወደ ሴትዮዋ ስመለከት በአባብ በተሞላ ጉድጓድ ውስጥ እየተነደፈች በከፍተኛ ሁኔታ ትሰቃይ ነበር። እሳቱም ትሉም በየፈረቃው ይርመሰመስባት ነበር።

እንደገና ወደ ሆቴሏ እየተመለከትን ሳለ አንድ ግንባሩ ላይ ብርሃን ያለበት ወጣት ሰው ወደ ሆቴሏ ሲገባ ተመለከትን። ይህም ወጣት ከክፍለ አገር "እግዚአብሔርን አገለግላለሁ" ብሎ ወደ አዲስ አበባ የመጣ ሰው ነበር። ምንም እንኳን አገለግላለሁ ብሎ ንብረቱን ሸጦ የመጣ ቢሆንም ነገር ግን ይሄንን ወጣት አስጠግቶት የአገልግሎት በር የከፈተለት ቤተክርስቲያንም ሆነ ሰው አልነበረም። ለተለያዩ ቤተክርስቲያኖችና አገልጋዮች ጥሪውንና ያለውን የአገልግሎት ጥማት ቢያስረዳቸውም እነርሱ ግን ፊዐመው በራቸውን ሊከፍቱለት አልፈለጉም ነበር። ይሄ ወጣት እራሱን ዝቅ አድርጎ የቤተክርስቲያን ዘበኛ እስከሆን ቢደርስም ምንም ተቀባይነት ያጣል። ኋላም ከዚያ በፊት ያስተዳድር የነበረውም ሆነ ይዞት የመጣው የራሱ ንብረት እና ገንዘብ ሁሉ ስላለቀበት ስራ ፍለጋ ወደ ደላላ ቤት ይሄዳል።

ትመጣለች፡፡ ከባለውስኪ ቤቷ ጋር ትንሽ ከተጨቃጨቀ በኋላም ስራዋን ትጀምራለች፡፡

የፅዳት ሰራተኛዋም የፅዳት ቁሳቁሷን ይዛ እና ልብሷን ለብሳ ወደ መፀዳጃ ቤቱ በመግባት ተጠቃሚዎቹ መጥተው እንዳያስቸግሯት ከውስጥ በኩል በመቆለፍ አዚያ መጥፎ ጠረን ያለበት ቦታ ሆና ወደ ጌታ "እባክህን ከዚህ ቦታ አውጣኝ" እያለች ማልቀሷን ተያያዘችው፡፡ "አባርከሻለሁ ደቡብ አፍሪካ ሂጂ ያልከኝ ለዚህ ነው? አባ መጥተሽ የእኔን ቤት ትሰሪያለሽ ያልከኝስ? በዚያ አንተን በሚፈራ ነብይ የተናገርከኝ፤ እንዲህ አላልከኝም? 'አንቺን ባርኬ ይህን ባሪያዬን ከቤት ኪራይ እና የቤት ኪራይ እንኳን መክፈል ከማይችልበት ሕይወት አወጣዋለሁ፤ በአንቺ የገንዘብ ድጋፍ እኔ የሰጠሁትን ራዕይ እውን ያደርጋል' ብለህ በባሪያህ በኩል በራዕይ የተናገርከኝስ የታል? እኔ እኮ የውስኪ ቤት አገልጋይ፤ የሰካራም ትውከት ጠራጊ እና የሽንት ቤት ፅዳት ሰራተኛ ነኝ፡፡ የታል የተሰፋ ቃልህ?" እያለች እንባዋ መንታ መንታ እየሆነ ይፈስስ ጀመር፡፡ እዚያው ሽንት ቤቱ ውስጥ እያለች እንባዋን በሶፍት ከጠራረገች በኋላ ሞባይሏን አውጥታ አዲስ አበባ ለሚገኘው ለዚያ መልዕክት ላመጣላት ነብይ ደወለችለት፡፡

ያን ጊዜም ያ ነብይ ብርቱ ፀሎት እያደረገላት እንዳለ እና ጠላት ሊያጠፋት ቆርጦ መነሳቱን፤ ነገር ግን ሁሉ ለበጎ እንደሚቀየር ይነግራታል፡፡ እርሷም ስለ እርሱ እንደምታስብ ነግራው "አንተ እኮ እንዲህ ያለ እውነተኛ ፀጋ ይዘህ እንዲህ በቅድስና እያገለገልክ ደመወዝ የለህ፤ እንዴት ነው እየኖርክ ያለኸው? የቤት ኪራይስ አልደረሰም?" ስትለው "ያው ሶስት ቀን ነው የቀረው አከራይዋ ደግሞ እንዲትም ቀን ካለፈባት የሞዛ አይደለችም 'ውጣልኝ' ነው የምትለኝ" አላት፡፡

እርሷም እየሰማችው እንባዋ በጉንጮቿ ላይ ይወርድ ነበር፡፡ "ሶስት ወር ሙሉ እርሱን እንኳን መርዳት አለመቻሌ አሁን እኔ ምን እረባለሁ" እያለች እርሱ እያወራት ታስብ እና ታለቅስ ነበር፡፡ የመጀመሪያ ወር ደመወዟን ያኔ ስራ ፈትታ በተቀመጠችበት ወቅት ላበደሯት ሰዎች በመመለስ ጨርሳው ነበር፡፡ የሁለተኛው ወር ደመወዝ ደግሞ ገና አልደረሰም፤ ምክንያቱም ገና ሃያ ቀን ነው የሰራችው፡፡

ከዚያም አንዳንድ ስራ ቦታ ከተዋወቀቻቸው ሰዎች የሚሰጧትን ብር ካጠራቀመችው በማግሰቱ ጠዋት 100 ዶላር እንደምትልክለት ትነግረዋለች፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ ከውጪ ሲንኳኳ "በል ቻው ነገ እልክልሃለሁ፤ ነገ ልደውል አሁን ወደ ስራ ልግባ" ብላ ስልኩን ዘግታ ማፀዳዳቷን እንደቀጠለች የጠረጴዛ እና የወንበር ጓጓታ እልፎ አልፎም ድው የሚል ድምፅ እና ጢው ጢው የሚል ድምፅ መሰማት ስትጀምር እዚያው መፀዳጃ ቤት ውስጥ ሆና ሁኔታዎችን መከታተል እና ወደ ጌታ መፀለይ ጀመረች፡፡ የሆነ ያልተለመደ ሁኔታ እንደተፈጠረ ገብቷታል፡፡

በኋላም ሙዚቃው ፀጥ ሲል የጥይት ተኩስ ድምፅ ሰማች፡፡ ልቧ ድው ድው እያለች "ኢድነኝ ኢየሱሴ" እያለች ስትጮህ አንዱ ሰውዬ ከመፀዳጃ ቤቱ በራፍ አጠገብ ወለሉ ላይ ሲወድቅ ታወቃት፡፡ ከዚያም ደሙ በበሩ ስር አልፎ ወደ መፀዳጃ ቤቱ እንደ ውሃ ይፈስስ ጀመር፡፡ ያኔ ታዲያ "በኢየሱስ ስም" ብላ ጮሃ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደገና የተኩስ ድምፅ አካባቢውን ስለ ሞላው ማንም ድምጿን አልሰማትም እንጂ፡፡ ልክ ነብዩ "ጠላት ሲያጠፋሽ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ጣልቃ ገባ" ሲላት ወዲያው ነበር ሁለት ሰይፍ የታጠቁ መላእክት እርሷን ለመጠበቅ መፀዳጃ ቤቱ በር ላይ የቆሙት፡፡

ያ መፀዳጃ ቤቱ በር ላይ የወደቀው ሰው ከወንበዴዎቹ አንዱ መሆኑን ፖሊሶች ከመጡ በኋላ ስትወጣ ነበር ያየችው፡፡ በእጁቹ መሳሪያ ይዞ ነበር፡፡ ልክ ጓደኛው ሊገድለው ባሰበበት ቅፅበት እርሱ ደግሞ ሽንቱ መጥቶ ስለነበር እና መፀዳጃ ቤቱ ውስጥ ምናልባት ሰው ሊኖር ይችላል ብሎ እያደባ ወደ መፀዳጃ ቤቱ እየቀረበ ስለነበር በጓደኛው ጥይት ተመትቶ የወደቀው እዚያው መፀዳጃ ቤቱ በር ላይ ነበር፡፡

በኋላም ፖሊሶቹ ልጅቱ ሰላማዊ እንደሆነች ከተረዱ በኋላ በህይወት የተረፈ ሰው መኖር አለመኖሩን ሲያጣሩ አንድ ኢትዮጵያዊ ተመትቶ ወድቆ ህይወቱ እንዳላለፈች አረጋገጡ፡፡ ይህንን ሰው ተጋግዘው ከተደፋበት ቀና ሲያደርጉት በድንገት "ምን ሆኗ ነው?" በማለት በአማርኛ ሲናገር ሰምታው ደንግጣ ወደ እርሱ ስትጠጋ ፍፁም ጤነኛ በሚመስል መልኩ "የታል ሃብሌ? የታል ሃብሌ?"

ትንሳኤ ሙታን ባይኖርማ እኔም መውረድ እና ሰው መሆን፤ መቁሰል፤ መሰቃየት፤ መሰቀል፤ መሞት እና መነሳት ከዚያም መመለስም ባላስፈለገኝ ነበር፡፡ ገነት እንገባለን ብለው ሰዎች ብዙ ሃይማኖትን ባልፈጠሩና ባልሳቱም ነበር፡፡ በሩ እኔ ነኝ በእኔ በቀር ሌላ መግቢያ የለም ብዬ በተደጋጋሚ ተናግሬያለሁ፡፡ ማንም የራሱ ፅድቅ ወደ መንግስተ ሰማያት አያስገባውም አለኝ፡፡

## ታዋቂው ኢትዮጵያዊ ዳንኪረኛ

አሁንም ጉዟችን በሲኦል ውስጥ ቀጥሏል። ለቅሶ እና ጭይታ ከየቦታው ይሰማናል። የሰው ልጆች የሲቃ ድምፅ አካባቢውን ሞልቶታል። ከዚያም ወደ አንድ ጉድጓድ ቀረብን። በዚያም ጉድጓድ ውስጥ ጌታ ታዋቂውን ኢትዮጵያዊ ሙዚቀኛ ከብዙ ግብረ አበሮቹ ጋር በእሳት እየነደደ አሳየኝ። "ይሄንን አውቅሽውን በደሜ ላይ የቀለደ በህይወት ዘመኑ ሶስት ጊዜ 'አንተን ተቀበልኩህ' ብሎ ነገር ግን እንደበላንና ልቡን ለሰይጣን መጠቀሚያ መሳሪያ ሸጦ ብዙ የኢትዮጵያ ሰዎች እንዲስቱ ምክንያት መሆኑ ሳያንስ በዘመኑ ሁሉ በየጠንቋይ ቤቱ ሲዞር ኖሮ የነሰሃ እድል ተከልክሎ ቢድንገት ልቡ በመቆሟ ለሞት ቢቃ። ለዚህ ነው እዚህ ሲኦል ውስጥ እግሩ እንደተቆረጠ የሚሰቃየው አለኝ።

በምድር ሳሉ አካለ ጎዶሎ የነበሩ ሰዎች በሲኦል ውስጥም አካለ ጎዶሎ ሆነው ነው የሚኖሩት። በዚህ ሁኔታቸውም በሲኦል አላያቸው ላይ እሳት እየነደደ ይጮሁ ነበር። እየተመለከትሁ ሳለ የራሱን የወጣትነት ምስል የመሰለ መልከ መልካም እና እፍሮ የሆነውን ገፅታውን የሚመስል ከፉ መንፈስ ቆሞ ጎፈሬውን እያበጠረ በራሱ ይሳለቅበት ነበር። ታዲያ ፊቱ ፍም መስሎ "ሰራህልኝ አይደል?" እያለ በቂጡ ሲንፏቀቅ እና አንዳንዴም በደረቱ የተቆረጠ እግሩን እያወራጨ ሲሳብ ተመለከትሁት።

ወዲያውም በምድር ላይ ዘፈኑ ሲከፈት ሀሊናው እየደማ ማልቀስ ጀመረ። ከዚያም የእሳት ዲን በላዩ ላይ ያለማቋረጥ ይዘንብበት ጀመር። ብዙ ታዋቂ የሆኑ የኢትዮጵያ እና የሌሎች አገራት ዘፋኞችንም በዚህ ስፍራ በእሳት እየተቃጠሉ ተመለከቻለሁ። ከዚያም እንዲህ አለ "ምነው ከነሙሉ አካሌ በሞትኩ! ለምን እግሬን አስቆረጡኝ" እያለ ማባሪያ በሌለው ዐዐት እርግማን ማውረዱን ተያያዘው።

በእንደዚህ ዓይነቱ ፕሮግራም ላይ ለመገኘት ብዙ ሴት እና ወንድ ሞዴሎች መማለጃ እስከመስጠት የሚደርስ ደጅ ጥናት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ አብዛኛዎቹ የከተማዋ ሞዴሎች የገቢ ምንጫቸው እንደዚህ ካሉ አርከሰቶች በመሆኑ እጅግ የተንቆጠቆጡ መኪኖች ይነዳሉ፡፡ ዘመናዊ አልባሳትን ይለብሳሉ፡፡ ምክንያቱም ይህ ሰው ወደ ጭፈራ ቤቶቹ ከገባ ለእያንዳንዱ ሰው የማይታመኑ ብዙ ብሮችን ይሰጣል፡፡ ይህ ከፉ ስነምግባርም በምድራቱ ላይ እንዲበዛ ምክንያት የሆነው እርሱ ነው፡፡ ትልልቅ ባለስልጣኖችን በመያዝ ምድራቱ እንዳትባረክ ብዙዎችን ሲበዘብዝ ነው የኖረው፡፡

በከተማው ውስጥ የሚገኙ ጥሩ ጥሩ ቦታዎችን ከመንግስት በመውሰድ ባያለማ ይልቁንም ገንዘቡን በውጪ ባንኮች ነው የሚያስቀምጠው" ብሎ ጌታ በቁጣ እና በንዴት ተሞልቶ ወደ ምድር ሲመለከተው ሰውዬው መንገጭላ ልክ በእሳት እንደሚሸሽ ፈሲታል ሆኖ በቤተሰቦቹ ተገልሎ ዊልቸር ላይ ተቀምጦ ገንቦች እና ትንኞች በአፉ እና በአፍንጫው ሲገቡ እና ሲወጡ አየሁ፡፡ በመንገድ ዳር ሞቶ ሁለት እና ሶስት ቀን እንደቆየ አስከሬን ከዚህ ሰው የሚወጣው መጥፎ ሽታ አካባቢውን መጥፎ ጠረን እላብሶት ሰዎች ወደ እርሱ መቅረብ እስከማይችሉ ድረስ ሆኖ ነበር፡፡

# የአስቆሮቱ ይሁዳ

ወደ ሌላኛው ክፍል ስናልፍ የአስቆሮቱ ይሁዳን እንዲሁ በሚንገዋገወው ጥላ መሳይ ምጣድ ላይ ተጥዶ ጭሱ ከእርሱ እስኪወጣ ከስር የሚንቦገቦግ እፍላል ከላይ ደግሞ የእሳተ ጎሞራ አይነት ፍም በላዩ ላይ ይወርድበት ነበር:: ጌታን ሲያይ እሪታውን ለቀቀው:: ከዚያም "መሲሁ ቢታኝ ተተጣሁ አባክህ አራራልኝ፡ በእነዚያ ንፁህ ፍቅር በተሞሉ ዓይኖችህ እዮኝ እባክህ:: ልለምንህ አሁን ቢታ ተቀጥቻለሁ" እያለ ሳለ ጌታ ብሩህ ፊቱ ላይ ሃዘን ሲያጠላበት ተመለከትሁ:: እንባ በጉንጮቹ እየወረዱ በናፍቆት አይን ያነባ ጀመር::

ድምፁንም አውጥቶ ስትስቅ ብሎ እለቀሰ እና እባካችሁ በሚጠፋው ገንዘብ ነፍሳችሁን ለማትገዙበት ንፁህ የሆነውን ፍቅሬን አትለውጡት ብሎ ወደ ይሁዳ እያየ ይህ ሰው ከተከተሉኝ ሁሉ ይልቅ እወደውና እንከባከበው ነበር:: በጠላት ወጥመድ እንዳይገባም አሳስበው ነበር:: ነገር ግን እርሱ ከእኔ ፍቅር ይልቅ የገንዘብ ፍቅር ሲያይልበት ስመለከት ሁሉ መጨረሻው እየታየኝ አለቅስለት ነበር:: ብመከረውም ምክሬን ሁሉ ችላ ብሎ ላይጠቅመው ሸጠኝ:: ያም ሳያንሰው የሆዱን በሆዱ አድርጎ ገዳዮቹን መርቶ አምጥቶ ሮጦ መጥቶ እንደ ጥንቱ አንገቴ ላይ ተጠምጥሞ ጉንጬን ሳመኝ:: ግን እስኪ አስበው ያሳደግኸው፣ የምትወደው፣ ያስተማርኸው፣ ከእጅህ የበላ፤ የሞት ድግስ ደግሶልህ ለመግደያህ ምልክት አድርጎ የውሸት ፍቅሩን የውሸት መሳም ቢስምህ አለና በእንባዎቹ ጉንጮቹ ራሱ::

ይሁዳ እዚህ ይገባ ዘንድ የእኔ ፍላጎት አልነበረም፤ የከፋው የሰይጣን እንጂ:: ሰይጣን በሀሳቡ በድክመቱ መጥቶ ስለ ወደፊቱ እያሰላሰለ ሳለ 'ለምን እርሱን ሸጠህ የወደፊት መኖሪያህን መሬት አትገዛም' ብሎ ደግ አሳቢ መስሎ ሃሳብ ሲሰጠው ይሁዳ አፍቅሮተ ንዋይ ነበረበትና ይህንን የሰይጣን ሃሳብ

አልነቃበትም። ዛሬም 'በአቋራጭ የሆነ በረከት ታገኛለህ' እያለ እንደ ይሁዳ ብዙዎችን ወደ ሲኦል ከሚያመጣበት ስልቱ አንዱ ይሄ ነው።

ስንቱን ነው ዝረፉ እና መኪና ግዙ እያለ መኪናዎቹን ገልብጦ ለዘላለም ወደ እሳት የሚጥላቸው ስንቱን ነው ስረቁ ብሎ ሲሰርቁ በጥይት አስገድሎ የሚያመጣቸው ስንቱን ነው ጉቦ እንዲወስዱ ሃሳብን በልባቸው እምጥቶ እንደገና አስጠቁሞ ህይወታቸውን በእስር ቤት እንዲያሳልፉ የሚያደርገው ከዚያም ቤተሰባቸው ሲበተን እራሱን እንዲያጠፉ ሌላው ሌላውን እንዲያጠፉ እያደረገ ሃሳብ ወደ ልቡ እየከተተ የፈጀው" እያለኝ ጥቂት እንደሄድን አንድ ትልቅ ሰውዬ አሳየኝ። "ታውቀዋለህ?" ሲለኝ አውቅሁት "አዎ" አልኩት "አየው ይህንንም ሰው 'ሚስትህን ግደላትና እራስህ ሙት' ብሎ ከፉው ሃሳብ በልቡ ይከትብታል ከዚያም ሚስቱ የሞተች መስላው ስትወድቅ እርሱ ጭንትላቱ ላይ እንዲተኩስ አድርጎ ይገድለዋል። ባለቤቱ ግን እስከ አሁን ድረስ በህይወት አለች፤ እርሱ ግን በእሳት እየተሰቃየ ነው" አለኝ።

-እንዳይመጡብኝ እለምንሃለሁ" ብዬ ስለው "ማንም እዚህ ሰፍራ ይመጣ ዘንድ የእኔም የአባቴም ፍቃድ አይደለም። ነገር ግን ሰው በገዛ ፍላጎቱ ነው በምርጫው ምክንያት ወደዚህ የሚመጣው" አለኝ።

እንዲህም አለኝ "ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤ እናንተ ደካሞች ሸክም የከበደባችሁ ወደ እኔ ኑ እኔም እሳርፋችኋለሁ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና። ለነፍሳችሁም እረፍትን ታገኛላችሁ። እውነት እውነት እላችኋለሁ እመኑኝ ቃሌን የሚጠብቅ ለዘላለም ሞትን አያይም። እኔ መንገድም ህይወትም እውነትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔ የአለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝም የህይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም። እኔ እዳኝ እንደሆንኩኝ ባታምኑ በሃጢያታችሁ ትሞታላችሁ ብለህ ንገራቸው" አለኝ።

እንዲህም አለኝ "እናንተ በመፅሀፍት የዘላለም ህይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋል ስለዚህም እነርሱን ትመረምራላችሁ። እነርሱ ግን ስለ እኔ የሚመሰከሩ ናቸው። ነገር ግን ህይወት እንዲሆንላችሁ ከዚህ ከከፉ ሰፍራ እንድትድኑ ወደ እኔ ኑ ተመለሱ። የሚያምነብኝን ቢሞት እንኳን ህያው አደርገዋለሁ። እባካችሁ የሰው ልጆች ሆይ ዛሬም ድምፄን ስሙ። ከሚመጣው ቁጣ በእኔ በማመን ትረፉ እያምልጡ በላቸው" አለኝ።

ከተማረ ሰው እስከ ተራ ሰው ድረስ ሁሉም ሰው ለእርሱ የተመደበ አርኩስ መንፈስ ይከታተለዋል።

እነዚህ አርኩሳን መናፍስት አንዳንድ ጊዜ የሚተያየሩ ሲሆን ይህንን በማያደርጉ ሰዓት ስለሚከታተሉት ሰው መረጃ ይለዋወጣሉ፤ ሪፖርት ይደራረጋሉ። በመቀጠልም ሰይጣን ሊላኛው ግድግዳ ላይ በእስክሪን ውስጥ ራቁታቸውን የሚጨፍሩ ሴት መሳይ መናፍስትን እጅግ ወሲብ ቀስቃሽ የሆነ ዳንስ ሲደንሱ ማሳየት ጀመረ። ይህንን ጊዜ ሰይጣን እጅግ ተደሰቶ እነዚህን መናፍስት ወደ እርሱ ጠርቶ ብዙ ሀይል አስታጠቃቸው።

እነዚህ ሴት መሰል መናፍስት በኋላም በየአውቶቡስ ጣቢያው፤ በአየር ማረፊያዎች፤ በወደቦች እና በባቡር ጣቢያዎች ቆመው ልክ ከትራንስፖርት የሚወርዱ ሰዎችን "አሁን እኮ አንተን የሚያውቅህ ሰው የለም ከአንዱ ቆንጆ ጋር ዝሙት አድርግ፤ ጠጣ" እያሉ ፓስተሮችን እና አገልጋዮችን ሳይቀር እንዲያስቱ ተልከው የግብረሰዶም እና የዝሙት እንዲሁም የመጠጥ እና የጫት መንፈስን እንዲያሰራጩ በሀይል ተሞሉ።

በነገራችን ላይ እነዚህ ሴት መሰል አርኩሳን መናፍስት በስጋ እንደ ሰው መገለጥ ይችላሉ። እኔና ጌታ ከአርኩሳን መናፍስቱ ጀርባ ለመድረስ ትይዩ ሆነን ነበር ሁኔታውን የምንመለከተው። ሆኖም ግን እኛ እናያቸዋለን እንጂ እነርሱ እኛን ማየት አይችሉም ነበር። ከዚያ በኋላ ደግሞ ወንድ እና ሴት የምድራችን ዲዛይነሮች ዲዛይን ስለሚያደርጉት ሰይጣናዊ አልባሳት በጥልቀ ስልጠና ተሰጣቸው፤ ሀይልም ተሞሉ።

አልባሳቱ ዲዛይን የሚደረጉትም ለወንድም ሆነ ለሴት ወሲብ ቀስቃሽ እንዲሆኑ ታስቦ ነው። ሌሎች መናፍስቶች ደግሞ በሴቶች አዕምሮ ላይ ሆነው ራቁታቸውን ለመሄድ እስኪመኙ ድረስ የሚገፋፏቸው ሆነው ሀይል ተቀበሉ። ተተናኛተውም የጌታን ተከታዮች ኢላማ እንዲያደርጉ ተነገራቸው።

እንደፈለግን መንቀሳቀስ እና መስራት አትቀናል። በአየር ላይም ሆነ በውስጥ ያሉ ኤጀንቶቻችን እየተወረሱ እና በእርሱ ሰዎች የእኛ የነበሩ ጠንቋዮች በነቢያቱ እየተበሉጡ ተከታዮቻቸውን በሙሉ እያጡ ነው" በማለት ተናገረ።

በነገራችን ላይ ሰይጣን የኢየሱስን ስም መጥራት ስለማይችል እርሱ እያለ ነው የሚጠራው። ለምን ቢባል ስሙ ሃያል ስለሆነ እና ስሙን መጥራት በራሱ ላይ አደጋ ስለሚያመጣበት ነው። ንግግሩን በመቀጠል ሰይጣን እንዲህ አለ "የመሃመድ ተከታዮችም እየፈለሱ ወደ እርሱ እየገቡ ነው። ምን እየተሰራ ነው ብዙ ሙተተኞች ከየአለማቱ ብንልክም 'መስራት አቃተን' እያሉ አገራቱን ጥለው እየወጡ ነው። የአፀድ አምላኪዎችም እየቀሩ ነው። ነባሯ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንም እንደገና በተሃድሶ ወደ እርሱ እየተመለሰች ነው። ስራችን ከሰሯል" በማለት ሰይጣን እንደ እሳት በቅናት ሲቀላ ተመለከትሁ።

"ስለዚህ አዲስ እቅድ ነው የሚያዋጣው" አለ ሰይጣን "ደግሞ እኮ ሁለት ነብያቶች ናቸው ያቃቱን። ለምን እነርሱን በሴት አታጠምዷቸውም?" ብሎ ሲል ከእርኩሳን መናፍስቱ አንዱ "ኸረ እነርሱ ፈፅሞው ትዳር እንኳን አይፈልጉም፤ ብዙ ጊዜ ሞክርን ሆኖም ግን አልቻልንም አለ።" ጌታም እነዚያ የተባሉትን ሁለት ነቢያት ከምድር ላይ ሲያሳየኝ አንዱ እኔው እራሴው ነበርሁ። ከዚያም ደንግጬ የራሴን አካል እየደባበስኩ "እንዴ ጌታ ሆይ" ብዬ ወደ ጌታ ስመለከት ጌታም ፈገግ ብሎ "ያንኛው ወደፊት ያለው ማንነትህ ነው። ነገር ግን አንተው እራስህ ነህ፤ ለዚህ ነው እኮ የማስጎበኝህ። ነገም ትላንትም በእኔ ፊት ዛሬ ነው። መጀመሪያውም መጨረሻውም እኔ ነኝ። ለዚህ ነው በምድርህ ኢትዮጵያ ለማንም ነብይ እና ባለራዕይ ተገልጬ በማላውቅበት መንገድ ለአንተ እየተገለጥኩልህ ያለሁት አለኝ። ለሌላኛው ነብይ ማንነት ስጠይቀውም "ያንን ደቡብ አፍሪካ ወስጄ ያሳየሁህን ታሪክ አስታውስ" አለኝ።

ማንም ትንቢት ቢኖረው፤ ያለውን በሙሉ እንኳን ለድሆች ቢለግስ፤ በልሳን ቢናገር፤ ወሩን ሙሉ ቢፆም ቢያሳልፍ፤ ፍቅር ግን ከሌለው ከንቱ ነው፡፡ ድካሙን እና ልፋቱን በተነ ማለት ነው፡፡ ለመሪዎች እንዲህ በላቸው ህዝቡን እርስ በእርሱ የሚያስተሳስሩ የቤት ለቤት ፕሮግራሞችን አብዙ፡፡ ሕዝቤ ፍቅር በማጣት በጠላት እየተመታ ነው፡፡ እናንተም ለሰው ፊት ሳታደሉ ፍቅርን ለግሱ፡፡

እኔን ከሆነ የምታገለግሉት እኔ ፍቅር ግድ ብሎኝ ነው ከዙፋኔ ያወረደኝ፡፡ በህዝቤ ፊት መሪ እድርጌ ብሾማችሁ እናንተ ግን ልባችሁ በጥበባችሁ ላይ ከወደቀ እጥርዳችኋለሁ፡፡ ባለ እደራዎች እንጂ ባለቤቶች አይደላችሁም፡፡ በዝና ቃንቃችሁ ብትፆሙ፤ ብትፀልዩ፤ ብትሰብኩ፤ ብትተነብዩ፤ ብትሰጡ፤ ለሁሉም ሰው የሚሆን ፍቅር ከሌላችሁ ልንገራችሁ ከንቱ ናችሁ፡፡ ይህንን እያወቃችሁም እንታዘዝም ብትሉ እጥርዳችኋለሁ፡፡ በአደባባይ ገመናችሁን እገልጣለሁ፡፡

ይህ ትምህርት ከእኔ አይደለምና ቅኑ በፍቅሬ ኑሩ፡፡ በቤቴ የእኔ ምሳሌዎች ናችሁ፡፡ ገርነታችሁ ለሰው ሁሉ ይታወቅ፡፡ ይህንን ስታደርጉ ፀጋዬ እለት እለት ይበዛላችኋል" አለኝ ጌታ፡፡ ሰይጣንም ንግግሩን ቀጥሎ "ተበልጠናል እጅግ ተበልጠናል፡፡ አዳዲስ እስትራቴጂዎችን መንደፍ አለብን" በማለት በብስጭት አዲሱን እስትራቴጂ ማንበቡን ቀጠለ፡፡ "በአሜሪካውያኑና በአውሮፓውያኑ ትከሻ እስራኤልን በቴክኖሎጂ ሜፍ ላይ ማስቀመጥ አለብን፡፡ ቀጣዩን ትውልድ የምንዋጋበትን መንገድ ከዚያ ነው የምናገኘው፡፡ በሚቀጥሉት ሃምሳ አመታት ሁሉንም የሰው ልጆች ከሃዲ ማድረግ አለብን፡፡ ይህንንም በሙከራ ደረጃ በአውሮፓ እና በአሜሪካ በሚገኙ ወጣቶች ላይ ተግባራዊ አድርገነዋል፡፡

በመጀመሪያ ሰው ከመካዱ በፊት በዝሙት እንዲወድቅ ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም የፖርኖግራፊ ሱሰኛ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ እንደምታውቁት ሰው ዝሙት ሲሰራ ለማይረባ አዕምሮ ተላልፎ ይሰጣል ይላል ቃሉ፡፡ ይህን እድል ነው ሁሌም መጠቀም ያለብን፡፡ ሰው ለማይረባ አዕምሮ ከተሰጠ ደግሞ ሲጋው በላዩ

ላይ የበላይነትን አገኘ ማለት ነው፡፡ ሲጋው የበላይነት ካገኘ ደግሞ ግብረሰዶም ማድረግ ይቻላል፡፡ ከዚያም ግብረሰዶማዊነት በትምህርት ፖሊሲው ላይ፣ በፖለቲካው ውስጥ፣ እንዲሁም በቤተክርስቲያን ተቀባይነት እንዲያገኝ ማድረግ፡፡ ይህ ስልት በአሜሪካ እና በአውሮፓ ዘጠና በመቶ ስኬታማ አድርጎናል፡፡ በዚህ ስልት የቤተክርስቲያን ፓስተሮችን ባዶ ሕንፃ እና ባዶ ወንበሮች አሲታችፈናቸዋል የሚሄድ የለም፡፡ ካለም አሮጊት እና ሽማግሌው ነው፡፡ እነርሱም አልፎ አልፎ ነው የሚሄዱት፡፡

ስለዚህ በዚህ እስትራቴጂ ማዕቀፍ ስር ወደፊት መያዝ ያለባቸው አፍሪካውያን ናቸው፡፡ በዚህ እስትራቴጂ መመታት አለባቸው፡፡ አፍሪካውያን ገና ከድህነት ሳይወጡ እርዳታ የሚያገኙበትን ገንዘብ በመያዝ የአውሮፓ እና የአሜሪካ ፖለቲከኞች እንዲያወጡ ያደረግነውን የአመፅ ህግ፣ መንግስቶቻቸው በግዳጅ እንዲቀበሉ ማድረግ፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ ውስጥ ውስጡን በፊልሞች እና በኢንተርኔት በፈሰቡክ ፖርኖግራፊን በማስፋፋት ክርስቲያኖች ለትዳራቸው ታማኝ እንዳይሆኑ በማድረግ ወጣት አገልጋዮችን እራሳቸውን በገዛ በማርካት ሱስ እንዲጠመዱ በማድረግ አገልግሎታቸውን ማሰነካከልና በባለትዳሮች መካከል ግጭትን በማብዛትና በማለያየት ግብረሰዶማዊነትን በማስፋፋት ህዝቡን ከአምላኩ ጋር እንዲጣላ በማድረግ ባገኘነው ምቹ አጋጣሚ በተሰፋ መቅረጥና በተለያዩ በሽታዎች መምታት፡፡

በኑሮ ረገድ ፈጣሪ ለአፍሪካ በረከትን ከዚህ በኋላ ሰለፈቀደ ይህንን ማስቆም አንችልም፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ያሉ ክርስቲያኖች መሪዎቻቸው መለኮታዊ ሀይሉን እንዳያምኑ ማድረግ፡፡ ቢያምኑም በተግባሬ እንዲኖሩ ማድረግ፡፡ ከዚያም አሰደናቂ እና አሰቂኝ የሆኑ ትምህርቶችን እንዲያስተምሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

ቶሀም ከአዘመራው ብዙ ምርት ወደ ጎተራ እንዳስገባ ገበሬ ሰይጣን ሲያኩራራው ተመለከትሁ።

ሌላው ደግሞ ሲኦል በምትገኝበት ምድር ውስጥ ልክ እንደ ሰው እግሮቿን፣ እጆቿን እና እንገቷን በራሱ በዲያቢሎስ እርዳታ ለማንቀሳቀስ ስትሞክር በምድር ባሉ ሰዎች ላይ የምድር መናወጥ ሆኖ እጅግ ብዙ ህዝብ ሲያልቅ ተመለከትሁ። ሰይጣን በተለያየ ወቅት ሆን ብሎ ይህንን ያደርግ ነበር። ይህ ደግሞ ሌላው ውጤታማ አዝመራው ነበር። እየተመለከትነውም እራሱ ሰይጣን ከሲኦል ወጥቶ በአየሩ ላይ ይበርና የተለያዩ አውሎ ንፋሳትን ያስነሳ ነበር። እንዳንዴም ደመናዎችን ወደ አንድ ቦታ ከአየሩ ላይ በመሰብሰብ በዝናብና በአውሎ ንፋስ ሰውን በጅምላ ለመጨረስ ይፈገን ነበር። በአጠቃላይ በየቀኑ ያጋጠመውን ምቹ ሁኔታ ሁሉ ተጠቅሞ ሰዎችን ወደ ሲኦል ለመውሰድ ይጣደፍ ነበር። ይህ ሁሉ ከፋቱ ግን ብዙ ጊዜ አይሳካለትም ነበር።

ይህ የሰይጣን እቅድ የማይሳካባቸው ሁለት ምክንያቶች ናቸው። አንዱ መንፈስ ቅዱስን ሲያይ ስለሚሸሸና እየተሸሎከለከ ስለሚደበቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ቅዱሳኖች ይህንን ድርጊቱን በመንፈስ ቅዱስ ህይወታቸውን በቅድስና ጠብቀው በመንፈስ እየተመሩ ሲያፈርሱት ነው። እንዳንዴ አንድ ሰው እንኳን በጌታ በኢየሱስ ስም ብሎ በመንፈስ ተሞልቶ ሲቃወም በአለም ላይ ያለውን የሰይጣንን እቅድ እና ስራውን ሲያፈርስበት እና ሲያከሽፍበት እንደሚችል ጌታ ነገረኝ።

በመቀጠልም ጌታ ወደ ሰሪያ ወሰደኝ እና በዚያም ሁለት ተፋላሚ ሀይሎችን ተመለከትሁ። ሁለቱም ሀይሎች ባላቸው አቅም ሁሉ ሰይጣን በሸረበው ሴራ እርስ በእርስ ለመጠፋፋት ተዘጋጅተው ነበር። በአየሩ ላይም በጥንብ አንሳ መልክ መናፍስቶች ከእነርሱ እጥፍ ሆነው ተዘጋጅተው ነበር። ወዲያውም

ጦርነቱ ተጀመረ፡፡ ከዚያም እያንዳንዱ ወታደር ላይ እነዚህ መናፍስቶች እንደ ፈረስ ተቀመጡባቸውና ይጋልቧቸው ጀመር፡፡

እየጋለቡ ወታደሩ ወደ ፊት እየተኮሰ እንዲሮጥ ያደርጉት ነበር፡፡ በሁለቱም ወገን ሆነው በሚዋጉት ሰራዊቶች ላይ ነበር እነዚህ እርኩሳን መናፍስት የሚሳፈሩባቸው፡፡ አንድ ወታደር ደግሞ ደጋግሞ በሚመታው ጥይት እየሮጠ ተዝለፍልፎ ሲወድቅ እና ሲሞት ሌሎች እርኩሳን መናፍስቶች ነፍሱን ወደ ሲኦል እያካለቡ ይወስዷት ነበር፡፡ ጋላቢዎቹ መናፍስቶች ግን አንዱ ሲወድቅባቸው ሌላ ሰው ላይ ይሳፈሩ ነበር፡፡ በሁለቱም ወገን እየተቀያየሩ ይሄንኑ ተግባራቸውን ይፈፅሙ ነበር፡፡ ይሄንንም ያለማቋረጥ ያከናውኑ ነበር፡፡

ጌታም "አይ የሰው ልጅ ተላላ ነው አያስተውልም፤ ተመለከትክ፤ መናፍስቶቹ አንድ ናቸው" አለኝ፡፡ እነዚህ አዋጊ እርኩሳን መናፍስት ሁሉንም ሰው ካስጨረሱ በኋላ እየተሳሳቁ ለሰይጣን ሪፖርት ለማድረግ ሲሄዱ ተመለከትን፡፡ የብዙ ሰዎች እስከሬን እዚህም እዚያም ወድቆ ነፍሳቸውም ወደ ሲኦል ተወስዶ ነበር፡፡ ወዲያውም መናፍስቶች ሪፖርት ካደረጉ በኋላ ብዙ ከፋትን ጨምረው ወደተለያዩ የአለም አገራት ለተመሳሳይ ተግባራት በምድር ሁሉ ተረጩ፡፡

ሌሎች ልክ እንደ አክራሪ እስላም ፊታቸዉን በጥቁር ጨርቅ ጥቁር የአሸባሪዎች ባንዲራ ይዘው በአረብኛ ፊደል ድግምት ያለበት ሀይል የሌለው ግን ባዶ የሆነ እጅግ በዉሸት የተሞሉ ተንኮለኛ መናፍስቶችን አሰልፎ የመሀመድን ፊት ሚካፕ ያደረገ አንድ እጅግ ጨካኝ እርኩስ መንፈስ ከአርሱ የከፉትን መናፍስቶች እየመራ ከሲኦል ማህፀን አሸባሪነትን እና አክራሪነት ቀድቶ ወደ አዳራሹ ገባ፡፡ ያኔ ሰይጣን ከተቀመጠበት በመነሳት የለበጣ በሆነ ሳቅ ፈገግ ካለ በኋላ በተጠንቀቅ በፊቱ የቆመውን መንፈስ ተነስቶ በጥፊ መታውና ንግግሩን ቀጠለ፡፡ "ብዙ አስትራቴጂህ እየተነቃብህ ነዉ፡፡ ብዙ የምድር መንግስታት ከእኔ በወሰዱት ጥበብ ስራህን እያፈረሱብህ ነዉ፡፡ አልቻልከም እየተነቃብህ ነዉ፡፡

አዳዲስ እቅዶች የሉህምና ለነገሩ ተወዉ እኔ አንድ አለኝ በማለት ከፋት ለማፍለቅ ከማይሰለቸዉ አእምሮዉ "ያ ቅዱስ መጽሀፍህ አለ" ብሎ ፈገግ አለና "አይደል እንዴ? በመግደል ገነት ትገባላችሁ የሚለዉን አንድ አትጠቀምበትም? ከእርሱ ተከታዮች ጋር አብረዉ ተከታዮችህ እንዳይኖሩ፤ እንዲገድሏቸዉ፤ እንዲዘርፏቸዉ፤ እንዲያርዷቸዉ፤ በጅምላ ሰዎችን እንዲፈጁና እንዲያሸብሩ ከዚያም አለምን ከእርሱ ተከታዮች እንዲያፀዱት፤ ከዚያም አኔ ብቻ ንጉስ ሆኜ በእያናሳሊያም የምመለከበትን ጊዜ ማምጣት ተሰኖሃል::

ስለዚህ አሁን ሂድና የአንተን ተከታዮች የሀብት ምንጫቸዉን ገቧ እርስ በእርሳቸዉም እንዲተላለቁ አድርግ:: በክርስቲያን የአፍሪካ አገሮች ላይ ሽብርን አከናዉን:: አሁን ያንተ አቅድ አልተሳካም:: ተከታዮችህን አጥፍቶ ጠፊ አድርጋቸዉ:: በተመረጡ ታላላቅ የገበያ ቦታዎች፤ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች፤ ቤተክርስቲያኖች፤ ወዘተ ባላደጉ አገሮች ደግሞ  በገንዘብ በማታለል በማስለም ሰራተኞችን ከክርስቲያን አገሮች በመዉሰድ ልጆች እንዲወልዱ በማድረግ እንደ ከዚህ ቀደሙ ተከታዮችህ ብዙ ሰዉ እንዲወልዱ አድርግ:: ስለጠንን የሚሉትን ተከታዮችህን አጥፋ አትራራ:: ወደ ስልጣኔ እንደይገቡ ከልክል:: ፍርሃትን እና ሽብርን በምድር ነዋሪዎች ላይ ንዛ ብሎ አጅግ ካሰቃየው በኋላ አበሳጭቶት ከብዙ በጀቶች ጋራ ወደ ምድር ላከው::

ያ ከቶ እርኩስ የእስልምና መንፈስም "አላሁ ዋኩበር" እያለ ሲጮህ ታከታዮቹም አብረውት ይጮኹ ጀመር:: ታድያ ጌታም እንዲህ አለኝ "አላህ ማለት ሰይጣን በመሃመድ ዘመን በመካከለኛው ምስራቅ የሀሃይና የጨረቃ አምላክ ነኝ ብሎ ይሰራበት የነበረ ስም ነው:: ስለዚህ ተከታዮቼ ፈፅመው ይህን ስም ለእግዚአብሔር መጠሪያነት እንዳይጠቀሙበት አሲታውቃቸው፤ አስጠንቅቃቸው" አለኝ::

እነዚያ መናፍስቶች እጅግ የተሳለ ካራ ይዘው ወደ ህዝቡ ገቡ፡፡ አብዛኛዎቹ ወደ ሙስሊም አገራት ነበር የሄዱት፡፡ ሄደውም እንደ ስልጣን ተዋረዳቸው በየሰዉ ላይ ከንጉስ እስከ ተራው ሰው ድረስ ተቆመጡባቸውና እንደ መኪና ይሾፍሯቸው ጀመር፡፡ ከዚያም እርስ በእርስ እንዳይስማሙ በማድረግ የማጥፋት ተልዕኳቸውን ይፈፅሙ ጀመር፡፡ ያ መንፈስም ወደተለያዩ አገሮች አጥፍቶ ጠፊዎችን እያሰለጠነ ይልክ ነበር፡፡ ለአንዳንዶቹ እኔ የአላህ ነብይ መሃመድ ነኝ እያለ እየተገለጠ ሕይወታችሁን እንኳን መሰዋእት ብታደርጉ በገነት እኔ እቀበላችኋለሁ እያለ እራሱን ልክ የእግዚአብሔር የቅርብ አማካሪ አድርጎ በተዘዋዋሪ ሳይጣንን ማስመለኩን ቀጠለ፡፡ ወደ አውሮፓ ወደ አፍሪካ እንዲሁም ወደ ተለያዩ የእለም አገራት በመካ መዲና በመቀመጥ አጥፍቶ ጠፊዎችን ይልክ ጀመር፡፡

ወደየአገራቱ የሄዱት አጥፍቶ ጠፊዎች ሁሉ ግን አይሳካላቸውም ነበር፡፡ በብርቱ የሚፀልዩ ክርስቲያኖች ባሉበት ቦታ ስራቸው ሲከሽፍና ምስጢራቸው ሲጋለጥ እመለከት ነበር፡፡ ግማሾቹም ሲያዙና ሲያብዱ ሁሉ አይ ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ ክርስቲያኖች ሰይጣን የሚሰራባቸው እስትራቴጂዎችን እየጠቆማችሁ በመቃወም ብትፀልዩ ጨለማ የሆነ ስራውን ማፍረስ ትችላላችሁ፡፡

ቀጥሎም ሌላ እጅግ ከፋትና ተንኮል የተሞላ የሞት አደጋዎችን የሚያቀነባብር እርኩስ መንፈስ መጣ፡፡ እርሱም ከሲኦል ማህፀን በተመሳሳይ አደጋና ድንገታዊ ከፋት የሚለውን ቀድቶ ወጣ፡፡ ይህ ከፉ መንፈስ በባህር ላይ የሚንቀሳቀሱና በምድር በመኪና የሚሄዱ ሰዎችን በማሳት በጅምላ ደም በማፍሰስ የታወቀ መንፈስ ነበር፡፡ እርሱም በተመሳሳይ ሰይጣናዊ ሃይልና ስልጣን ከተሰጠው በኋላ በከፋት ተሞልቶ ሰዎችን በጅምላ ለመጨረስ ያለ ርህራሄ ከሰራዊቱ ጋር አብሮ ወደ ምድር የተለያዩ የእለም አገራት ተሰራጨ፡፡ በተለያዩ እስትራቴጂዎች የተገለጡት እነዚህ እርኩሳን መናፍስት ሁሉ ለአላማቸው እየተረዳዱ ተናብበው እና ተመጋግበው በጥንቃቄ ነበር የሚሰሩት፡፡

# ሞቶ የተነሳው ብራዚላዊ

በዚሁ መንፈስ አተነባባሪነት አንዲት መርከብ በአትላንቲክ ውቂያኖስ ላይ እየተጓዘች ሳለች ከላይ ሰይጣን እራሱ ባስነሳው ማዕበል መናጥ ጀመረች፡፡ ካፒቴኑም መርከቡን ለማዳን ከማእበሉ ጋር መታገሉን ቀጠሉ ነበር፡፡ እዚያ መርከብ ላይ ክርስቲያን የሚል ስም የያዙ ብዙ ሰዎች ቢኖሩም ነገር ግን አንድ ብቻ እውነተኛ ክርስቲያን ነበር ከመሃከላቸው ያለው፡፡ እርሱ ደግሞ በመናፍስቱ እለም ስራቸውን በማፍረስ የሚታወቅ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው ብራዚላዊ ነው፡፡

መርከቧ ከሶስት እስከ አምስት ሺህ ሰው ጭና ከላቲን አሜሪካዋ ብራዚል ወደ ሰሜን አሜሪካ ነበር የምትጓዘው፡፡ በዚህ ጉዞ መሃል ውቅያኖስ ውስጥ ከማዕበሉ በሚደርስባት ግፊት ወደ ላይ እና ወደታች እየተናጠች ተጨንቃ ሳለ ከላይ በአውሎ ንፋሱ ከሌሎች መርከቦች ጋር የምትገናኝበትና የቴሌስኮፕ መመልከቻዋ ተነቃቅሎ በላይኛው የመርከቧ ክፍል የነበሩ ሰዎችን ጭምር ንፋሱ እንደ ወረቀት እያውለበለበ ሲወስዳቸው እንመለከት ነበር፡፡ የመርከቧ የላይኛው ክፍል በንፋሱ እየተነቃቀለ በላይዋ ተጭነው የነበሩትን ኮንቴይነሮች ሳይቀር እንደ ወረቀት እየነቃቀለ ከጣለ በኋላ ከስር በኩል ግማሽ አካሏ ተቀድዶ ውሃ ወደ ምተሩ ክፍል እየገባ ነበር፡፡

በመጨረሻም ምንም እንኳን ማዕበሉ ያቆመ ቢሆንም ነገር ግን መርከቧ ከደረሰባት አደጋ ማገገም አቅቷት ቀስ እያለች መስጠም ጀመረች፡፡ ይህን የተረዱት የመርከቡ ሰራተኞች እየተሯሯጡ ሰው ሁሉ በአየር የተሞላ ጃኬት እንዲለብስ ከሊቃ ማስቀመጫው እያወጡ ይሰጡ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎችም ይህንን የህይወት ማዳኛ ጃኬት ከለበሱ በኋላ ወደ ውቂያኖሱ እራሳቸውን እየወረወሩ ሳለ ያ ወንድም "ኢየሱስ አድነኝ" እያለ በተደጋጋሚ በመጮህ ወደ እግዚአብሔር ይጣራ ነበር፡፡

ይህ ሰው በብራዚል ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ከልጅነቱ አንስቶ እያገለገለ ካደገ በኋላ ትምህርቱን በከፍተኛ ውጤት አንደኛ በመውጣት ቢጨርስም ለእግዚአብሔር የአገልግሎት ጥሪ ምላሽ በመስጠት የሙሉ ጊዜ አገልጋይ በመሆን ጌታን ማገልገል ጀመረ:: በኋላም ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ሁልጊዜ በሀቀኝነትና ከእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር በመወገንና ብዙ በመፀለይ "የመፅሀፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ዛሬም ህያው ሆኖ ይሰራል፤ ቤተክርስቲያን ያለ መለኮታዊ ሀይሉ ያለ መንፈሱ ሙት ናት::" እያለ በመሞገት ይታወቅ ነበር። በኋላም ከቤተክርስቲያኑ በዚህ ሀሳቡ ቢገለልም እርሱ ግን "የእኔ ኢየሱስ ህያው ነው ዛሬም ይሰራል:: ታሪክ አይደለም" ብሎ ያምንና ያስተምር ስለነበረ ለብዙዎች አልተመቻቸውም ነበር:: በኋላም ሲፀልይ ሳለ ብዙ መገለጦች ይመጡለት ጀመር:: ይህንንም ለቤተክርስቲያን አገልጋዮች ሲነግራቸው ፈፅመው ተቃወሙት::

ከእለታት አንድ ቀን ጌታ አንተ እሰም አቀፍ አገልጋይ ነህ። ስለዚህ ወደ አሜሪካ ሄደህ እንግሊዘኛ እና መፅሃፍ ቅዱስ መማር አለብህ ይለዋል:: ለእግዚአብሔር ድምፅ ክብር የነበረው ይህ ወንድም ተነስቶ በመርከብ ተሳፍሮ ወደ አሜሪካ በዚህችው መርከብ ሲጓዝ ምንም አይነት ህጋዊ የሆነ የኢሚግሬሽን ወረቀት አልያዘም ነበር::

ፀልዮ ስለነበር የሲኪዩሪቲ ሰዎች እያዩት እንዳላዩት ሆነው ነበር:: እርሱ ግን ከአንድ ባዶ ከሆነ ኮንቴይነር ውስጥ ማታ ማታ እያደረ በጠዋት ከፀለየና ቃል ካነበበ በኋላ ወንጌልን ይመሰክር ነበር:: ቀኑን ሙሉ በመርከቡ ላይ ባለ የገበያ ሰፍራ በመዝናኛ ቦታዎች እየሔደ ስለ ጌታ ይመሰክር ነበር:: ብዙዎቹ ግን ቱሪስቶች ስለ ነበሩ እንደመዝናኛ ይቆጥሩት ነበር እንጂ የሚሰማው አልነበረም:: "የመዳን ቀን ዛሬ ነው!" እያለ ይሰብክ ነበር::

አንድ እለት በመርከቡ ላይ ባለ አንድ የመዝናኛ ሰፍራ የተዘጋጀ የሙዚቃ ኮንሰርት ብዙ ሰዎች እየተመለከቱ ነበር:: ታዲያ ይህ ወንድም ወደ መድረኩ

በመሄድ ከአስተዋዋቂው ማይኩን በመቀበል በመንፈስ ተሞልቶ "የመዳን ቀን ዛሬ ነው። ይሄ መርከብ አደጋ ቢደርስበት እንኳን እውነተኛው መርከብ ሊሰጥም አይችልም። ከሞት ፍርሃትና ከሲኦል አምልጡ። ኑ ወደ መርከቡ! ወደ ኢየሱስ ግቡና በኖህ ዘመን አለም ሁሉ በውሃ ሲጠፋ እንደተረፉ እንደ ኖህ እና ቤተሰቡ ጌታን አምናችሁ ከዘላለም ጥፋት ትረፉ" እያለ ሲነግራቸው ሳለ ህዝቡ ሁሉ የያዘውን እቃ ሁሉ፣ ሴቶቹ ጫማቸውን ጭምር እያወለቁ እርሱ ላይ በመወርወር "ውረድልን እንዝናናበት" እያሉ በስድብ ተሞልተው በቁጣ እየገፈታተሩ ከፖሊሶች ጋር ሆነው እየገፈተሩ ከመድረኩ ካወረዱት በኋላ ወደ እስር ቤት ወስደው አሰሩት። በዚያም ሳለ ምንም አይነት ትኬትም የመጓጓዣም ሆነ የኢሚግሬሽን ወረቀት እንደሌለው ስለተረጋገጠ ታስሮ እንዲጓዝ ተወሰነበት።

እዚያው በታሰረበት አንድ ቀን በልሳን ተሞልቶ በሃይል እየፀለየ ሳለ ከእርሱ ጋር ታስረው የነበሩ ብዙዎች ከነበሩባቸው በሽታዎች እና ከአጋንንት እስራት ነፃ ይወጡ ነበር። እስር ቤቱ ውስጥ እርሱ ሲገባ ሌሎች እስረኞች ይረበሹሉ በሚል ምክንያት ለብቻው በአንድ ክፍል እንዲቀይ አደረጉት። እርሱ ግን ማመስገኑን አላቆመም ነበር። በዚሁ ምክንያት ከላይኛው ክፍል ወደ ውስጠኛው ክፍል ገብቶ ነበር የታሰረው። ከዚህም የተነሳ የመጀመሪያው እውሉንፋስ እስረኞችንና መጀመሪያ የታሰረበትን ከላይ ያለውን እስር ቤት ጠባቂዎቹን ከነ ኮንቴይነራቸው ጠራርጎ ሲወስዳቸው እርሱ ግን ለብቻው ውስጥ ስለነበር የታሰረው ለመትረፍ ቻለ።

ሰዉ ሁሉ የህይወት ማዳኛ ልብስ እየወሰዱ ወደ ባህር ሲገቡ የመርከብ ጠባቂ ፖሊሶች በመርከቡ ላይ በተጫኑችዉ የሞተር ጀልባ ላይ እርስ በእርስ ሲጠራሩ የእርሱንም ጠባቂ ጠርተዉ ሲወስዱት ጠባቂዉም የእስር ቤቱን በር ሲከፍት ሁልጊዜ ሲፀልይ ያየዉ ስለነበር ያንን ወንድም በጀልባዋ አሳፍረዉት የመርከቡን ካፒቴን ጨምረዉ መርከቡንና ህዝቡን ጥለዉ ጀልባዋን አስነስተዉ ነጉዱ።

አልነበረም። ነገር ግን እንጀራን ብቻ የበሉ እንጀራ ሲያጡ ተርበው ሁሉም በመዛል በውቂያኖስ ሰምጠው ቀሩ። የሚዝናኑትም ሁሉ ህይወታቸው በሰይጣን እጅ ወደቀች። እየተሲቃዩም በሰኦል ታጎሩ።

ሰይጣንም ወደ ኋላ ሲመለከት ዳግመኛ ወጣቱ ከሞት መነሳቱን እንደተመለከተ አይኑ ወደ ደምነት ተለወጠ። እፍጥጦ "እርሱ ነው እርሱ አይደለም" እያለ ፊህ ቀረ። ከዚያም በብስጭት በሲኦል ያሉትን ያለማቋረጥ እንደገና እስር እጥፍ ከፊቱ በላይ ይሰቃዩ ዘንድ እሳቱን ያነድደው ጀመር። ለእርኩሳን መናፍስቱም እንዲያሰቃዩዋቸው አዘዘ። በብስጭት የሲኦልን እግር፣ እንገትንና እጅ ያንቀሳቅስ ገባ። ያን ጊዜ ታድያ በሩቅ ምስራቅ የሚኖሩ ሰዎች ላይ የመሬት መንቀጥቀጥ አስነስቶ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው። ህንፃዎችንና ከተሞችን አወደመ። ያንን የሸለመውን እርኩስ መንፈሰም በብስጭት ማዕረጉን ገፍፎ በእሳት ባህር ውስጥ ወረወረውና ሌላ ከእርሱ የከፋውን በእርሱ ቦታ ሾመው።

ያ ብራዚላዊ ወንድም ግን "ጌታ ይመስገን እኔ ድኛለሁ እኔ እምልጫለሁ" እያለ የደሴቲቱ ወገኖችን ማገልገሉን ቀጠለ። ከዚያም በደሴቲቱ ለሚሽነሪ አገልግሎት ከመጡ አገልጋዮች ጋር በመገናኘቱ ከዚያም ለትምህርትና ለአገልግሎት ወደ ኒው ዮርክ ልከውት በቲዎሎጂ ድግሪውን በመያዝ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ትውልድ ሀገሩ ወደ ብራዚል በመመለስ የብራዚል እንዲሁም የላቲን አሜሪካ የመንፈስ ቅዱስ መነሳሳትና ለብዙ ሚሊዮኖች መዳን ምክንያት መሆን ቻለ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዲያብሎስ ይህን ሰው ይፈራው ጀመር። ሆኖም ግን መዋጋቱን አላቆመም ነበር። ነገር ግን ሁልጊዜ በዚህ ወንድም አሸናፊነት ነበር ፈተናዎቹ ሁሉ የሚጠናቀቁት። አገልግሎቱ ሁሉ በኃይልና በመገለጥ ነበር። ክርስቲያኖች ልሳን በሚናገሩ ሰዓት አጋንንትን እንዴት ግራ እንደሚያጋቡ በዚህ ወንድም አገልግሎት ለመታዘብ ቻልኩ። በእንደኛዉ አሁድ በሪዮ ዴጀኔሮ በዋና

ከተማዋ በተካሄደ ኮንፍረንስ ላይ ይሄ ወንድም ተጋባዥ ሆኖ ጌታ ያደረገለትን በመመስከር ላይ ሳለ በአስታዲየሙ ዉስጥ በሰዎች ላይ ተቀምጠዉ ቃሉን እያጣመሙ ህዝቡን በፈዝ ሞልተዉ የነበሩ መናፍስቶች እየተወጉና እየተጣረዱ ሲሸነፉ እንዲሁም ድል ሲነሱ በሰማይ ላይ እሲቃ ነን እያሉ እየሩ ላይ የተለያዩ ዘዉድ የሜት ሁሉ ከምስክርነቱ እና ጉባኤዉ በልሳን ሲናገር ግራ ሲጋቡና ድባት ሲሙቱ ተመለከትሁ።

ሰይጣን ሁል ጊዜ የተለያዩ ሰድሰት አይነት የሰለላ መረቦችን በሶስት ዙር አለምንና ሰዎችን ተብትቦ ነዉ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ ለመምሰል ጥረት ሲያደርግ ያየሁት። ነገር ግን እነዚህን የሰለላ መረቦቹን ሁሉ በልሳን የሚፀልዩ ሰዎች እየበጣጠሱ ሲያልፉ እና ከሀዋ አልፈዉ ወደ እግዚአብሔር መገኘት ሲገቡ ለመመልከት ችያለሁ።

ወገኖቼ መንፈሳዊዉ አለም እዉነት ነዉ። ሰይጣን ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖችን ከመንፈሳዊዉ አለም በማጠራጠርና የማይደረስበት በማስመሰል በማሰላቸት እና በድንዛዜ እየመታ መናፍስቱ ግን ያለማቋረጥ ሃያ አራት ሰዓት እየተቀያየሩ ኢንፎርሜሽን እየተለዋወጡ የሰዉን ልጅ ሲያጠቁት አመለከት ነበር። የጠላትን ሀሳብ እንስተዉም እንደሚል ቃሉ በመናፍስቱ አለም የሚፈሩ እና በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ በመገለጥ የሚፀልዩ ክርስቲያኖች የመናፍስቱን መረብ ሁል ጊዜ ሲበጣጥሱ እጅግ ብርቱዎች ነበሩ። እነዚህ እንደዚህ የሚፀልዩ ሰዎች ለሰይጣን ሁልጊዜ ስጋት ናቸዉ።

መንፈስ ቅዱስ ምን እንደሚገልጥላቸዉ ሰይጣን ማወቅ ስለማይችል እነዚህ የበረቱ የፀሎት ሰዎች የተለያዩ ማዘናጊያ ጣቢያዎቹን በድንገት ሁልጊዜ በማደባየት ይታወቃሉ። በአየሩ ላይ ብዙ አለቆችና ስልጣናት በቅዱሳን ፀሎት እየታሰሩ በእግዚአብሔር መላእክት እየተጠረጉ ወደ ሲኦል ይወረወሩ ነበር። ይኼ ሁሉ በየሰከንዱ የሚከናወን ተግባር ነበር። ብዙ ክርስቲያኖች በልሳን ሲፀልዩ ሀይል

እየተሞሉ በየማይከሮ ሰከንዱ ዲያቢሎስና ሰራውን እቅዱን ሁሉ ያፈራርሱ ነበር፡፡ ሰይጣን የዚያን ጊዜ በጠንካራ ቡጢ ዓይኑን እንደተመታ ሰው ተሰምቷቸውበት የያዛቸው የቅዱሳን በረከቶች ከብብቱ እየወደቁ ለቅዱሳን ይደርሷቸው ነበር፡፡

በዚህም ምክንያት እየተመናበረበረበት በየቀኑ ያቀደውን ጥፋት ከማድረስ ይልቅ ወደ መከላከልና ወደ መሸሽ ድምፁንም ወደ ማጥፋት ይገባል፡፡ እርኩሳን መናፍስቱም በተለያዩ አፀዶቻቸው እየተሰሙ ምቹ ሁኔታ ይጠባበቁ ነበር፡፡ ሰይጣንና ሰራዊቱን ብርቱ ያደረጋቸው ሁልጊዜ የሚያሳዩት ትጋትና ተስፋ አለመቁረጣቸው እንጂ አንድ ክርስቲያን እንኳን ከላይ እንደጠቀስኩት አይነት ፀሎት ሲፀልይ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ መናፍስትን ይፈጃቸውና ያስራቸው ነበር፡፡ ነገር ግን የሚያሳዝነው አንዳንድ ክርስቲያኖች እየተኙ በተለያየ ሀሳብ ተይዘው በመንፈሳዊው አለም ያላቸውን ሀያልነት እንዳይረዱ ስለሆኑ በጥርጥርና በደመነፍስ በኢየሱስ ስም ሲሉ መናፍስቱ ቢበተኑም ወዲያው ይመለሱባቸው ነበር፡፡

እንደዚህ አይነት ፀሎት በሰይጣን ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ የሚባል መሆኑን ለማወቅ ችያለሁ፡፡ በአፋቸው የኢየሱስን ስም ይጠራሉ በልባቸው ግን ሀጥያትን ያስላስላሉ፡፡ ያኔ ታድያ በኢየሱስ ስም ሲሏቸው የስሙ ጉልበት ብቻውን ሲያባርራቸው ብትን ብለው እንደገና እንደ ንብ ወዲያው ሁለንተናቸውን ይቆጣጠሩት ነበር፡፡ አልፈውም ከፀለዩ በኋላ በተለያዩ አጋንንታዊ ፈተናዎች በበቀል ስለሚያሰቃዮአቸው "ስለፀለይክ እና ስለፆምክ ነው እኮ ይኼ ፈተና የመጣብህ" በማለት በመዋሸት ሰይጣን የብዙ ክርስቲያኖችን ልብ በማስፈራራት እንዳይፀልዩ ከፀለዩም በመንፈስ እንዳይፀልዩ ይከለክሏቸውና ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰይጣንን እንዲፈሩ ያደርጋቸዉ ነበር፡፡

አብዛኞቹንም በዚህ መንገድ በጠላት ድል የተነሳ ህይወት እንዲኖሩ እና ቃሉንም በማንበብ የሚገኘዉን እምነት እንዳይዙ ቃሉን ማንበብ እንዲጠሉ (እንዲሰንፉ) በማድረግ ምንም እንኳን ያለ ቃሉና ያለ ፀሎት ክርስቲያን መኖር እንደማይችል ቢያዉቁም ለተረዱት እዉነት ምላሽ እንዳይኖራቸዉ በማያቋርጥ ስንፍናና ድንዛዜ ይመታቸዋል::

ከዚያም የተለያዩ የሀጥያት ድራማዎችን በሚቆጣጠራቸዉ አእምሮዎች በማዘጋጀት በሃጥያት በተደጋጋሚ በመጣል በማያቋርጥ ከስ ሁሌግዜ የበደለኝነት ስሜት እንዲሰማቸዉ በማድረግና በአፅማቸው እስኪቀሩ ድረስ በነፍሳቸዉ ከስተዉ ሀጥያትን ሲያጠቡ እንዲኖሩና በስብከትና በዝማሬ ላይ ብቻ እንዲመሰረቱ በማድረግ ሙሉ መዳንን ከማግኘት ይልቅ ተመላላሽ ታካሚ እንዲሆኑ አድርጎ የሚታከሙባቸዉንም የመዝሙርና የስብከቶችን ይዘት መለኮትነቱን በማስለቀቅ በምድራዊ ቁስ ላይ ብቻ የተመሰረተ በማድረግ ከእዉነተኛዉ መዳን ጋር እንዳይገናኙ አድርጎ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የዘመኑ ክርስቲያኖችን ተብትቦ ቤተክርስቲያንን እንደ እንፊ ትያትር በኮሜዲ ሰባኪዎች በመሙላት በስጋ ጦር ሲወጋ ተመለከትሁ::

አንዳንዶችን እንዲያዉም በአለም የሌለ ሃጥያት ዉስጥ እንዲገቡ በማድረግ ፈጽሞ ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይመጡና በአብይት እንዲሙቱ በድህነትና በስካር በሱሶች ጠላልፎ ወደ ሞት ሲነዳቸዉ ተመለከትሁ:: ወገኖቼ ይህን ጽሁፍ የምታነቡ ሁላችሁ አባካችሁ ዉደናችሁ ወደ እዉነተኛዉ መዳን ወደ ፀጋዉ ዙፋን በንሰሃና በመመለስ እንድትገቡ አማፀናችኋለሁ:: ለዚህ ነዉ በዚህ ምድ ዘመን ወደ መንግስተ ሰማይ የሚገቡ ሰዎች በገደል ዉሰጥ እንደሚንጠባጠብ የውሃ ጠብታ ጠብ ጠብ ሲል የተመለከትኩት:: ወደ ሲኦል ግን እንደ ትልቅ ጅረት እንደ ከረምት ጎርፍ ሃሰው ልጆች ነፍስ ሲፈስስ ነው የተመለከትኩት::

እነርሱን በድህነትና ነፃነታቸውን በመንጠቅ ከዚያም በማስጨፍጨፍ እና በማጨፋጨፍ እንዲሁም የእውነቱን መንገድ አስመስለን በብዙ ሐይማኖቶች ግራ አጋብተን ለዚህ ደርሰናል፡፡ የአሁኑ አቅዴ ግን ከመከላከል ወደ ማጥቃት ተሸጋግሯል፡፡ ስለዚህ ሰዎችን ሁሉ መንፈሳዊውን አለም በማስካድ ይሄንኑ አስተሳሰብ በተለያዩ ከፍተኛ ተቋማት የሰው ልጆችን የከፋት እውቀት ማሳደግና ሁሉንም ሃይማኖቶች እንዲከዱ በማድረግ ሰው የሚኖረው ለስራና በስራ ብቻ እንደሆነ ማስረጽ" በማለት ተናገረ፡፡

እንባቢዎቼ ስራ ለሰው ልጆች በአዳም ሃጥያት ምክንያት በእርግማን መምጣቱ ይሰመርበት፡፡ ሰይጣን ንግግሩን ቀጥሏል "ሐይማኖት ካለም ብርሃን ሰይጣን ነው ወይንስ እግዚአብሔር በማለት ብርሃን የመምሰልን ስርዓት አጠናክረን በመዘርጋት ምድር ላይ ያለ ሰው ሁሉ በምቾትና በብልጽግና በመሙላት ከእርሱ ጋር ተወዳድሮ መመለክ" እያለ ያለማቋረጥ አይኑን ጨፍኖ ተመሰጠ፡፡ ከዚያም የምድር ዋና ዋና መንግስታትን በቀጥታ እኔን በሚያመልኩ መሪዎች መሙላት፡፡

በመቀጠልም አይሁዶች እንጠብቃለን በሚሉት መሲህ ተመስሎ መወለድ፡፡ በዚህ ሁሉ ግን አደጋን በምድር በማብዛት ሰዎች በየቀኑ እንደ ውቅያኖስ ያለማቋረጥ ወደ ሲኦል እንዲገቡ ማድረግ፡፡ ከዚያም ከኢየሩሳሌም ትእዛዝ እየሰጠሁ መሲሁን መስዬ የተመረጡትን ማሳት፡፡ በኋላም አለምን በሙሉ ከእርሱ አምላኪዎች ማጽዳት፡፡ የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን አዳዲስ ፈጠራዎችን ከሰዉ ልጆች ጋር በመሆን በመፍጠርና ምሽግን በማዘጋጀት እርሱ ሲመጣ ተዋግተን ማሸነፍ አለብን፤ ማሸነፍ አለብን" ሲል አርኩሳን መናፍስቱ በመሪነህ ይዘዉት የነበረዉን ጦር መሳይ የሃጢያት ፍላፃዎች መሬቱን በመቀጥቀጥ ድጋፋቸዉን ልክ እንደ ጅብ ሳቅ በማሽካካት እና በማልጎምጎም እንደ አባብ ሲጥሲጥታ አይነት ድምጽ አወጡ፡፡

ሰይጣንም ያንን አሲታቂ ሳቁን ሲስቅ በሲኦል ያሉ ነፍሳት ሲቃያቸዉ ጨምሮ ኖሮ በጩኸትና በለቅሶ ሰፈሩ ተሞላ፡፡ ያኔ ታዲያ ሙት ከሆነዉ ከሲኦል ማህፀን

የወንድ ነበር። ማንኛውንም ሰው የሚያደነዝዝበት ማደንዘዣ መርዝ ከሲኦል በቀዳት እቃ ውስጥ እራሱ ሰይጣን ሞላበት። ከዚያም ይደንሱ የነበሩት ሴቶች በቅዕበት አይን ወደ ዘንዶነት ተቀየሩ። በኋላም እንደተቀባ የኮብራ እባብ አንገታቸውን ቀና አድርገው መርዛቸውን በአለቃው መንፈስ እቃ ውስጥ ተፉት።

በመቀጠልም መናፍስቱ ሁሉ አንዴ እንደ ሰው፤ ሴት፤ ወንድ፤ እባብ፤ ጅብ አይነት ፍጥረት በመሆን ይለዋወጡ ያዙ። በኋላም ሰውን ሁሉ ያስቱ ዘንድ ሰይጣን ስልጣን ከሰጣቸው በኋላ በምድር ሁሉ ተሰራጩ። ከዚያም ይሄ የገዛው መንፈስ ፍጹም የማርያምን ምስል በመምሰል የጠፈሯ ንግስት የተባለ ዕሁፍ ያለበትን ዘውድ በራሷ ላይ በመጫን ጨረቃን እንደ ማዘዣ ጣቢያዋ ስታደርግ ተመለከትሁ። በዚያም መናፍስቱ ዘፋን አዘጋጅተውላት ተቀመጠች። በስሯ የነበሩትንም መናፍስት በሙሉ ወደ ምድር አሰማራች። በኋላም መናፍስቱ በሰዎች ሁሉ ላይ የተለያየ እርኩሰታቸውን በገዛው መንፈስ ወደየሰዉ ሁሉ ሲደፉት ተመለከትን።

ይህ መንፈስ በሰዎች ሁሉ ላይ የተደፋ ቢሆንም ነገር ግን በተለይ በእውነተኛዎቹ የጌታ ተከታዮች ላይ በብዛት ያለማቋረጥ ይደፋባቸው ነበር። ኋላም ከዚህችው እርኩስ መንፈስ ፊት እጅግ ብዙ የሆኑ ከባህር ውስጥ የወጡ ሴትና ወንድ የሚመስሉ መናፍስት ቆመው ነበር። ሁሉም ብዙ ሃይል ከእጆቿ ከተቀበሉ በኋላ ወደ የአገልጋዮች ቤት ሲገቡ ተመለከትናቸው። ሰዓቱም ከለሊቱ 8:00 ሰዓት አካባቢ ነበር። ኋላም አንቅልፋቸውን አብርረው በህልማቸው በማለጥ አብረዋቸው ገዘው ሲሰሩ ተመለከትሁ።

አንዳንዶቹ በማግስቱ አገልግሎት ያለባቸው ሁሉ ነበሩበት። ቀጥሎም በከስ ብዙዎቹ ለእግዚአብሔር የሚገባውን እውነተኛ እምልኮ ማቅረብ እንዳይችሉ ሲያዘገዩአቸው እንመለከት ነበር። ብዙጊዜ ወጣት የሆኑ አገልጋዮችን የሚዋጉበት አንዱ መንገድ ይሄ መሆኑን ተገነዘብኩ። ሌሎችን ደግሞ በአብዛኛው ወጣት ወንድና ሴቶችን እራሳቸውን በተለያየ መልኩ በተመሰጠ ከብዙ ሴቶች እና

ሰው ሁሉ ያጣው የአዲሱን ሰው ማንነት ነው። መውለድ፣ መስራት፣ መብላት፣ መጨነቅ፣ ሰው ሁሉ ሲወርድ ሲዋረድ እየኖረበት ነው። ወንድሜ ምንም አይነት አዲስ የኑሮ ማሻሻያ ቴክኒክ ያገኘህ ቢመስልህ አትሳሳት። አንተ አሁን ስለደረስክበት አዲስ መስሎህ ይሆናል እንጂ ነገሩ ግን አዲስ አይደለም።

ቃሉ ሲናገር እግዚአብሔር እራሱ እነሆ አዲስ ኪዳን ከህዝቡ ጋራ የምገባበት ጊዜ ይመጣል ይላል። እነሆ አዲሱን ነገር አደርጋለሁ እርሱም አሁን ይበቅላል ይላል። 'ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፏል' ብሎ ይናገራል። ስለዚህ ይህ አዲስ ፍጥረት ነው በአዲሱ ኪዳን ክርስቲያን ተብሎ የተጠራው። ይህ ፍጥረት ነው ከአነ አዳም ውድቀት በፊት የነበረውን ህይወት እንዲኖር የተፈቀደለት። ሳይለፋ፣ ሳይደክም፣ በክርስቶስ ባገኘው ቤዛነት እንዲያው ያለ ቅድመ ሁኔታ በነጻ በፀጋው የዳነው፣ ስለዚህ ይህ በፀጋ የዳነ አዲሱ ፍጥረት ያንን አሮጌውን ፍጥረት እንዴት ሊያገለግለው ይችላል? እንዴት ከአንድ ምንጭ መራራና ጣፋጭ ውሃ ሊቀዳ ይችላል? መልሱ በእጭሩ አይችልም ነው።

ለዚህም ነው ጌታ ሲናገር ማንም መስቀሉን ተሸክሞ ሊከተለኝ የማይወድ የእኔ ሊሆን አይችልም እንዲሁም ዘመዱን፣ እራሱን፣ ገንዘቡን፣ እውቀቱን፣ ሁሉን ጥሎ ሊከተለኝ የማይወድ የእኔ ሊሆን አይችልም በማለት ያስተማረው። ታዲያ ለመኖር መስራት ቢኖርብንም ለመስራት ግን መኖር የለብንም። ለክርስቶስ ብቻ ነው መኖር ያለብን። የእኛ ነገር ሁሉ በዚህ እውነትና እውቀት ከተቃኘና ለውስጣዊ ማንነታችን ማሰብ ከጀመርን እምላካችን የሚያስፈልገንን ቀድሞ አውቆ ያዘጋጅልናል።

የምድር የሆነው ነገር ሁሉ ከመሸሽ ይልቅ እኛን መከተል ይጀምራል። ማንም በዚህች ምድር ላይ ሲኖር ለሲጋው የሚኖር ከሆነ እርሱነው ማለት ነው የምድሩን ነገር የሚከተለው። በህይወት ዘመኑ ሁሉ ኑሮን ሲከተል ሲደርስበት እና ሲቀልበት፣ ክብርን ሲከተል ሲደርስበት እና ሲያንሰበት፣ ሀብትን ሲከተል ሲደርስ ሲያንሰበት፣ እንዲሁ እያለ ወደ መጨረሻው መጥቶ ሳይሞላለት እጣው በሲኦል

መልአኩቴን የሚሰማ ሁሉ እራሱን በማየት ካለበት እንግዳ አሲተሳሰብ ዛሬ ይውጣ፡፡ በመመለስ እና በማረፍ ይድናልና ከአመፅ ልቡን ‘ያሸሸ” አለኝ፡፡ ሰይጣንም እነዚያን እርኩሳን መናፍስት በተለያየ አላማ ወደ ምድር ካሰማራ በኋላ ስብሰባው ተበተነ፡፡ ከዚያም እኛም በብርሰሃን ሉላችን ተሳፍረን ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ከሲኦል ወጥተን ከሲኦል ርቀን ምንም እንኳን የሄድን ቢሆንም ጩኸታቸውና ስቃያቸው ልቤን በጣም ስለ ነካው ለረጅም ጊዜ ከጆሮዬ አልጠፋም ነበር፡፡

# ምዕራፍ አራት

## አማራጭ መንገዶች

### መንታው መንገድ

ጌታ ይህንን ሁሉ ነገር ካሳየኝ በኋላ አሁን ና እንሂድ" ብሎኝ ወደ ምድር ተመለስን:: በኋላም አንድ ፀጥ ያለ ጎዳና ተከትለን ጥቂት እንደተጓዝን ሁለት መንታ መንገድ ላይ ደረስን:: እዚያም የምድር ሰዎች ሁሉ ተሰልፈው ወረፋቸውን ሲጠባበቁ ተመለከትሁ:: እነርሱም በቅደም ተከተላቸው ወደ መንታው መንገድ ይመጡና ይሰለፋሉ:: ከመንገዶቹ አንዱ የጠበር መንገድ ሲሆን ዳርና ዳሩ ገደል የሆነ ነው:: ለመሄድ የማይመች እና ረግረግ ያለበትም ነው:: 'ይህ የኢየሱስ መንገድ ነው' የሚል ሰሁፍም ተፅፎ በቀስት መልክ ተሰቅሎበታል:: ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ብዙ መንታ መንገዶች ያሉት ሆኖ አሰፋልት እና ሲጓዙበት ቀና የሚመስል ጎዳና ነው:: በኋላም እዚያ መንሻ ላይ ቆመው "በዚህ ጋ ሂዱ፤ ይሄ መንገዱ ቅርብ ነው፤ ምቹ ነው" እያሉ የተለያዩ የሐይማኖት አባቶች፣ ሳይንቲስቶች፣ አለም እራሷ ሰው ተመስላ፤ ሰዉን ይገፋፉ ነበር::

እንዲሁም ራሱ ሰይጣንም "አማራጭ መንገድ አለኝ" እያለ ይለፈልፍ ነበር:: ከህደትም ቆሞ "አባካችሁ የሚሏችሁ ሁሉ ዝም ብሎ ነው፤ ውሸት ነው፤ አትመኑ:: በአይናችሁ የሚታየው ብቻ ነው ልክ:: መልካም የሆነውን አይታችሁ ሂዱ" እያለ ማስታወቂያውን ይናገር ነበር:: በኢየሱስ መንገድ ላይ ደግሞ ወንጌላውያን፣ ፓስተሮች እና ነቢያት ሁሉ የተዘረጋ መፅሃፍ ቅዱስ በሚመስል ውሃ ላይ ቆመው በብዙ ፈገግታ "አባካችሁን ወደ ኢየሱስ መንገድ ኑ:: ይሄ ነው እውነተኛው መንገድ" እያሉ በትህትና እና ልመና በሚመስል መልኩ እየተቀባበሉ እጆቻቸውን ዘርግተው ይማፀኑ ነበር::

በዚህ በኢየሱስ መንገድ ወደኋላ ለመመለስ መሞከር በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ በሌሎቹ መንገዶች ግን ሰዎች እንደፈለጉ በአንዱ የተወሰነ ይሄዱና ደግሞ ወደ ሌላው ይተይሩ ነበር፡፡ ጌታም "ልጄ ያየኸውን በደንብ ፃፈው" ብሎ አዕምሮዬን በእጆቹ ዳሰሰው፡፡ ከዚያም አያንዳንዱን እንቅስቃሴ በጥልቀት የምመለከትበትን ዓይን ሰጠኝ፡፡ ቀድሞ ከነበረኝ እይታ መቶ እጥፍ እድርጎ የገጠመልኝ ዓይን እይታዬን በእጅጉ አጠራው፡፡

በኋላም ስመለከት ከተሰለፉት እጅግ ብዙ የምድር ህዝቦች አንዳንዶቹ "በእስፓልቱ እንሂድ ወይንስ በእውነት መንገድ፤ በኢየሱስ መንገድ እንሂድ" እያሉ ተራቸውን እያሳለፉ ትራከቶችን እየወሰዱ እያነበቡ እየጣሉ እዚያው መንገድ ላይ እንደቆሙ ዘመናቸው የሚያልቅ እና የሚያረጁ ሰዎችን ተመለከትሁ፡፡ ከዚያም "ቆይታህን ጨርሰሃል" እያሉ ቆይታቸውን የጨረሱትን ሰዎች ነፍሳቸውን ከስጋቸው እየለዩ ከፉ መናፍስቱ ይወስዷቸው ነበር፡፡

መንታው መንገድ ላይ ሲያመነቱ ጊዜያቸውን የጨረሱትን ሰዎች የሰይጣን ሰራዊቶች እስገድደው በሰፊው መንገድ እቻኩለው መጨረሻው ገደል ወደሆነ ሰፍራ ወደ ሲኦል አፍ ወደ እሳቱ ይጨምሯቸው ነበር፡፡ በነገራችን ላይ እዚህ መንገድ ላይ የቆሙትም ሆኑ መርጠው የሚጓዙት ከእግዚአብሔር የተወሰነላቸው የምድር ቆይታ ከ—እስከ የተባለ የተገደበ እድሜ አላቸው፡፡ ይህንን እድሜ ሲጨርሱ ለሰው ልጆች ሁሉ እየመረጡ ግዜህን ጨርሰሃል የሚል በቀይ ካርድ ላይ የተፃፈ ዕሁፍ ሲሰጡት ወዲያው ነፍሱ ከስጋው ትለይና በጠባቡ መንገድ የሚሄድ ከሆነ መላዕከቱ በሰፊው ጎዳና የሚሄድ ከሆነ ደግሞ እርኩሳን መናፍስቱ ይወስዱት ነበር፡፡

ነበር ተመለከትኩ። ስጋና መንፈስ ግን ግድ አልነበራቸውም። ይህም የሆነው ስጋ እስከ ቀይ ክርዱ ብቻ ስለሚጓዝ እና ጉዳዩ ስላልነበረ ነው። የሰው መንፈስም እንዲሁ የሚሻር ስለሆነ ነው። ሆኖም ለነፍስ ይህን ሁሉ ለገቶ ለጥተዋት ረጅሙን መንገድ እንድትጓዝ የራሳቸው ባልሆነው ጉዳይ እንዲሁ እያሏት ለጊዜው ያላቸውን ተደማጭነት ተጠቅመው ለሲኦል ሲያሳብሏት ተመለከትኩ።

እስከ መጨረሻው ድረስ ግን ልክ ኮምፓስ አቅጣጫን እንደሚጠቁም በየትም ቢያዟዟሯት በየትኛውም መንገድ ቢያስኬዷትም አይኖቿ ወደ እግዚአብሔር ወደሚወስደው መንገድ ይመለከት ነበር። ግን ምን ዋጋ አለው፤ ይኼ ስግብግብ ስጋና ከእርሱ የሚተባበሩ ሰውች አስተሳሰብ(የሰው መንፈስ/አዕምሮ) ላይኖሩበት ቀና በመሰላቸው መንገድ ሰውን ሁሉ ለሲኦል ዳረጉት እስኪ በሆዴ። ሰው ሁሉ መንገደኛ ነው፤ መድረሻውን ነው የማያውቀው እንጂ።

ከህፃን እስከ አዋቂ ሁላችንም መንገደኛ ነው። አንዳንዱ ቆሞ ይልና ከሰልፉ ወጥቶ ሌላ ሰው ሁሉ እየሄደ እንዳለ ለቆምበት፤ ባይገባኝም ተመልሶ ሰልፉን እያለ ወደ ሰልፉ ይገባ ነበር። ሰው ሁሉ ወደ ሞት ነበር ጉዞው። ነገር ግን በሰልፉ መሃል አንዳንዶች ወደ ጠባቡ መንገድ እየገቡ የሚታየውን ሳይሆን የማይታየውን ተብቆ አድርገው እምነት በሚባል ድልድይ ሲሻገሩ ተመለከትኩ።

ጀሙንም ሲጠጡ አመለከት ነበር። ኋላም ደማቸዉ ፈጽሞ የክርስቶስ ሆኖ ይቀኖር ነበር። ሲጋቸዉም የእግዚአብሔር መቅደስ የመንፈሱም ማደሪያ ሆኖ ሲሰራ ተመለከትሁ። ከዚያም ጉዟቸዉን ፈጽመዉ ያለመታከት የሚሄዱበት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከተከናወነላቸው በኋላ ለሁሉም የተለያዩ ማዕረጎች ተሰጣቸዉና በአስር እጥፍ ፍጥነት በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ መጓዝ ጀመሩ።

# የሰይጣን ፈተና

ሰይጣን እነዚህን የፅድቅ መንገድ ተጓዦች መንገዳቸውን የተጨናነቀ ያደርግባቸው ነበር። በአንዳንዶች ላይ በመንገዳቸው ጉድጓድ ቆፍሮ በውስጡ ጦሮችን ሰክቶ ልክ አውሬ እንደሚታደን ያድናቸው ነበር። በሌሎቹ ደግሞ አሽክላን ይዘረጋባቸውና የሚፈልጉትን ነገር በአሽክላ ያጥረው ነበር። ቅዱሳኑም ልክ እንደበጎች መስለው ታዩኝ። ሰይጣንም እንደ አንበሳ ድምጽ ሆኖ ያጓራባቸው እና ይዞራቸው ገባ።

ግማሹ በርግገው ፈርተው ሲወድቁ በውጥመዱ ሲያዙ ተመለከትሁ። ሌሎቹ ግን ፀንተው ይቃወሙት ነበር። ከዚያም ከበጎቹ የሚምዘገዘግ ሚሳኤል ነገር እሳት ሆኖ አንበሶቹን ፈጃቸው። የቃሉንም ሰይፍ ታጥቀው፣ በእምነት ጥሩር ተመሽምተው፣ በጠላት አሽክላ ላይ ተረማምደው፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሆነው፣ ጉድጓዶችን በጥንቃቄ አልፈው ሲሄዱ ተመለከትኩ። ግማሾቹ እርኩሳን መናፍስቶች እባብና ጊንጥ መስለው በየመንገዳቸው ተሰውረው አመለከት ነበር። ነገር ግን ለሁሉም እንደ ጋሻ ነሃስ የሆኑ ጫማዎች ተሰጣቸው። በየጉኙ ውስጥ ተሰውረው የነበሩትን እየረጋገጡ እባቦቹና ጊንጦቹ እንደ ፌስታል እየተጨማደዱ ሲፈነዱ እነርሱ ግን ጉዟቸውን ቀጠሉ። 'እባብና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በክፉ ሃይል ላይ ስልጣን ሰጥቻችኋለሁ' የሚለውን ቃል አስታወሰኩ። ክርስቲያኖች ብቻቸውን ከሚሄዱ ይልቅ በህብረት ሲጓዙ እጅግ ውጤታማ መሆናቸውን በክፉ ሃይላት ላይ አቅማቸው በአስር እጥፍ እንደሚጨምር ተገነዘብሁ።

ወደ ክርስትና በመመለሱ መሪዎች የእስላም ጂሃዲስቶች በማስገባት ከተማዋን ያቃጥሏታል ቤተክርስቲያንን ጭምር አቃጠሉ፡፡

ክርስቲያን የሆኑትንም እያሳደዱ ይገድላሉ፡፡ ከዚያ በኋላም ይህንን ወንድምና ሌሎችንም ከያዟቸው በኋላ የእስልምና ቃልኪዳን የሚገባበት ቦታ ወሰደዋቸው የሆነ ጉድጓድ እንዲዘሉና መሃላ እንዲያደርጉ ይጠይቋቸዋል፡፡ ሁሉም ረጅም ቢላዋ ይዘው ነበር፡፡ ሁሉም አረመኔ ሙስሊሞች ነበሩ፡፡ በኋላም ክርስቲያኖች በሙሉ እሳልፈው እስልምናን የተቀበሉትን ወደ ግራ እንቢ ያሉትን ደግሞ ወደቀኝ ከዚያም በቀኝ ያሉትን ግንድ ላይ አስተኝተው ልክ እንደ እንዳ በማጅራታቸው ያርዱአቸው ነበር፡፡

የዚህ ወንድም ተራ ሳይደርስ ይህ ወንድም ታስሮም "እየሱስ ጌታ ነው እትፍሩ" እያለ ጓደኞቹን ሲያበረታታ ሳለ ከአራጆቹ አንዱ ከሰልፉ አውጥቶት ካንበረከከው በኋላ "አንተ ነህ የእኛን ስራ የምታፈርሰው" ብሎ ቢላዋውን አንገቱ ላይ ሲያሳርፍ እየሰነዘረ ሳለ ድንገት በአካባቢው ላይ የጥይት እሩምታ ይሰማ ጀመር፡፡ ያኔ ለካ የመንግስት ሰራዊት ደርሶ ኖሮ እሱመው ይህን ወንድም ለማረድ የሰነዘረውን ሰው ግንባሩን ሲመቱት እዚያ ወንድም ላይ በደረቱ ሲደፋ ያወንድምም እጆቹ ወደኋላ ፍፁም በህራሄ በሌለው ሁኔታ ታስረው ስለነበር እርሱም ሰውዬውን ገፍትሮ ወደ ጎን ወደቀ፡፡ ከዚያ ጥቂት ግዜ የጥይት እሩምታው ከቀጠለ በኋላ ተመልሶ ፀጥ አለ፡፡

ያኔ ታዲያ የተለያዩ ከሚካው ጋር የተመሳሰለ ቅጠላ ቅጠል በየሰውነታቸው ላይ ያሳሰሩ ወታደሮች መጥተው ሁሉንም ከታኙ በኋላ እርሱንና ጓደኞቹን ከእስራቸው ፈትተው ለቀቁአቸው፡፡ በኋላም ለካ እንዲዘሉ ሲደረጉ የነበረበትና እስልምናን ስለ መቀበላቸው ኪዳን የሚያስገቡበት ጉድጓድ ከአንገታቸው ላይ ታርደው በተጣሉ የሰው ጭንቅላት ተሞልቶ ነበር፡፡ በኋላም ይሄንኑ

ከተማ ከገባ በኋላ በዚያም ሁለት ቀናት ቆይቶ ፊልም በመፀፀት እና ንስሃ በመግባት ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ ጉዞውን ወደ ገጠር በማድረግ በጅጅጋ አካባቢ ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በብዙ ርሃብ፣ እርዛትና ችግር ቆይቶ በስተመጨረሻ በነበረበት ገጠር በወባ በሽታ ከታመመ በኋላ እንደምንም ወደ ጅጅጋ ከተማ ይመልሱታል፡፡

ታዲያ እጅግ ስትስት ብሎ በማልቀስ ተመልሶ ወደ ሌላ ስፍራ በመምጣት በዚያች ከተማ ከተያዘው የወባ በሽታ ከዳነ በኋላ በአንድ ምሽት ጌታ ራሱ በህልሙ ይገለጥለትና ሰላም ለአንተ ይሁን" ብሎ በብርሃን ወደ ራሱ እጁን ይዞት ይወስደውና ወደ አንድ ከፍ ወዳለ ተራራ ካወጣው በኋላ በብሉይ ኪዳን እንዳለው አይነት መሰዊያ ላይ አስተኝቶት ልክ እንደ ዶክተር የሰውነት ከፍሉን ከፈወሰ በኋላ ደሙንም ከውስጡ ቀድቶ መሰዊያው ላይ ያፈስሰዋል፡፡

እስከትሎም ጌታ የራሱን ደም በውስጡ በመጨመር እንደገና ያነቃውና ልጄ ዛሬ ከኤችአይቪ በሽታና ከሌሎች ቫይረሶች እና ህመሞች ፈውሼሃለሁ ነገ ሄደህ የህክምና ምርመራ በማድረግ ማረጋገጥ ትችላለህ" ብሎ ወደ አንድ ሌላ ከፍታ አውጥቶት ከከፍታው ላይ ከጌታ ጋር እየበረሩ ከተማዎችን ወደታች እየተመለከቱ ያለምንም ከንፍ ከመሬት ስበት ውጪ ልክ ውሃ እንደሚዋኝ ህዋውን ይዋኙ ነበር፡፡

ጌታም በአንተ ውስጥ ያለው ደሜ ነው ማንም ሰው በእምነት ቢነካህ አንተም ደግሞ ሰዎች ብትነካ ካሉባቸው ከማንኛውም ደዌ ነፃ መውጣት ይችላሉ" በማለት እጅግ የከበሩ መንፈሳዊ ማእረጎችን ካስያዘው በኋላ የቃልኪዳን ቦታ ወደ ሆነችው ቤተልሄም ከተማ እስራኤል አገር ውስጥ በሚገኝ ከፍታ ቦታ እጠገብ ወዳለው ገደል አፋፍ ወስዶት ጌታ አንተም ላትተወኝ እኔም ሳልተውህ እነዚህ ጠጠሮች ምስክሮች ናቸው" በማለት 12 ጠጠሮችን ወደገደሉ እንዲወረውር

ያደርገዋል። እርሱም ከወረወረ በኋላ በማስከተል የህይወት ታሪኩን ሁሉ የኋላውንም የወደፊቱንም አሳየው።

በኋላም ዘይትን አንስቶ በጭንቅላቱ ላይ አፍስሶበት በመጨረሻው ዘመን የሚገለጠው ክብር እንዲያገኘው በስልጣኑ ከሾመው በኋላ ያ ወንድም ሲነቃ በውስጡ ጌታን እያመሰገነ እና እየባረከ ለሊቱ ሲነጋ ወደ ሆስፒታል ሄዶ ሲመረመር ፍፁም ጤነኛ እንደሆነ ይገለፅለታል። ማመን አቃተው። ይህ ሰው ከእርሱ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀሙ እና ከእርሱ ጋር ያሳለፉ ሶስት ሴቶች ያለ ምህረት በዚህ በሽታ ማቅቀው እና ተላልጠው ሲሞቱ ተመልክቷልና።

እናም ይህንን ታሪኩን ሰዎች በሙሉ ያውቁ ኖሯል እና ፈፅሞ ማመን ተሳነው። በመቀጠልም በሌሎች ሁለት የህክምና ተቋማት በመሄድ በተመሳሳይ ቢመረመርም ዶክተሩ ኢየሱስ ፈውሶት ነበርና ዳግመኛ ሊገኝበት አልቻለም ነበር። ይህ ወንድም በሚገኝበት ጉባኤ ፈፅሞ ድንዛዜ ማየት ይከብዳል። ሲያመልክ የምሩን ያመልካል፣ ሲፀልይ የምሩን ይፀልያል ለጌታ የምሩን ነበር የሚኖረው።

ነገር ግን በህይወቱ ከዚህም በኋላ እጅግ ብዙ ፈተናዎች እየመጡበት ይፈትኑት እና ይነሳ ነበር። እርሱ ራሱ በላዩ ላይ ያለውን ክብር እኛ የምናየውን ያህል አያውቀውም ነበር። ለዚህ ወንድም ሰፍራ የሰጡት ሁሉ እጅግ ይከብሩ ነበር። ሁልጊዜ የጌታ ዓይኖች በእርሱ ላይ ነበሩ። የባረኩት ይባረኩ ነበር። የረገሙት እየተረገሙ እስከ ሞት ድረስ ይደርሱ ነበር። እንዲፀልይላቸው እንኳን ፈቅደው ወደ እርሱ የመጡ ሁሉ ከማንኛውም ችግር ነፃ ይወጡ ነበር። ሰይጣንም ይህንን አውቆ በብዙ ቀን ከለሊት ይዋጋው ነበር። ጌታ ግን የሰይጣንንም ፈተናዎች ጭምር ወደ በጎ የእርሱንም ድካም ለመልካም እየለወጠ ወደ ፊት ያስገሰግሰው ነበር።

ይኸው ምክር መልኩን በመቀየር የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድ ሲኖት መሆኑን ጌታ ተናግሮኛል።

እናም ታዳያ ይሄ ወንድም በብዙ መከራ እና ችግር በላዩ ላይ ከተሸከመው የሂዮን መንገደኞች ምግብ መሃከል አንዳንዶቹ ይህን ይመስሉ ነበር። እየተጓዘም ሳለ ተይዞ ከነበረበት የረግረግ እና የጭቃ መንገድ በነጭ እምነበረድ እንደተሰራ በሚያምር እና ፍፁም ሙላት ወደተባለው መንገድ ገባ እና ያለ ምንም ማመንታት መንገደኞችን እየመገበ ወደ ገነት በሚወስደው መንገድ መጓዙን ቀጠለ።

ሰይጣን እጅግ በብዙ ወጥመዶች ሊያሰናክለው ቢሞክርም አልቻለም ነበር። ሰይጣን የቱንም ያህል በዚህ መንገድ ቢዋጋም እንኳን በእምነት በጌታ ይቅር ባይነት ምህረት ላይ የተደገፈ ሰው አሸንፎ ለድል እንደሚበቃ ከዚህ ወንድም ህይወት ለመረዳት ችያለሁ። ወንድሜ በዚህ መንገድ ብዙ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ፣ ድካም፣ ሃጢያት፣ በሽታ፣ ድህነት፣ ኪሳራ ወዘተ ሊገጥምህ ይችላል። የጌታ ሃሳብ በአንተ እንዲፈጸም ከወደቅህበት እየተነሳህ መራመድህን ማቆም የለብህም። ብቻ ባይገባህም እያለተሰህም ቢሆን ተጓዝ። ሰዎች ባይረዱህም፣ አንዳንዴ ምንተ ነገር ለማንም ባይገባም ተራመድ። ያን ጊዜ ሃይል ታገኛለህ። ክርስቲያን ከሆንክ ተስፋ መቁረጥ የለብህም አስትንፋስህ እስካለ ድረስ እንደገና የመመለስ እና የመታደስ እድሉ ያለህ መሆኑን ላስገነዝብህ እወዳለሁ።

አባቱ በአማልኩቱ ስም ዘመዶቹን ምስክር አድርገው ይምሉና ልጃቸውን ይረግሙታል::

ከዚያን ቀን በኋላ ቤተ ዘመዱም ከገዛምድና ሃረግ ውስጥ ይህ ሰው ይሰረዝ ብሎ ይወስንበትና ከአባቱ ቤት አንዲት ጥብቆ ብቻ ሰጥተውት ያባርሩታል:: ወጣቱ ግን ውስጡ ምንም ሳይነካ ቁጥቋጦ ውስጥ ገብቶ ይፀልይ፤ የክፉን ስራ ያፈርስ ጀመር:: ያኔ ታዲያ በአየሩ ላይ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በአካባቢው ላይ የሚመለኩ አውልያዎችን እሳት ያዘንብባቸው ገባ:: በእውነቱ ልጁ ሲታይ አይን የማይገባ ነበር:: ነገር ግን ከውስጡ የሚወጣው እሳት እጅግ ታላቅ ነበር:: መናፍስቶቹ "ምን መጣብንን" በማለት እየተቃጠሉ ስፍራውን ሲለቁ ይታይ ነበር:: በአካባቢው ላይ ኀገር ነን የሚሉት የአብድርቃድር፣ የሼህ ሁሴን፣ የከድር መናፍስቶች እስከ ጭፍሮቻቸው ከተቀመጡበት በአየሩ ላይ ካለው ዙፋናቸው እየተገለበጡ ወደ ምድረ በዳ ይሸሹ ጀመር::

ይህ ወጣት በመናፍስቱ አለም እጅግ አስፈሪ ሰው ሆነ:: አንድ መሃን የሆነች አከሱቱ ባሏ ጠንቋይ የነበረ ከሁለት አመት በፊት ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ እራሱን ወደ ባህር ወርውሮ የገደለ ሰው ሚስት ነበረች:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሴትየዋ ምንም እንኳን ጥሪት ንብረት ቢኖራትም 'ባሏን ሌላ ጠንቋይ ረግሞት ነው የሞተው' ተብሎ ስለሚነገር ዘመድ አዝማድ ሸሽቷት ጎረቤት ሁሉ ርቋት ብቻዋን ነበር የምትኖረው:: ከዚያም ወጣቱ አማራጭ ሲፈልግ እርሷ ጋር ቢሄድ ብቻ መኖር እንደሚችል መንፈስ ቅዱስ ይገፋፋውና ከእርሱ ሰፈር አምስት ኪሎ ሜትር ርቃ ወዳለችው አከሱቱ በምሽት ሳይቀር ተጉዞ ይደርሳል:: ሮጣውን፣ አዲስ ኪዳኑንና በትሩን ይዞ ሲገባ ሴትየዋ ቃሟ ይደርሳል:: ሰላም ይላትና አጠገቧ መደብ ላይ እንደተቀመጠ ሴትየዋ ህመሙ ይበረታባትና መሳል፣ ማቃሰት ትጀምራለች::

ተነክቶ አንድ እሁድ ቀን ቤተ ክርስቲያን መጥተዉ ወጣቱን ይቅርታ ይጠይቁታል፡፡ እርሱም ይቅር አላቸዉ፡፡ ከዚያም ሁሉም ጌታን እንደ ግል አዳኛቸዉ አድርገዉ ተቀበሉ፡፡ ቤተሰቦቻቸዉንና ዘመዶቻቸዉንም ጭምር ጌታን እንዲቀበሉ አደረጉ፡፡

ወንጌል በመከራ በሚፀኑ እንዴት እንደሚያፈራ ከዚህ ወጣት ህይወት ተረዳሁ፡፡ ለካ በጌታ ፊት የታወቀ በኢጋንንቱ አለም የሚያስፈራ አገልጋይ ለመሆን ጌታን መቀበል ብቻዉን በቂ ነበር፡፡ ይሄ ልጅ ለራሱ እንኳን አዲስ ክርስቲያን ነዉ፡፡ ነገር ግን አርበኛ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ዉስጥ ካሉ አገልጋዮች ሁሉ ጌታ ሞዴል አድርጎ ያየዉ ነበር፡፡ ይህ ወጣት ከዚያ በኋላ በአጭር ጊዜ ወደ አስራ አራት ቤተክርስቲያናት ሲተከል በቃ፡፡ እርሱ በሚያልፍበት መንገድ መናፍስቱ ላይ ሽብር ይሆን ነበር፡፡

በኋላም ይህ ወጣት የጠንቋዩ ልጅ የነበረችዉን ቀይ ቆንጆ የሆነች ልጃገረድ በቤተ ክርስቲያን ጌታ በተገኘበት ስነስርዓት አገባ፡፡ ቀጥሎም የሚያማምሩ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ልጅ ጌታ ሰጣቸዉ፡፡ አሁን በአካባቢዉ ታዋቂ አገልጋይ ሆኖ ይኖራል፡፡ እግዚአብሔር በኑሮ እና በሀብት ባርኮታል፡፡ እርሱ ግን ዛሬም የወንጌል ሰራተኛ ነዉ፡፡ ዛሬም ይመሰክራል፣ ቤተክርስቲያን ይተክላል፡፡

ጌታም ይህንን ሁሉ ካሳየኝ በኋላ ይህ ወጣት ትልቅ ሰዉ ሆኖ እየዘመረ ልጆቹንና ሚስቱን ይዞ ወደ መንግስተ ሰማያት ሜካ ዱሩን እየበጣጠሰ በእምነት እየዘመረ ሲሄድ ተመለከትሁት፡፡ ፊቱም በዚህ ሁሉ ዉጣ ዉረድ ውስጥ ያለፈ እስከማይመስል ድረስ ፊቱ ያበራ ነበር፡፡ እየገሰገሰ፣ እየመሰከረ በእምነት በበጉ ደም ሰይጣንን ድል ነስቶ ዘልቆ ወደ መንግስተ ሰማይ ሄዶ ተመለከትሁት፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ጉዞ ወደ ገነት እና መንግስተ ሰማያት

### የፍፁማን መንገድ

እኛም በጠባቡና የመንግስተ ሰማይ መግቢያ በሆነዉ በኢየሱስ መንገድ ከጌታ ጋር ወሰጤን ደስ እያለዉ በሀሴት ተሞልቼ በብርሃን ሉሏ ውስጥ ሆነን በፍጥነት እንጓዝ ጀመር:: በየመንገዱ በጉዞ የደከሙትን እያበረቱ በረግረግ ዉስጥ የተጣሉትን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ሆነው እየደገፉ በስራ እጅግ ተወጥረዉ የጌታን መላእክት አየኋቸዉ:: ጊዜዉን ለጨረሰውም ተጓዥ አረንጓዴ ካርድ ይሰጡት ነበር:: ወዲያውም ስጋውን እንደ ልብስ አውልቆ መንፈሳዊውን ስጋ ይለብስና በሁለት መላእክት በፍጥነት ወደ መንግስተ ሰማይ እንዲገባ ይደረግ ነበር:: ሰይጣንም በግ የመሰሉ ተከላዎችን ወደ መንገድ ሲያስገባ አየሁት:: እነርሱም ውስጥ ውስጡን እየሄዱ አውነተኛዎቹን በጎች ይነክሷቸውና ያስነክሷቸው ነበር::

አንዳንዱንም ከመንገድ አውጥተው ሊበሏቸው ሲሉ የጌታ መላእክት እየደረሱ ሲያስጥሏቸው አይ ነበር:: ተከላዎቹ ምንም እንኳን ባያስታውቁም በአይናቸው ይታወቁ ነበር:: አይናቸው አሻጥር ብቻ ነው የሚያየው በዚያላይ ወደ ግራ ወደ ቀኝ ይቃላውጣሉ፤ ያደባሉ:: ይሄ ነበር የተከላዎቹ መለያ:: በዚህም መንገድ ከጥቂት ጉዞ በኋላ እጅግ ምቹ የሆነ እና እንደ ሴራሚክ ንፁህ የሆነ ነጭ አስፓልት ዙሪያው በፍራፍሬ:- ማንጎ፤ ፓፓያ፤ ሙዝ፤ አቦካዶ፤ እፐል ወዘተ የሞሉበት፤ ሰው ሁሉ በፈለገ ሰዓት ጎራ እያለ የሚያርፍባቸው ዘመናዊ መቀመጫዎች ያሉት ማንም ሲፈልግ በዚያ የሚያልፍ ያለ ችግር የፈለገውን በነፃ መጠቀም የሚችልበት ሰፊ አስፋልት ላይ ደረስን::

እጆን ያዘኝ፤ በቀኙ ዳሰሰኝና ፍፁም አዲስ ሰው ሆኜ እንደገና ቆምኩኝ። ኋላም ና ልጄ አለኝና ጉዟችንን ቀጠልን። እየተጓዝን ሳለ ደረጃው እጅግ ብዙ ስለሆነ ብሉ በቀኝ እጁ ያዘኝና እንደሚንሳፈፍ ሆነን የመጨረሻው ደረጃ ላይ ስንደርስ ሁለት ግዙፍ የሚያማምሩ አይኖች ያላቸው መላእክት ረጃጅም ነጭ ክንፋቸውን እጥፈው ደረታቸውን በጥሩር ታጥቀው እግራቸው በነሃስ ግንቢሌ ከጉልበታቸው በታች ተሸፍኖ በሁለት በኩል የተሳለ ሰይፍ ይዘው በሌላኛው እጃቸው ጋሻና ጦር ይዘው በተጠንቀቅ ከቆሙበት እንዲሁም እበሩ ላይ የህይወት መዝገብ በቀኝ በኩል ይዞ ከቆመው መልአክ ጋር በደረታቸው ሰጥ ብለው ጌታን እጅ ነሱትና በፍጥነት በሩን ወለል አድርገው ሲከፍቱልን ታላቅ ብርሃን ሁሉን ስፍራ ፈጽሞ አበራው። በነገራችን ላይ ጌታ እራሱ ብርሃን ነበር።

የምንሄድበትም መንገድ አይን የማይወጋ ታላቅ ብርሃን ነበረው። ኋላም ከበሩ በወጣው ብርሃን ውስጥ ስንገባ እጅግ አረንጓዴ በሆነ መስክ ላይ ነጫጭ ልብስ የለበሱ የዘንባባ አይነት የወርቅ ዝንጣፊ በጭንቅላታቸው ላይ የደፉ እጅግ ብዙ የሰው ቁጥር ሊቆጥር የማይችላቸው የተለያዩ ቀለም ያላቸው በተለያየ የእድሜ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ይዘው

*ለጌታችን እግዚአብሔር ሆይ*

*አንተ ሁሉን ፈጥረሃል*

*ሁሉ ስላልካቸው ሆነዋል*

*የዘላለም ፈጣሪ ጌታ አምላካችን ሆይ*

*ክብርና ውዳሴ የበላይነት ለአንተ ብቻ ነው እያሉ ይዘምሩ ነበር።*

ተጋለውም ለጌታችን ሁሉም ወድቀው

*ለወደድከን*

*ከሃጥያታችንም በደምህ ላነፃኸን*

*ለአባትህም መንግስት ካህናት ላደረግኸን*

*ስለ እኛ ሰው ለሆንከው*

*ለሞትከው ከሙታንም ለተነሳኸው*

*ከይሁዳ ነገድ ለሆንከው አንበሳ*

*ማህተሙን ትፈታ ዘንድ ለቻልከው*

*ለታረድከው በግ*

*ለነገሥታት ንጉስ ለአልፋና ለኦሜጋ*

*ዘላለም ህያውም ለሆንከው*

*ኢልሻዳይ ጌታ*

*ኃይል ክብርንና ባለጠግነትን*

*ጥበብንና ብርታትንም*

*ልትቀበል ይገባሃል*

*በረከት ሃይልም ብርታትም*

*ምስጋናችንም ለአንተ ይሁንልህ ብለው እጅ ነሱት።*

መላእክቱም አዕላፋት ነበሩ። ሁሉም በደረታቸው ለጥ ብለው እጅ ነስተውት ኃይልም ምስጋና ክብርም ውዳሴ ልትቀበል ይገባሃል ብለው ሰገዱለት። ኋላም ብዙ የተለያየ ቀለም ያላቸው ህፃናት እየሳቁ ወደ እርሱ እሮጠው መጥተው ተጠመጠሙበት። የተወሰኑትን አንስቶ ከሳማቸው በኋላ እንደገና በመጡበት አኳኋን በአረንጓዴ የሚያምር በማሽን የተከረከመ በሚመስል

## ፃድቃን ሰማዕታት

እየተጓዝን ሳለ ሌላ የከበረ ግቢ ደረስን፡፡ ጌታ እበሩ ላይ ሲደርስ በሩ ወለል ብሎ ተከፈተ፡፡ በዚህ ያሉት ሰዎች የለበሱት ወርቅ ሲሆን በእንቁ የዘንባባ ዝንጣፊ መስሎ የተሰራ ጌጥ ጭንቅላታቸዉ ላይ አስረዋል፡፡ ፊታቸዉ እጅግ ያበራ ነበር፡፡ ጌታም እንዲህ አለኝ እነዚህ ለህይወታቸዉ ሳይሳሱ እራሳቸዉን ለወንጌል የሰጡ ናቸዉ፡፡ ህይወታቸዉን በወንጌል ምክንያት ያጡ፣ በከተሞች የታረዱ፣ በዘይት ተቀቅለዉ የሞቱ፣ ተሰቅለዉ የሞቱ ናቸዉ" አለኝ፡፡ ከዉጪ ያሉት ወደዚህ መግባት አይችሉም እነዚህ ግን ደምቀዉ በቅዱሳኑ ዉስጥ ሲንጎራደዱ ተመለከትሁ፡፡ ጌታም "ይሄ መኖሪያቸው ነው" ብሎ አለኝ፡፡

እጅግ ታላቅ በሆነ ድምፅም ጌታ ሆይ ደማችንን ተበቀልልን እንጂ እያሉ እጅ ከነሱ እና ከሰገዱ በኋላ አለቀሱ፡፡ ጌታም አብሯቸው በቁጭት ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ እና ትንሽ ታገሱኝ እበቀልላችኋለሁ አለና ወደ እኔ ዞሮ እንዲህ አለኝ፡፡ "በምድር ላሉት ንገራቸው፡፡ የቅዱሳንን ደም የሚያፈሱትን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ እበቀላቸዋለሁ፡፡ ፃድቃን ለሚያሳድዱ ወዮላቸው" ብሎኝ ጉዟችንን ቀጠልን፡፡ ቅዱሳኑም በደስታ እና በሆታ በብዙ ምስጋና በእልልታ መልካም መአዛ ያለው አምልኮ አቀረቡለትና መብረቅ፣ መደሰታቸውን ቀጠሉ፡፡ ከዚያም በሩ በእነርሱ ፍቃድ በራሱ ጊዜ ወለል ሲል እየወጡ በቅዱሳኑ ውስጥ እንደ ወርቅ ደምቀው ሲገቡ እና ሲያመልኩ ተመለከትን፡፡

ስለኖራቡ እነርሱ እንዲህ በነገሱበት ከተማ ይኖራሉ፡፡ ለልባቸው ብናገራቸውም አይታዘዙትም፡፡ ለመሪዎች አይገዙም፡፡ ይባስ ብለው ባገኙት ሃብት በትዳራቸው ላይ ይወሰልታሉ፡፡ ለልጆቻቸው እኔን ሳይሆን ሃብትን አውርሰዋቸው ነው የሚሞቱት፡፡ ልጆቻቸው እግዚአብሔርን በመፍራት እያሳደጉትም፡፡ እሞላትታው አሳድገው የከፋት ደቃ መዝሙር አይረዳቸው፡፡ ህይወታቸውን በማስመሰል ነው ያሳለፉት፡፡ ስለዚህ ያኔ በጥንት እኔን በተቀበሉበት ፍቅር ነው በጭንት የዳኑት አለኝ፡፡ ብዙ ፓስተሮችን እና አገልጋዮችንም በዚሁ ሰፍራ ማየት ቻልኩ፡፡

እነዚህን መረጃዎች ሙስሊም ከሆኑ ግለሰቦች እና ከሌሎች የእስልምና አገር ዲፕሎማቶች ጋር አብረው በድብቅ አዲስ አበባ ውስጥ ተከታታይ ስብሰባ በማድረግ ነበር የሚለዋወጡት፡፡ በተቻለ መጠንም ይህ ጉዳይ ወደ ተግባር እንዳይገባ የኢትዮጵያ መንግስትን ጨምሮ በተለያዩ ምእራብዊ ዲፕሎማቶች ሳይቀር መምከራቸውን ቀጠሉበት፡፡ ነገር ግን ይህ ሙከራቸው በሙሉ በኢትዮጵያው መሪ ውድቅ ሲደረግባቸው በመቆየቱ መሪውን በገንዘብ ለመደለል በተለያየ መንገድ ሙከራ ቢያደርጉም ሊሳካላቸው አልቻለም ነበር፡፡ በስተመጨረሻም በ2003 ዓ.ም መጋቢት ወር ላይ ኢትዮጵያ ግድቡን መገንባት መጀመሯን ይፋ አደረገች፡፡

በዚህ ጊዜ ግብፆቹ እጅግ ተደናግጠው በተለያየ መንገድ ኢትዮጵያ ላይ ጫና ማሳደር ጀመሩ፡፡ እንዲያውም በወቅቱ በአገራቸው የነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋት ያዛቸው እንጂ ምንንም ያህል መፈናፈን የማይቻልበት ሁኔታ ነበር የሚፈጠረው፡፡ ግብፆች ከያዙት እቅድ መሃከል አንዱና ዋነኛው ይህንን የኢትዮጵያን መሪ መግደል እና በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ሙስሊሞችን የተለያዩ አንጃዎችን እንዲያቋቁሙ በማድረግ አገሪቱን ማሸበር ነበር፡፡

እነዚህ አንጃዎች በኋላ ላይ ምስጢራቸው ተጋልጦ በኢትዮጵያ መንግስት መታሰራቸው ይታወቃል፡፡ ከዚሁ ባሻገር በ2005 ዓ.ም የረመዳን ፆም ፍቺ ወቅት እስከ 15 ሚሊዮን ሙስሊሞችን ወደ አዲስ አበባ በሳምንት ጊዜ ውስጥ በማስገባት ድንገተኛ የህዝብ ማእበል በመፍጠር በከተማይቱ ውስጥ ያሉ ቤተመንግስቶችን፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን፣ እንዲሁም የሬዲዮ ጣቢያዎችን በሙሉ በቁጥጥር ስር ማዋል የሚል እስትራቴጂ ነድፈው ሲንቀሳቀሱ መረጃው ቀድሞ በመንግስት ጆሮ በመግባቱ ሊከሸፍ ችሏል፡፡ ሆኖም ግን የመሪው ግድያ ጉዳይ ከተለያዩ የአረብ የሰለላ ተቋማት ጋር በመቀናጀት በአለም ዙሪያ ከሚደረጉ የተለያዩ አለማቀፍ ስብሰባዎች በአንዱ ላይ እንዲከናወን እጅግ ምስጢር ተደርጎ ተይዞ ነበር፡፡ በኋላም በግንቦት 2004 ዓ.ም 22ኛው የአለም የኢኮኖሚ ፎረም

በሚካሄድበት ወቅት ግድያው እንዲደረግ ተወስኖ ነገር ግን በሌሉ አቅጣጫ ቀደም ሲል መሪውን በገንዘብ ለማማለል ይደረግ የነበረውም ሙከራ እንደ አማራጭ ተይዞ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ በገንዘብ ለመደለል የተደረገው ሙከራ ፈፅሞ ሊሳካላቸው አልቻለም፡፡

ስለሆነም በዚሁ የስብሰባ ቀን እጅግ ረቂቅ የሆነ የጨረር መርዝ ተዘጋጅቶ ይህንንም ጉዳይ እንድታስፈፅም አንዲት የአረብ ዝርያ ያላት አሜሪካዊት ተመርጣ ነበር፡፡ በቅርብ እርቀትም አንድ የግብፅ የደህንነት ባለሙያ የጋዜጠኛ ባጅ በመልበስ የካሜራ ባለሙያነቱን የሚገልፅ የተጭበረበረ መታወቂያ በማሳየት ካሜራ በመያዝ መሪዎቹ መግለጫ በሚሰጡበት ሰዓት እየቀረፀ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በግብፅ የደህንነት መስሪያ ቤት በሻቢያ በኩል በሚረዱ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች አንድ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ መሪውን ለመሳደብ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ የዚህ ጋዜጠኛ ስድብም ሰውዬው ጨረሩ በሚወጋቸው ወቅት ድንገት የተለየ ባህሪ ሊያሳዩ ይችላሉ ይህም በአካባቢው ኃይሎች ላይ ጥርጣሬ ሊፈጥር ይችላል በሚል ሽፋን ለመስጠት ነበር፡፡ ምናልባት የተለየ ባህሪ ቢታይባቸው እንኳን በአደባባይ መሰደባቸው አበሳጭቷቸው ነው በሚል ወደ ሌላ ምርምር እና ጥርጣሬ እንዳይገባ ታስቦ ነበር ይህ የሆነው፡፡ ሆኖም ግን ተሳዳቢው ጋዜጠኛ ይህንን የግብፆች ተንኮል በፍፁም አላወቀውም ነበር፡፡

የግድያ ሙከራው የተከናወነበት ሂደት ይህንን ይመስል ነበር፡፡ ጋዜጠኛ መስሎ እጭበርብሮ ወደ ስብሰባው የገባው ግብፃዊው የደህንነት ሰው በካሜራው እየተመራ የመሪውን እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ይከታተል ነበር፡፡ በኋላም ያቺ የአረብ ዝርያ ያላት አሜሪካዊት አስተናጋጅ የያዘችውን የጨረር መሳሪያ ተሳስታ በጋናው ፕሬዝዳንት ላይ በማድረጓ ይህ የደህንነት ሰው በካሜራው ላይ በተገጠመው ጨረሩን በሚያሳይ ማይክሮስኮፕ ተመልክቶ የእጅ ምልክት ቢያሳያትም እርሷ ግን ያለማቋረጥ በጋናው ፕሬዝዳንት ጭንቅላት ላይ ጨረሩን ተከለችው፡፡ በነገራችን ላይ ይህ ጨረር ፈፅሞ በሰው አይን የሚታይ ባለመሆኑ ማንም ሰው ሁኔታውን ማወቅ አይችልም ነበር፡፡ በኋላም ይህ የደህንነት ሰው ካሜራውን

እለት የጤናቸው ሁኔታ ተባብሶ እስከ ሞት ድረስ እንደሚያደርስ ከተረዱ በኋላ በመኝታቸው ሳሉ በልባቸው ያኔ በወጣትነት ያመልኩት የነበረውን አምላክ "ጌታ ኢየሱስ እባክህ ሀጢያቴንና በደሌን ይቅር በለኝ አንተ የእውነት መንገድ ነህ" እያሉ ወደ እግዚአብሔር በልዩ ተመስጦ ሲፀልዩ ተመለከትሁ፡፡ ኋላም ነፍሳቸው ወደ እግዚአብሔር ፊት ሲገባ እና ተቀባይነት ሲያገኝ ሁለት ነጫጭ መላእክቶች ነፍሳቸውን ይዘው ወደ ገነት ሲያመጧት ልክ በሰጋ እንዳሉ በጤንነት እንደማውቃቸው ሆነው ተመለከትሁ፡፡ ጌታም ንግግሩን በመቀጠል "የመጀመሪያው ገነት የገባ የኢትዮጵያ መሪ ሆኖ ነው እንግዲህ እዚህ ያለው" ሲለኝ እኔም እያየሁት ስለነበር እየኘና ለጌታ ወድቆ ከሰገደ በኋላ እባክህን ወዳጄ አናግረኝ አለኝ፡፡ ጌታም ሄደና ጭንቅላቱን አሻሸው፡፡

እርሱም እንዲህ አለ "እባክህ ጌታ ሆይ ልጆቼንና ቤተሰቦቼን ወደ አንተ እንዲመጡ አድርግልኝ" አለው፡፡ ጌታም "ከሰመና ከታዘዙ ዘሬም ምህረቴ ብዙ ነው" አለው፡፡ "በዙሪያቸው መልእከተኞች አሉላቸው እነርሱን ይሰሟቸው መልእከት ካለህ ይኸው ንገረው ያድርስልህ" ሲለው ወደ እኔ ዞሮ "እባክህን ዞር ብዬ እይቻቸው የማላውቃቸውን ዘመዶቼን የኢትዮጵያ ህዝብ ይንከባከብልኝ እደራ ሚስቴን ልጆቼን ደግሞ እባካችሁ ወደዚያ እሳት እንዳትሄዱ እባካችሁ ሁሉም እውነት ነው ሳያችሁ ደግሞ ናፍቄአለሁ ኑ ወደ ጌታ ወደ ኢየሱስ እርሱ ነው መንገዱ የተውኩላችሁ ሃብትና ክብር ጠፊ ነው፤ የሚቀር ነው አደራ፤ አደራ" አለኝ፡፡ በኋላም ጌታ ሲዳስሰው ፍጹም ደስተኛ ሆነ፡፡ እንደ ወጣትነቱም መመላለስ ጀመረ፡፡

## የገነት ከፍታ

በገነት ውስጥ እየተጓዝን ወደ አንድ የሚያምር ከፍታ ስንደርስ ከፍታውም በብዙ ምንጮች ተከብቦ በመንቀሳቀስ እና በማሽብሸብ ላይ ነበር። በላዩ ላይም ባለው የሚያምር አዳራሽ ውስጥ ሆሞሪያቱና ነብያቱ በከበሩ ወንበሮች ላይ ተቀምጠው በመንፈሳዊ ቅኔ እንደ ወንዝ በፊቱ እየፈሰሱ ሲዘምሩ አየናቸው። ሁሉም የሚያምር የወርቅ ልብስ በየደረጃቸው ለብሰው ነበር። የጌታ እናትም ማርያም አብራቸው ነበረች።

ሁሉም በደረታቸው በመውደቅ እጅ ከነሱት በኋላ "ታርደሀልና ይገባሃል፣ ክብርን ልትቀበል ይገባሃል" እያሉ ከወደቁበት ተነስተው ቆሙ። እርሱም በፈገግታ እንደ ወንድም እያቀፈ የከበረ ሰላምታ አቀረበላቸው። በኋላም እነርሱም በአምልኮ ዝማሬ ባማረ ዜማ ቅኔ መዝመር ያቀረቡለት ጀመር። እኔም አይኔን እያማተርኩ በመፃሃፍ ቅዱስ የማውቃቸውን የእምነት አርበኞች ማየት ጀመርኩ።

ሁሉም ቅዱሳን ነቢያት እና ሐዋርያት በዚህ ስፍራ ነበሩ። የሁሉም ፊት የሚያበራ ሆኖ እንደ ህፃን ልጅ ነበር። ፀጉራቸውም ከበረዶ ይልቅ ነጥቶ ከብርን አላብሷቸው ነበር። በራሳቸውም ላይ በወርቅ እና በእንቁ የተንቆጠቆጠ ዘውድ አድርገው ነበር። አብርሃምን ሳየው በፍፁም መሰጠት በመንፈስ እየዘመረ ተመለከትሁ፤ ማርያምንም ሳያት በብዙ ደስታ በመንፈስ ሆና ታመልከው ነበር። ከዚያም ጳውሎስና ሙሴ፣ ኤልያስ መሃል ቆመው ዝማሬውን እየመሩ ያስዘምሩ ነበር። በኋላም አብርሃም፣ ጴጥሮስና የጌታ እናት ማርያም እና ጳውሎስን ተኳቸውና አምልኮ እና ዝማሬውን መምራቱን ቀጠሉ። ፊልመው ነበር የሚያመልኩት።

እንደዚህ አይነት አምልኮ በምድር አይቼ አላውቅም እናም እኔም ተማርኩ አብሬያቸው ማምለኬን ቀጠልኩ። ሁሉም የተለያዩ እንደ ማርሽ ባንድ አይነት

የሙዚቃ መሳሪያ ነበሯቸው፡፡ ግማሹ ሲዘምር ሌላው ሙዚቃ ይጫወት ነበር፡፡ ይሄ ውህደት መዝሙሩን በሚመሩት በጴጥሮስ በማርያምና በአብርሃም የጣት ምልክት ብቻ ነበር የሚከናወነው፡፡ አንድም ገንፍ ሳይል ያማረ ዜማ ወደ ጌታ ፊት ወጣ፡፡

ዝማሬውም እንዲህ የሚል ነበር

*ቅዱስ ቅዱስ ነህ አንተ ጌታ አምላካችን ሆይ፤*
*አንተ ሁሉን ሰርተሃል ሁኑ ስላልካቸው ሆኑ፤*
*ከነገድ ከቋንቋ ህዝቦችን ይዋጅ ዘንድ*
*አዳኝ የሆነውን ልጅህን የፍቅርህ ምሳሌ የሆነውን ሰጠኸን፤*
*ማን አለ ማህተሙን የሚፈታ*
*አንተ ግን ችለሃል የእኛ ጌታ*
*ለወደደን ከሃጢያታችንም በደሙ ላጠበን*
*ሃይልና በረከት ክብርም ባለጠግነትም*
*ለታረደው በግ ለኢየሱስ ክርስቶስ*
*እስከ ዘላለም ይሁን፡፡*
*የአለም መንግስት ለእርሱ ለጌታችን ሆነች*
*ስለዚህ ተመስገን ለሰው ልጆች ሁሉ ሰላም ይሁን፤*
*በምድር በዲያቢሎስና በጭፍሮቹ ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ*
*የቅዱሳንን ደም ትበቀል ዘንድ ዘመን መጣ፤*
*አገልጋዮችን ታጠቅ ዘንድ ዘመን መጣ፡*
*ለሊትና ቀን የወንድሞቻችን ከሳሽ ጥለሃልና ዘመን መጣ*
*በሰማይና ምድር ሃሴት ሊደርጉ ክርስቶስ ጌታ ነግሷልና፡፡*

መንፈስ ህዝቡ ሁሉ ተቀብሎት ያመልክ ነበር። ኢየሱስን በሚያወድስ መዝሙር እና ቅኔ እየኖሩ በአምልኮ ተሞላ። ሁሉንም ከፍ ብለን ስናያቸው በብሩህ ደመና እንደሚመላለሱ ሆነው ነበር። ሃዘን የለም፤ በሽታ የለም፤ ጭንቀት የለም፤ ጭንገቱ የለም፤ እንዲሁም የፊት መጨማደድም አይታወቅም። ሁሉም ሰው ክብር ነበር የሚታየው ስለዚህም ሰው ሁሉ ያለማንም ትትጓች ያሰበውን በነፃነት እና በማድረግ ብቃት ጭምር ከእግዚአብሔር ቅድስና ተካፋይ ሆኖ የሚኖርበት ስፍራ መሆኑን ለማወቅ ቻልሁ።

- የሚከድኑ ዘማሪዎች ይነሳሉ ካለኝ በኋላ እነዚህ በዚህ ስፍራ ያየሃቸው የዳኑት እንደዚህ ባለ ትጋት ውስጥ አልፈው ነው ብሎኝ ጉዟችንን ቀጠልን፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## የእግዚአብሔር ዙፋን እና አዲሲቱ ኢየሩሳሌም

### አዲሲቱ ኢየሩሳሌም

እየሄድንም ገነትን መሀል ለመሃል አቋርጦ የሚያልፍ የህይወት ዉሃ ወንዝ ተመለከትን:: ከዚህ የህይወት ዉሃ አንዴ የጠጣ ሰዉ ዳግመኛ አይጠማም ነበር:: ኋላም ከምድር ድል ነስተዉ የሚመጡ አዳዲስ ሰዎች ሁሉ እየተሻሙ ሲጠጡ ተመለከትሁ:: በወንዙ አንፃር በቀኝ በኩል እየተጓዝን ሳለ ወደ አዲስ ሰማይና ምድር ውስጥ ዘልቀን ስንገባ ሌላ አዲስ እጅግ ውብ እና በመሰራት ላይ ያለች አዳስ የምታምር ከተማ ተመለከትሁ:: ደጃፏ፣ ቅጥሯ በሙሉ እንደ ወርቅ የሚያበራ ነው:: ንፁህ ወርቅም ነበር:: እጅግ ብዙ መላእከትም በዙሪያዋ በስራ ላይ ነበሩ:: እያንዳንዱን ደረጃ ሲወጡ ከብርን የሚጨምሩ ብዙ ደረጃዎችን ካለፍን በኋላ ወደ በሩ ስንቀርብ እዉቆ ወለል ብሎ ተከፈተልን::

በቅጥሩ ላይም በቅጥሩ ዉስጥም በስራ ላይ የነበሩ መላእከት በደረታቸዉ ለጥ ብለዉ ለጌታ ሰላምታ ሰጡ:: ክብር ሊታረደዉ በግ ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን፤ ምስጋናም ለአምላካችን ለእግዚአብሔር፤ ብለዉ ተነስተዉ በተጠንቀቅ ከቆሙ በኋላ ጌታ በብዙ ፍቅርና አክብሮት ሰላምታ ሲሰጣቸዉ ወደ ስራቸው ተመለሱ:: እኛም እንደ መስታወት በሚያበራዉ የወርቅ አስፓልት እየተራመድን ወደ ዉስጥ መጓዝ ቀጠልን:: መላእከቱ ሁሉ ግን በስራ ተጠምደዉ ነበር::

ጌታም ሁልጊዜ እየተቀያየረ ምስል የሚያሳይ በከተማ ዉስጥ ወደ ተቀመጠ ትልቅ እስክሪን አመለከተኝና እስክሪኑን ለእኔ በሚገባኝ መልኩ መልእኩ እንዲያስረዳኝ ነገረው:: ከዚያም በእስክሪኑ ላይ ማንም ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ "የከተማይቱ ዲዛይነር እግዚአብሔር ነው" የሚል ፅሁፍ ተመለከትሁ።

ነበሩት፡፡ እነዚህ መጋዝኖችም ዙሪያቸዉ አጠቃላይ ከከበረ እንቁ የተሰራ ሲሆን ወደ የትኛዉም ሀዋ ሊጓዙ የሚችሉም ነበሩ፡፡ በየትኛውም ሰፍራ የሚከናወነን ነገርበሙሉ የፈለጉትን መርጦ ለመከታተል የሚቻልበት በሳሎን ውስጥ እጅግ ዘመናዊ ከሰው ቁመት ሁለት እጥፍ የሚበልጥ እስክሪን ነበር፡፡ ህያው የሆኑ ፎቶዎች፣ ዘመናዊ ላይብራሪና ድርወሮች፣ ሸልፎች ወዘተ በውስጡ የተለያዩ የቤት እቃዎች ነበሩበት፡፡ ሁሉም ቁሳቁሶች ከወርቅ፣ ከእንቁና እጅግ ከከበሩ መአድኖች፣ ከከበሩ ድንጋዮች ነበር የተሰሩት፡፡ በዚያ ላይ እንደየሰዉ ፍላጎት የሚቀያየሩም ነበሩ፡፡

አንድ ሰው ጠዋት እንደዚህ አይነት ቤት ውስጥ ከነበረ ትንሽ ቆይቶ ደግሞ የፈለገውን አይነት አድርጎ መኖር ይችላል፡፡ ከማንኛውም አደጋ ነፃ ነው፡፡ ረሃብ እና ችግር፣ ራቁትነት፣ ህመም፣ ሃዘን፣ ጨለማ፣ በዚህ አይታወቁም ነበር፡፡ ውጪ ላይ መስኩ የመኖኛ ገንዳ ነበረው፡፡ ከተለመሙ ጀምሮ መጠኑን እንደ ነዋሪው ፍላጎት መቀያየር ይቻላል፡፡

ተጦሎም ሌሎች እንደ የውሻ ቤት የመሳሰሉ በየቤቱ ደጃፍ አጠገብ አነስተኛ ቤቶች ነበሩ፡፡ ነገር ግን በውስጣቸው በገነት በሞኙንት የዳኑትን ቅዱሳኖች ልክ በትልልቁ ቤት ፊት ለፊት ቀሞጪው በቦታና በሁኔታ ተወስነው ያለምንም ሽልማት ባዷቸውን በበፅት ሆነው አመለከት ነበር፡፡

ቅዱሳኑ ያለ ሀሳብ ሁልጊዜ አዲስ የሆነውን እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እያዩ በመገረም ማምለክና ማወደስ ብቻ ነው ስራቸው፡፡ በኋላም ቤቱን እየጎበኘሁ ባለ በቤቱ ውስጥ የሚስተናገዱ ሰዎችን አመለከት ነበር፡፡ ከእጃቸው በሚወጣ ጨረር መሳይ ነገር እንድ ወንበርና ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብለው የሚፈልጉትን እቃ እየሩን እንደመቅዘፍ እያሉ ትልልቅ እቃዎችን ሳይነኩ ሲያንቀሳቅሱና ለሚፈልጉት ግልጋሎት ሲያውሉት አመለከት ነበር፡፡

"በሻረ መልኩ በትዕበት በሁሉ ሰፍራ በተገኘ ልክ ኢድንና ሰፍቶ ማየቴ ያሰደንቀኝ ነበር። በመንፈሳዊው አለም ውስጥ መፍጠንም ሆነ መዘግየት እኩል ነበር። ተመልሰም እጄን ይዞ ወደ ውስጥ ገባና በሱሗ ውስጥ ምቹ በሆነ ወንበር ላይ አስቀምጦኝ እርሱም ተቀመጠ። ወዲያውም በልቤ "ብርሃናት ሁሉ ያወሩታል እንዴት የሚገርም አምላክ ነው!" እያልኩ እያሰብኩ ሳለሁ ከአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሰንወጣ እኔ ግን በውስጤ ከዚህች ውብ ከተማ ላለመሄድ አመንትቼ ሳለ ሳልጠይቀው እራሱ "እይዞህ ልጄ በክብር በምትህ አከብረኸን ለዘለአለም ትኖርባታለህ" በማለት አፅናንቶኝ ሰንጓዝ መላእክቱም በስራ ላይ እንዳሉ ሆነው ሰላምታ ከአንገታቸው ጎንበስ በማለትና በአክብሮት ለጌታ አቀረቡለት።

እሁንም ሲፈጥራቸው ነበር የተመለከትነው፡፡ ያለ ምንም ጣልቃ ገብነት ቀጥታ በእርሱ ፊት ህያው ሆነው አባት ለልጆቹ እንደሚያወራቸው በምድር ስላሉት የሰው ልጆች እንዴት በአምሳሉ እንደፈጠራቸው፣ እንዴት እንደሚወድዳቸው፣ ሁልጊዜ ያወራቸዋል፡፡ "አንድ ቀን ልጆቼን በመጨረሻው ቀን ለፍጥረት ሁሉ እገልጥላቸዋለሁ፡፡ ልጆች አሉኝ፤ የእኔ የሆነውን ሁሉ የሚወርሱ፤ እናንተንም በድድቅ የሚያስተዳድሯችሁ ይገለጣሉ፡፡ ልጄ ቀኔ በተበቡ ብዙዎችን ይማርካል፤ ማደሪያዬ በእነርሱ መሃከል ይሆናል" እያለ ሲያወራቸው እሰማ ነበር፡፡

እግዚአብሔር የሚያወራው ሁሉ ውስጤን ያዘልለው ነፍሴን ያስፈነድቃት ነበር፡፡ እርሱ ማን ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ውስጥ ሆኖ ድምፁም እንደ ብዙ ውሆች ድምጽ ሆኖ በሚያስፈራ፣ በስልጣንና በፍቅር ንግግር ሲናገር እኔን ጨምሮ ፍጥረት ሁሉ ይሰማው ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ ከዋክብቶችና ጋላክሲዎች በፊቱ ይዘልሉ፤ ይፈነድቁ ነበር፡፡ ሁልጊዜም አይኖቹ በልዩ አትኩሮት በምድር የሚመላለሱትን ሰዎች ያዩ ነበር፡፡ ያንጊዜም ክርስቶስ ልክ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሚሆነውን አይነት ምስል ምድርን፣ የሰው ልጆችን በሙሉ ሸፍኖ ጌታ በመስቀል ላይ እየቃተተ ተመለከትሁ፡፡ ያን ጊዜ ታዲያ

*በምድር ላሉ ሁሉ ለሰው ልጆች ለሰዎች*

*አዳቻው ተከፈለ ፍርዳቸው ተሻረ*

*በአንድያ ልጅህ ዲያቢሎስ አፈረ*

*ስምህ በምድር ሁሉ አሁንማ ተከበረ*

*ፍጥረት ሁሉ ለአንተ ምስጋና ዘመረ*

የሚል መዝሙር በሀዋ ውስጥ ያሉት ጋላክሲዎች፣ መላእክቱና ከዋክብቶች በሚያገምር ዜማ ይዘምሩ ነበር፡፡ ያለ ከልካይ ተወንጫፊ ኮከቦች ከሰማየ ሰማያት እየተወናጨፉ በሽበሽባ ተሞሉ፡፡ ያለማቋረጥ እልልታና 'ልክ ነሆ' የሚል ጭብጨባ፣ ፉጨት ታላቅ ሃሴትና ደስታ ሲሆን ተመለከትን፡፡

መናፍስቱን ሲመታ እንመለከት ነበር። የተለያየ ቅርፅ ያላቸው ዘንዶዎች በአየሩ ላይ ሲሞቱ ይታይ ነበር።

ከዚያም መላእክቱ ወደ አንዳንዶቹ በመብረር በእሳት ሰይፍ እንገታቸውን ከላያቸው ሲቆርጡ እንመለከት ነበር። ጌታም እንዲህ አለኝ። "መብረቅን የሚልኩት መላእክቶቼ ናቸው። ውጊያው ሁልጊዜ የተለመደ ቢሆንም ነገር ግን መላእክቱ ከውሃና ከእሳት የተሰሩ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ዲያቢሎስ የበለጠ በምድር ቁጣቁስ ውስጥ እየተደበቀ ቅዱሳንን እንዳያጠቃ ነው ይህንን አይነት የውጊያ መንገድ የሚታየው። ስለዚህ በደመና ውስጥ አንዳንዴ ለሰው በሰጋ አይን እንኳን የሚታዩ ዘንዶዎች እንገታቸው ተቆርጦ ወደ ምድር ተንጠልጥለው ይታያሉ" አለኝ።

ከልጅነቴ ጀምሮ አንዳንዴ ታላቅ ዝናብ ከዘነበ በኋላ እውነተኛ ዘንዶ የሚመስል ጭራውን ወደ ምድር አንጠልጥሎ በደመናው ላይ እመለከት የነበረውን አስታወሰኝ። እንዲያውም በእኛ አካባቢ ይህ የሰማይ ዘንዶ ምድርን በጭራው ሲነካት ምድር ትገለባበጣለች የሚባል አፈ ታሪክን አስታወሰኝ። አሁን ግን ጌታ ያለኝ እውነተኛው ነበር። በዚህን ጊዜ መናፍስቱን በተደጋጋሚ መላእክቱ ጨፍጭፈዋቸው አየሩን በዘንዶ ቁርጥራጭ ሞልተውት ነበር። በነገራችን ላይ መላእክቱ የሚወረውሩት ፍላፃ ጫፉ ላይ ብረት መሳይ ሹል መውጊያ ያለው የጦር መሳሪያ ነበር።

እየተመለከትንም ይህ ፍላፃ አንድን የዲያቢሎስ ጭፍራ ሲያሳድደው በፍጥነት ወደ አንድ ትንሽዬ ሬዲዮ ወደ ያዘ ወጣት ልጅ ስር ገባ። ይህን ጊዜ በልጁ ውስጥ የተከማቹ የክርስቶሳውያን ጠላት አድርገው እያሰለጠኑት የነበሩ ከፋ መናፍስት ወደ ውስጡ ዘልቀው ነበር። እጅግ ከፋትንና ጥላቻን ሞልተው በውስጡ ይኖሩ ነበር። ታዲያ ይህ ወጣት ላይ ከላይ በመብረቁ የሚሳደደው መንፈስ ሲገባበት ልጁም ወደ ውስጡ ከገባውና በውስጡ ከነበሩት መናፍስት ጋር አብረው ተቃጥለው ሲሞቱ እመለከት ነበር። እንዲሁም እነዚህን እርኩሳን መናፍስት ከአየሩ ላይ መላእክቱ በመብረቅ ፍላፃ ሲያሳድዷቸው እግዚአብሔርን በፍጥረት ለማሳጣት እየሮጡ ወደ ህፃናት እንዲሁም ወደ እንስሳት እና ወደ ቤቶች ውስጥ ተጨንቀው ይገቡ ነበር።

አድርግልኝ፣ አድርግልኝ እኝ፣ እኛ በሆነ በሉት ተይዘው ተመለከትኳቸው። ጌታም እሰምርዬን ከፍቶት ነበርና እያንዳንዱን ነገር በያለበት አቅጣጫ በተቀመጥንባት የብርሀን ሉል አማካኝነት ማየት እችል ነበር። ጌታም እንዲህ አለኝ "ከብዙ መድረኮች የእኔ ምዕላት መሰበክ አቆሟል። ከዚህ ይልቅ ብዙዎች ጠፊ ለሆነው ለምድራዊ ስኬት ብቻ ይከተሉኛል። የእኔን ምኞት የማትሰብክ ቤተክርስቲያን ደግሞ እኔ ሙሽራዋ ያልሆንኩባት ቤተክርስቲያን፣ ቤተክርስቲያን አይደለችም የስብሰባ ቦታ እንጂ። እኔ በባሪያዎቼ በኩል የገለጥሁትን የምኞቴን ተሰፋ ዘንግተው እስከየት ለመጓዝ ነው? በእርግጥ እመጣለሁ የሚሰማ ካለ አሜን ማራናታ ጌታ ሆይ ቶሎ ና ይበል" ሲል እኔና የነበርንባት ሉል ሳንመካከር በአንድ ድምፅ "አሜን ማራናታ ጌታ ሆይ ቶሎ ና" በማለት እንደበታችንን ስንከፍት ፍጥረት ተስማምተው "አሜን ማራናታ በክብር ከፍ በል እምን ተገለጥ" አሉ፤ መላእክቱም ተስማምተው "በአያሟ ላይ ተቀምጠህ የቅዱሳንን ደም ልትበቀል እባክህ ጌታ ሆይ ፍጠን" ሲሉት፤ አየሩ ሁሉ በሰላም ተሞላ።

ልክ ሲነጋጋ ሲል እንደሚሆነው ሰማዩ አቅልቶ ነበር። የጌታችን ፊትም እጅግ በራ ያንጊዜ ቅዱሳን ከምድር "ናፍቀንሀልና ፊትህን እንየው፤ ይህ ምድር ጊዜያዊ ነው። አገር አለን፣ ጌታ አለን፣ መጥቶ ከሙንቅ ከመከራ የሚያድነን፣ የሚገላግለን። በእርግጥ እርሱ ይመጣል፣ ያኔ ሀዘናችን ያበቃል፣ አሜን ጌታ ሆይ ና" እያሉ ብዙዎች ነቅተው መጠባበቅ ጀመሩ እኛም ተሳፍረንባት በነበረችው የብርሃን ሉል ወደ ገነትም እሳት በጠፈር ውስጥ ጉዞ ቀጠልን።

በእኔ እምነው በህይወት ሳሉ ንስሃ ካልገቡ ንገራቸው ዋጋ ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ በመጨረሻው ቀን እድል ፈንታቸው ከሰይጣንና ከመላእክቱ ጋር በዲን እሳት መቃጠል ነው" ብሎኝ በመጣንበት በኩል ከጭለማው ዋሻ ውስጥ ወጥተን ወደላይ በህዋ ላይ መሄድ ጀመርን፡፡

ተነፍረን የነበርንባት የብርሃን ሉል "ጌታዬ አንተን ስለቸርነትህ፣ ስለደግነትህ፣ ስለፍቅርህ፣ ለአንተ የማይገዛ ማነው? አንተን የማያምን ሰው ሆኖ እንዴት ይኖራል? ሰው የሆንከው ለእነርሱ አይደል እንዴ? ጉድ ነዉ ይሄንን ሁሉ ፍቅር ቻል የሚል ካለ!" አለች እያዘነች፡፡ እኔ ደግሞ በምድር የሰዉ ልጆች እንዴት ልባቸዉ እንደ ደንደነ ታወሰኝ እና ስተከዝ ጌታ የልቤን አዉቆ እንዲህ አለኝ "ባሪያዬ ልጄ ንገራቸዉ ቢሰሙህ ይጠቀማሉ ባይሰሙህ የተደገሰላቸዉን ድግስ ንገራቸዉ፡፡ ከፈለጉ አመፀኛዉም ወደፊት ያምፅ፣ እርኩሱም ይርከስ፣ ፃድቁም ይፅደቅ፣ ቅዱሱም ይቀደስ፣ ለሁሉ እንደየስራዉ እከፍለዋለሁ፡፡ እነሆ በቶሎ ስለምመጣ ለሁሉ እንደየስራዉ መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ በእጄ ስለሆነ አትጨነቅ፡፡ ለሚሰሙህ ሁሉ እነሆ ጌታችሁ በቅርብ ይመጣል በላቸዉ፡፡ አገልጋዮቼንም ህዝቤን አፅናኑ አበርቱ በልልኝ፡፡ በኑሯችሁ ምሳሌ ሁኑ፣ አይኖቻችሁንና እጆቻችሁን ምድራዊ ከማድረግ ተቆጠቡ፣ ምፅአቴን ሰበኩ፣ አዳኝነቴን አውሩ፣ በላቸው" አለኝ፡፡ እኔም እሺ ታዬን ሰግጄ ገለጥሁለት፡፡ ኋላም ከፍታችን እየጨመረ ሲሄድ ከጠፈር ሙሉ ለሙሉ ወጣን፡፡

ወደታች ስንመለከትም ጠፈር ከተራራ ላይ ሆኖ በማታ እንደምትታይ በዘመናዊ መብራት ያሸበረቀች ከተማ መስሎ ታየን፡፡ ቀለሙም ፒንክ ከለር ሆኖ በነጫጭ ብርሃናት አሸብርቆ አምሮ ይታየን ነበር፡፡ በመቀጠልም የብርሃን ሉላችን ፍጥነቷን በመጨመር ወደ ላይ ትጓዝ ጀመር፡፡

# የፍርድ ዙፋን

ከፍታችን እየጨመረ ስንጓዝ ሳለ እጅግ ደማቅ በሆነ ብርሃን የተሞላ ብሩህ ደመናን አልፈን ወደ ሌላ ብርሃን ውስጥ ስንገባ እጅግ የተንጣለለ አደባባይ ተመለከትሁ፡፡ በመሃከሉም በብርሃን የተሞላ ታላቅ ዙፋን ተመለከትሁ፡፡ በላዩም ላይ እግዚአብሔር ተቀምጦበት መንፈስ ቅዱስም እርሱን ከብቦት ነበር፡፡ በቀኙም አዲስ ነጭ ዙፋን ነበረበት፡፡ ይህም ዙፋን ሰው ሁሉ ሊያነብበው በሚችል ቋንቋ 'የፍርድ ዙፋን' የሚል ፅሁፍ ተፅፎበት ነበር፡፡ በእእላፋት መላእክት አደባባዩ ተከብቦ ነበር፡፡

በቀኝ በኩል ደማቅ በበጉ ደም ልብሳቸዉን ያጠቡ እእላፋት ቅዱሳን ተመለከትሁ፡፡ ፍፁም ንፁህ ነጭ ቀሚስ መሳይ እግራቸዉ ድረስ የሚደርስ 'የፀጋ ልብስ' የሚል ፅሁፍ ያለበት ልብስ ለብሰዉ ነበር፡፡ በግራ በኩል ደግሞ እጅግ ልብሳቸው የቆሸሸ፤ በሃዘን ተቆራምደው የሚተከዙ፤ እና ፍርዳቸውን የሚጠባበቁ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፡፡ በቀኝም በግራም የቆሙት ሰዎች በስጋ ትንሳኤ ተነስተው ነበር በፊቱ የቆሙት፡፡

ኋላም ወደ አደባባዩ ስንደርስ የብርሃን ሉላችን በአደባባዩ ጠርዝ ስታርፍ ከዉስጧ 'የፅድቅ በትር' የሚል ጽሁፍ ያለዉ ማቶ ላይ ጠፈር እንደ አለም ካርታ ሉል የምትሽከረከርበት ከንፁህ ሀብረ ቀለም እንቁ የተሰራ የሉል ማስቀመጫ ያላት፤ ሀያዉ የሆነች የለመለመች በትር ይዞ ጌታ ወደ ዙፋኑ መራመድ ሲጀምር እኔንም አንድ መልአክ መጥቶ ወደ ቅዱሳን እንድቀላቀል አመለከተኝ፡፡ እኔም ፈጥኜ ወደ ቅዱሳን እንደገባሁ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠዉ ዉጪ ሁሉም ወድቀዉ ለጌታ ከሰገዱለት በኋላ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠዉ እጅግ በፈገግታ ተሞልቶ ለክብሩ ቆሞ እጁን ዘርግቶ "ውድ ልጄ በዚህ ተቀመጥ" ብሎ ጌታን በዙፋኑ ቀኝ ባለው በአዲሱ እና በነጩ ዙፋን ላይ አስቀመጠዉ፡፡

በመቀጠልም እግዚአብሔር እጅግ በሚያስፈራ እና በሚያስገመግም ድምፅ ይናገር ጀመር:: እንዲህም አለ "ፍርዱ እውነተኛ ነውና ይገባዋል:: ባሪያዎቼና መላእክቶቼ እንዲሁም እኔን የምትፈሩ ሁሉ ታናናሾችና ታላላቆች ሁላችሁ ላዳናችሁ ምስጋናን አምጡ" ካለ በኋላ ግርማን የተሞላ የክብር እና የምስጋና ካባ ለጌታ ደረበለት:: የፅድቅንም መጎናፀፊያ አለበሰው:: በጭንቅላቱም ላይ የብርሃን ዘውድ አጥልቆለት "ጉልበት ሁሉ ለእርሱ ይንበረከክ ዘንድ ምላስም ሁሉ ክብርን ያመጣ ዘንድ ታገዟል" አለ::

ያኔ ታዲያ ቅዱሳኑም ሁሉ "ሃሌሉያ" እያሉ በእልልታ እና በሆታ "ይገባዋል ግርማ ተላብሷል የምስጋናን ካባ ደርቧልና ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላካችን ነግሷልና ክብር ለበጉ ከሀጢያታችንም በደሙ ላጠበን በአባቱም መንግስት ካህናት ላደረገን ምስጋና ዉዳሴ ለሰሙ ይሁን" ሲሉ መላእክቱና በእግዚአብሔር ዙፋን ዘርፍ ያሉት ፍጥረታት ሁሉ "ይገባዋል መፅሃፉን ይወስድ ዘንድ ማህተሙን ይፈታ ዘንድ ችሏልና በረከትና ሀይልም ምስጋናም አምልኮ ሊቀበል ይገባዋል" አሉ:: ሁሉም "ክብር ምስጋና ለአንተ ይሁን ሀሌ ሉያ" እያሉ መዝሙራቸዉን በመቀባበል ሲዘምሩ እግዚአብሔርም "ይገባዋል፣ ይገባዋል" ይል ነበር::

በኋላም በነጩ ዙፋን የተቀመጠው ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ስራው መጠን ዋጋውን ሲያከፋፍል ተመለከትሁ:: ብዙዎች እያፈሩ ሲመለሱ እመለከት ነበር:: አንዳንዶችም የልፋታቸውን ዋጋ ይቀበሉ ነበር:: በኋላም በግራው ለነበሩ "እናንተ አመፀኞች ፅድቅን ጠልታችሁ አመፅን ወድዳችኋልና ለሰይጣን እና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው ወደ ዘላለም ጥፋት ሂዱ" ሲላቸው ከውስጣቸው አንዳንዶቹ "ጌታ ሆይ አንተን አገልግለንሃል እኮ! ይህ ስፍራ አይገባንም የተለያዩ ድንቅ እና ተአምራት በስምህ አከናውነናል" እያሉ የሰሩትን ስራ ይቆጥሩ ነበር:: እርሱ ግን "በመንፈስ ጀምራችሁ በስጋ የጨረሳችሁ አይደላችሁምን? ስለዚህ ከስጋ ሞትን እጨዳችሁ ሂዱ ፊፅማችሁ ከፊቴ" በማለት ብዙ ስራቸውን በመውቀስ ዋጋቸውን

ከምድር እንደተሰበሱ ካሳወቃቸው በኋላ ሁሉም በመላእክቱ ተይዘው ወደ ገሃነም እሳት ሲጣሉ ተመለከትሁ፡፡

እስከትሉም በቀኙ ያሉትን በብዙ ምስጋና ካከበራቸው በኋላ "እናንተ ፅድቅን ስትጠባበቁ ለነበራችሁት እነሆ ዘመን መጥቶላችኋል ዳግመኛ ሃዘን እና ለቅሶ ወደሌለባት፤ ሰላም ሳይፈጠር ወዳዘጋጀሁላችሁ ወደ እረፍታችሁ ግቡ፡፡ እናንተ ተርቤ አብልታችሁኛል፡ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል፤ ታምሜ ጠይቃችሁኛል፡ ታርዤ አልብሳችሁኛል በጎድኖቼ ለም እንኳን ያደረጋችሁት መልካም ነገር በፊቴ አለ" በማለት ወደ መንግስተ ሰማያት እንዲገቡ ሲያዝዝ 'በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት የዳኑ' የሚል ቁልፍ ለሁሉም ተሰጣቸው፡፡ እነርሱም በብዙ ፍንደቃ እየቦረቁ ወደ አባታቸው መንግስት በዝማሬ እና በእልልታ ሲገቡ አየሁ፡፡

ቀጥሎም በታላቅ ሰንሰለት ታስሮ የዘንዶ መልክ ያለው ሰይጣን ከነጭፍሮቹ ጋር በታላላቅ መላእክት ተይዞ ወደ እሳት ባህር ሲወረወር ተመለከትሁ፡፡ በኋላም ጌታ በአጠገቤ ቆሞ ለምድር ነገሲታት እና አገሮች መልእክቱን ታደርሳለህ በማለት ከትልልቅ አገሮች እስከ ትንንሽ ደሴቶች ድረስ ወዳሉ የአለም ህዝቦች የመጨረሻውን ዘመን በረከት እና እርግማን ለሰው ልጆች ሁሉ መልእክቱን ይነግረኝ ጀመር፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## የመጨረሻው ዘመን የጌታ ትንቢት

### የመጪው ዘመን የዓለም ገፅታ

ከዚህ ሁሉ በኋላ ጌታ የመጪውን ዘመን የአለም ሁኔታ በዝርዝር ያሳየኝ ጀመር:: እንዲህም አየሁ እስራኤላውያን የሰለሞን ቤተመቅደስ በፈረሰበት ወቅት ሳይደረመስ የቀረው የቤተመቅደሱ አካል ነው ብለው የሚያምኑት እና ዌስተርን ዎል ብለው የሚጠሩት ግንብ የሚገኝበት የፂዮን ተራራ ከአለም ተራሮች ሁሉ በላይ እጅግ ከፍ ብሎ ሲወጣ ይታየኝ ጀመር:: ይህ ተራራ እጅግ ለምልሞ እና አምሮ ይታይ ነበር::

የአለም ተራሮች ሁሉ ቀስ በቀስ እያነሱ! እያነሱ! ዝቅ እያሉ ሲሄዱ ይህ ተራራ ግን ከፍታው እየጨመረ ይመጣ ነበር:: በተመሳሳይም በምስራቅ አፍሪካዊቷ ኢትዮጵያ የሚገኘውም የራስ ዳሽን ተራራ ከእስራኤሉ ተራራ ቀጥሎ ከሌሎች ተራሮች ሁሉ ከፍ እያለ ሲሄድ አየሁት:: ከዚህ በኢትዮጵያ ካለው ተራራ ውጪ ያሉት የአለም ተራሮች በሙሉ ለእስራኤሉ ተራራ ሲሰግዱለት አየሁ::

በእስራኤሉም ተራራ ላይ አሁን ካለው ባንዲራ በምስጢር እጋንንታዊ የሆነ 666 ቁጥር ተፅፎበት የተሻሻለ የእስራኤል ባንዲራ ተሰቅሎበት አየሁ:: እንደዚሁም በምስራቅ አፍሪካ ከፍ ባለው እና በኢትዮጵያ በሚገኘው የራስ ዳሽን ተራራ ላይ ደግሞ የመስቀል ምልክት ያለበት የኢትዮጵያ ባንዲራ ተሰቅሎበት ተመለከትሁ:: እያየሁም አንድ ግዙፍ እጅ ከሰማይ ተዘርግቶ ከእስራኤሉ ተራራ ይልቅ የኢትዮጵያን ራስ ዳሽን ተራራ ወደላይ ከፍ ሲያደርገው አየሁ::

ጌታም የዚህን ራዕይ ትርጉም አብራራልኝ:: ትርጉምም እንዲህ ነው:: የአለም አገሮች ሁሉ ሀብት ተሰብስቦ ወደ እስራኤል እና ኢትዮጵያ ይመጣል::

ለሞት እና ለስደት እንዲሁም ለከፍተኛ እንግልት በተለያዩ የአለም አገሮች ለባርነት ይዳረጋሉ፡፡

በእስልምና ሐይማኖት ውስጥ ካሉት አፓንንታዊ ሁንች በመነሳት አንዳንድ አክራሪ ድርጅቶች የእምነቱ ተከታይ ባልሆኑ ሰዎች ላይ በሚያደርሱት ተደጋጋሚ የሽብር ጥቃት ሳቢያ ሙስሊሞች በአለም ላይ ከፍተኛ የሆነ አድሎ እና መገለል ይደርስባቸዋል፡፡ ሐይማኖቱም በአለም ላይ የሚጠላ እና የሚወገዝ ይሆናል፡፡ እናም ቃዲያ በእነዚህ የእስልምና አክራሪ ሀይላት እኩይ ተግባር የተማረሩ የአለም አገራት በተለያዩ ችግሮች ከየአረብ አገራቱ የሚሰደዱ እነዚህን ሰደተኞች ላለመቀበል ይወስናሉ፡፡ ስለሆነም አብዛኛው የአረብ ሰደተኛ ህዝብ ሰሙን እና ሃይማኖቱን እየቀየረ ከሌላው ህዝብ ጋር የኢኮኖሚ ጥገኛ ሆኖ መኖር ብቸኛ አማራጩ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የዚህ መፅሃፍ ትንቢት ቃል አስቀድሞ የገባቸው አንዳንድ የሙስሊም አገሮች መሪዎች እና ባለሃብቶች በኢንቨስትመንት እና በልማት ስም ወደ አፍሪካ አስቀድመው ንብረታቸውን እና ቤተሰባቸውን ያሸሻሉ፡፡ በተለይም የምስራቅ አፍሪካን ኢኮኖሚ በአጭር ጊዜ ለመቆጣጠር ይተጋሉ፡፡ ቢቻላቸውም በተለይምበኢትዮጵያ ያሉትን ሙስሊሞች በማነሳሳት በፖለቲካና በኢኮኖሚው ዘርፍ የበላይነቱን ለመያዝ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከአፍሪካ አገራት በላይ ከፍ ብሎ ያድጋል፡፡ ሆኖም ግን በዚህ የሙስሊሙ የመስፋፋት ፍላጎት እና በኦርቶዶክስ እንቢ ባይነት መሃከል ለተወሰኑ ዓመታት የማያቋርጥ ፍትጊያ እና ፍጥጫ ይሆናል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን የአገሬው ሰው ፊቱም በአረቦቹ ላይ በማመፅ ሃብት እና ንብረታቸውን በገዛብዞ ያባርራቸዋል፡፡ ይህም የሚሆነው የአለምን ሃብት እና ወታደራዊ ሃይል በሰውር በተቆጣጠሩት ፂዮናውን ድጋፍ አማካኝነት ነው፡፡

ለእነዚህ ሁሉ ምርቶች ምቹ የሆነ መልክአ ምድር እና ለም የሆነ መሬት በመኖሩ እነዚህን የግብርና ውጤቶች ከአገር ውስጥ ወደ ውጪ በመላክ አገሪቱ ከመሪዎቹ ተርታ ትሰለፋለች። በተጨማሪም በአገሪቱ ውስጥ በፋብሪካ የተቀነባበሩ ምርቶችም ለአለም ገበያ ይቀርባሉ። በዚህም ምክንያት የአገሪቱ ህዝቦች እኩል የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ስለሚሆኑ እና የህዝቡ ንቃት ህሊና በትምህርት እና በቴክኖሎጂ እድገት ሳቢያ በሚያገኙት እውቀት ስለሚጎለብት ዘረኝነት እና ጎሰኝነት ቀስ በቀስ እየተሸረሸረ ይጠፋል። ህዝቡም ሁሉ ኑሮውን በማሻሻል ስራ ላይ ያተኩራል።

ቁስሉን ከማከም ይልቅ እያከኩ የሚያባብሱበትን እና ስለ እርሱ እያወሩ የስኬት መወጣጫ እርካብ የሚያደርጉትን ፖለቲከኞች ወሬ ከማዳመጥ ጆሮውን ይመልሳል፤ ከፖለቲካው ፈተናም ይበስላል። በዚህም ምክንያት ከፖለቲከኞች ይልቅ የብዙሃኑ ህዝብ አቅም ይበረታል። የኢኮኖሚ እድገቱን አስካልገታው ድረስ ማንም ይግዛው ማንም ግድ የሌለው ትውልድ ይነሳል። በአገሪቱ ያሉት የኦርቶዶክስ እንዲሁም የሌሎች ሃይማኖቶች እና የብሔር ብሔረሰቦች ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶች እና የአኗኗር ዘይቤዎች ከወትሮው በበለጠ የአለም ቱሪስቶችን ቀልብ ይገዛሉ።

በመጀመሪያ በፕሮቴስታንቶች ውስጥ የሚነሳው ለአለም ሞዴል የሚሆን የመንፈስ ቅዱስ ተሃድሶ በተቀቡ ነብያት ደምቆ ለአለም ህዝብ የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት ምክንያት ይሆናል። በዚሁም ምክንያት በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቃሉን ብቻ ነጥለው የሚሰብኩ አገልጋዮች በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት እንዲሁ ታላቅ ተሃድሶ ይሆናል። ለአለም ህዝቦች በሙሉ ሚሽነሪዎችንና የቴሌቪዥን ስርጭቶችን በማስተላለፍ እና ድንቅ እና ተአምራት በማሳየት በማስገረም ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይማርካሉ።

አዳዲስ ችግኞችን በመትከል ስራ ላይ በማተኮራቸው ነው አለኝ። በእነዚህ የምስራቅ አፍሪካ አገራት እጅግ ብዙ መአድናት መውጣት ይጀምራሉ። የወጡትም እስካሁን ከወጡበት አቅም አስር እጥፍ እና ከዚያም በላይ መውጣት ይጀምራሉ።

ከጥቂት አመታት በኋላ እነዚህ አገራት ከነዳጅ ላኪ አገራት ተርታ ይሰለፋሉ። በዚህም ሳቢያ የነዳጅ ላኪ አረብ አገራት ተገዳዳሪ ሆነው ብቅ ይላሉ። እናም ይህ የነዳጅ መአድን በተባበሩት መንግስታት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ በይፋ ለሰው ልጆች ሁሉ አደጋ በማለት እስኪፈርጀው እና አገልግሎት እንዳይሰጥ እስከሚታገድ ድረስ እነዚህ አገሮች ይህ ማዕድን ከሚያስገኘው ጥቅም ተቋዳሽ ይሆናሉ።

ኢትዮጵያም በዚሁ አመት መጀመሪያ ላይ በይፋ ከአለም ነዳጅ ላኪ አገራት ተርታ ትሰለፋለች። በመቀጠልም ኡጋንዳ፣ ኬንያ፣ ሱማሊያ፣ ጅቡቲ፣ ከውቂያኖሶቻቸው ሳይቀር ይህንን መአድን ማፈስ ይጀምራሉ። በቅርቡ በእነዚህ አገሮች ነዳጅ በመፈለግ ስራ ላይ ያሉ ኩባንያዎች በፍለጋቸው ውጤታማነታቸውን በይፋ ማስታወቅ ይጀምራሉ። ነገር ግን ኢትዮጵያ በምታገኘው ነዳጅ ዘይት ብቻ ሳይሆን የምትባረከው በልጆቿ እና በእኔ ብቻ ነው አለኝ ጌታ።

እንዲህም አለኝ በምስራቅ አፍሪካ እጅግ የከበረ ወርቅ፣ ታንታኒየም፣ የከበሩ ድንጋዮች፣ ፎስፈረስ፣ የተፈጥሮ ጋዝ፣ መዳብ፣ ፕላቲኒየም፣ ሶዳ አሽ፣ ጨው፣ ብረት፣ ፖታሽ፣ ንኬል፣ የድንጋይ ከሰል፣ ማንጋኒዝ፣ ማርብል፣ ሲመንት፣ ዩራኒየም፣ ካስትራይት፣ ቶፓዝ፣ ኦፓል፣ ፍሊንት፣ እንዲሁም የዳይመንድ ከምር በቀይ ባህር ውስጥ እና በደቡባዊ ሱማሊያ፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ የህንድ ውቂያኖስ አካባቢ ይገኛል። ይሄ አካባቢ ብዙ አገሮች በተፈጥሮ አደጋ ያለማቋረጥ

በሚንገላቱበት ወቅት በተለያዩ የእድገት ምንጮች፣ በሰላምና በእድገት ለአለም ተምሳሌት ሆኖ ይቀጥላል አለኝ።

በመቀጠልም የደቡብ አፍሪካ አገሮችን የበረከት ምንጭ እንዲህ በማለት ተናገረኝ። ይህ አካባቢ መጠነኛ የገቢ መቀነስ ቢታይበትም ነገር ግን አገራቱ በዙሪያቸው ከሚገኘው የህንድ እና የአትላንቲክ ውቅያኖስ ድንበር አካባቢ የነዳጅ ዘይት፣ ዩራኒየም፣ ዳይመንድ፣ እንዲሁም ወርቅ፣ ፕላቲኒየም፣ ማንጋኒዝ፣ ፎስፌት፣ ወዘተ በገፍ ያመርታሉ። በዚህ ምክንያት እጅግ ብዙ ሃብታም መንግስታት ከዚህ አካባቢ ይነሳሉ። ኢኮኖሚያቸውም የተረጋጋ ሆኖ ለሰው ሁሉ በሚጠቅም መልኩ ስራ ላይ ይውላል።

በዚህ አካባቢሙቀት የሚጨምር ቢሆንም ግን አስቀድመው አካባቢያቸው ላይ ለደኖች እና ለችግኝ ተከላ ልዩ ትኩረት ከሰጡ ይከላከሉታል አለኝ። በምእራብ አፍሪካ አካባቢ ወደፊት ስለሚኖረው ሁኔታ ጌታ እንዲህ አለኝ። ይሄ አካባቢ በአለም ላይ እጅግ ብዙ ገቢ ከሚያገኙ አካባቢዎች መሃከል ይሆናል። የዚህ አካባቢ ነዋሪዎች ተግዳሮት የሆነው የወረርሽኝ በሽታ በተለያዩ ጊዜ አካባቢውን ቢያጠቃውም በአገራቱ በእኔ የተቀቡ አገልጋዮች ይህንን የጠላትን እቅድ የማፍረስ ብቃት አላቸው አለኝ።

ይሄ አካባቢ ከየትኛውም የአፍሪካ ክፍል እጅግ በመልደግን የበለፀገ ነው። 50 ከመቶ የሚሆነው የእድገታቸው ምንጭ ከመእድናት የሚያገኙት ገቢ ነው አለኝ። እንደ አውሮፓውያን የዘመን ቀመር ከ2020 ጀምሮ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል በዚህ አካባቢ ይሰፍናል። ይህ አካባቢ የብዙ አለም አቀፍ ኢንተርፕረነሮች መነሻ ይሆናል። በዚህ አካባቢ የሚገኙ አገራት አስቀድመው የአካባቢ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ አንድነትን ከእነዚህ አመታት ጀምሮ ያፀድቃሉ ካለኝ በኋላ በአካባቢው የሚገኙትን መእድናት ማለትም ወርቅ፣ የነዳጅ ዘይት፣ ብረት፣

ይናገረኝ ጀመር፡፡ እነዚህ የአውሮፓ አገራት ለበረከታቸው ምክንያት እኔ ነበርኩ፡፡ ነገር ግን አሁን አብዛኛዎቹ ትተውኛል፡፡ በብልፅግና እና በሲጋ እውቀት ለውጠውኛል፡፡ እኔ የከፈትሁትን አዕምሯቸውን ለጥፋት እና ለሲይጣናዊ አስተምህሮት ሸጠውታል፡፡ አልፈውም በአዳም እርግማን ምክንያት የመጣውን ስራ መኖሪያቸው አድርገውታል፡፡ 'ሰው መኖሪያው ስራ ነው' በማለት በግልፅ ሲናገሩ እንኳን አያፍሩም፡፡ ያ ብቻ አይደለም ከርስትና ያረጀ ኋላቀርነት ሆኖባቸዋል፡፡ የአባቶቻቸውን ፀሎት እና እንባ ገደል ከትተውታል፡፡ አንዳንዶች ከዚህ አልፈውም በከህደት ተሞልተዋል፤ ሌሎቹም በመቅደሴ በግብረሰዶማዊነት ሰደቡኝ፡፡ ይባስ ብለው ወንድ ከወንድ ሴት ከሴት አጋቡበት፡፡

ያ ብቻ አይደለም በቤተከርስቲያኔ የሙዚቃ ድግስ እያዘጋጁ ዘሞቱበት፤ ጨፈሩበት፡፡ በደሜ ዋጋም ቀለዱበት፡፡ ሰጪውን ትተው ስጦታውን አሰበለጡ፡፡ ተምረው ተምረው ደነቆሩ እንጂ አላወቁም፡፡ በዚህም ምክንያት በሚቀጥሉት አመታት በፂዮናውያኑ ቢልየነሮች በተለያየ ወቅት ከባድ የኢኮኖሚ ቀውስ እና ኪሳራ ይደርስባቸዋል፡፡ በነገራችን ላይ እነዚህ ፂዮናዊ ቢሊየነሮች አሁን በአለም ላይ የምናውቃቸው ቢሊየነሮች እንዳልሆኑ ማወቅ አለባችሁ፡፡

እነዚህ ቢሊየነሮች የአለምን አንድ ሶስተኛ ሃብት በተለያየ ድርጅት እና ካምፓኒ ስም የተቆጣጠሩ ናቸው፡፡ በተለያዩ ድርጅቶቻቸው እና ባንኮቻቸው በትሪሊየን የሚቆጠር ሃብት ባለቤት ናቸው፡፡ ለመንግሲታት ጭምር ብድር የሚሰጡ ናቸው፡፡ ፈፅመው በስውር ነው የሚንቀሳቀሱት፡፡ በአሁን ሰዓት እንኳን አቅማቸው ከአሜሪካ ጀምሮ ታላላቅ የሚባሉ የአለም አገራትን በአንድ ጀምበር ድሃ የማድረግ አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህም ነው እነዚህ ሰብሰቦች በፈለጉ ሰዓት የኢኮኖሚ መዋዠቅን የሚያመጡት፡፡ የባለፈው የኢኮኖሚ ውድቀት አቅማቸውን የሞከሩበት እንጂ የመጨረሻቸው አይደለም፡፡ ከ2031 ጀምሮ ግን በአለም ህዝቦች ላይ የኢኮኖሚ ውድቀቶችን በማምጣት ቻይናን ሳይቀር አሜሪካን እና አውሮፓን አሽመድምደው የበላይነትን ይወስዳሉ አለኝ፡፡

# የንስሃ ፀሎት

ቃልህ ሊናገር ሊያስብ ጌታ እንደሆን በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህ እና ሰው በልቡ አምኖ ይፀድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና። በእርሱ በሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም። በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁኑኑ ተፈርዶበታል። በእውነት እና በመንፈስ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና እንደሚል ጌታ ኢየሱስ ሆይ ይህንን ታላቅ መልእክትህን አንብቤያለሁ፤ እውነተኛ አምላክ እንደሆንክም አምኛለሁ፤ መዳን ከአንተ ውጪ በሌላ በማንም እንደሌለም ገብቶኛል ስለዚህም ልቀበልህ ወስኛለሁ፤ ሀጢያቴን ይቅር በለኝ፣ ከዚህ ካነበብኩት ዘላለማዊ ቅጣት አድነኝ፤ ይልቁንም በሰው ቋንቋ የማትገለፀውን መንግስትህን አውርሰኝ፤ ስሜን በህይወት መዝገብ ላይ ፃፍልኝ፤ አመሰግንሃለሁ። አሜን።

ራእዩን የሰጠ ጌታ የተባረከ ይሁን። በመጨረሻ ጌታ እንዲህ አለኝ "ይህንን መልእክት ያነበባችሁ እና የሰማችሁ በሙሉ ይህ መፅሃፍ ከመፅሃፍ ቅዱስ ቀጥሎ እጅግ ለፍጥረት ሁሉ አስፈላጊ ሆኖ ዘላለም የሚናገር የትንቢት እና የራእይ መፅሃፍ መሆኑን አስታውቃችኋለሁ። ማንም እዚህ መፅሃፍ ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ አይችልም። እነሆ እኔ በቶሎ እመጣለሁ ለሁሉም እንደ ስራው እከፍል ዘንድ ዋጋዬ በእጄ ነው። ድል ለነሳው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ። በሁለተኛውም ሞት አይጠፋም። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ" አለኝ። አሜን ማራናታ ጌታ ሆይ ቶሎ ናልን። አሜን።

-ተፈፀመ-